ትማር
TIMMAR

FAWE
Ethiopia

ፋዌ ኢትዮጵያ ብሄራዊ ቻፕተር ዓመታዊ መጽሄት
FAWE-Ethiopia National Chapter Annual Magazine



ቅፅ 21/Volume 21
ታህሳስ 2015/December 2022

የቱሰሜ (እኛም እንናገር!) ስልጠና ተሳታፊዎች

Participants of TUSEME (Lets's Speak Out!) training



ይዘት/Contents

የፋዌ - ኢትዮጵያ ጽ/ቤት ዳይሬክተር መልዕክት.....1
የፋዌ - ኢትዮጵያ ቻፕተር ዓመታዊ የሥራ ክንውን.....2
የቁንፅል ቀሚስ ተቃዋሚ የሕግ መምሪያ ምክርቤት አባሏ.....7
የትማር እንግዳ፣ ወ/ሮ አልማዝ ገ/ዮሃንስ.....9
የአብክመ ትምህርት ቢሮ እና የፋዌ - ኢትዮጵያ ትብብር.....11
አርአያዎቻችን.....13
ለፋዌ - ኢትዮጵያ ፕሮግራሞች ስኬት የባለድርሻ አካላት አስተዋፅኦ.....15
በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚከሰት እርግዝናና ተፅእኖዎቹ.....16
የፋዌ - ኢትዮጵያ ንዑስ ቻፕተሮች ዓመታዊ ሪፖርት.....18
ህፃናትን ከወሲባዊ ጥቃት ለመከላከል.....21
ቆይታ ከቀድሞ የፋዌ - ኢትዮጵያ ስኮላርሺፕ ፕሮግራም ተጠቃሚዎች ጋር.....22
MESSAGE FROM FAWE-ETHIOPIA EXECUTIVE DIRECTOR.....29
OVERVIEW OF FAWE-ETHIOPIA'S ANNUAL ACCOMPLISHMENTS.....30
TIMMAR GUEST.....35
THE WOMEN WHO OPPOSES WEARING A MINISKIRT.....37
INTERVIEW WITH FORMER FAWE-ETHIOPIA SCHOLARSHIP BENEFICIARIES.....38
COOPERATION BETWEEN FAWE-ETHIOPIA AND AMHARA NATIONAL REGIONAL GOVERNMENT EDUCATION BUREAU.....42
CONTRIBUTION OF STAKEHOLDERS TO THE SUCCESS OF FAWE-ETHIOPIA'S PROGRAMS.....44
FAWE-ETHIOPIA SUB-CHAPTERS ANNUAL REPORT (2013-2014/2022).....46

FAWE-ETHIOPIA COLLABORATORS:

- MINISTRY OF EDUCATION
- REGIONAL FINANCE AND ECONOMIC DEVELOPMENT BUREAUS
- REGIONAL STATE EDUCATIONAL BUREAUS
- REGIONAL STATES WOMEN, CHILDREN AND SOCIAL AFFAIRS BUREAUS
- FAWE-ETHIOPIA'S SUB-CHAPTERS
- MASTERCARD FOUNDATION/MCF
- MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS OF NETHERLAND
- GOVERNMENTS OF UNITED KINGDOM, IRELAND, SWEDEN, AND NORWAY (CIVIL SOCIETY SUPPORT PROGRAMME 2/CSSP2)
- NETWORK OF ETHIOPIA WOMEN'S ASSOCIATIONS/NEWA
- BASIC EDUCATION NETWORK ETHIOPIA/BEN-E

PUBLISHER:
FAWE ETHIOPIA CHAPTER
PHONE NUMBERS: OFFICE- 011-6-676645
011-6-676679
FAX: 011-6-676657
E-MAIL: FAWE@FAWEETHIOPIA.ORG
P.O.BOX: 20882,CODE 1000

EDITORS
ROMAN DEGEFA
GETENET MAMMO

DESIGNED AND PRINTED BY:
MM PRINTING
E-MAIL: mmprinting22@gmail.com
MOBILE NUMBERS: +251-011-868 8685
+251911 24 7878

የፊት ሽፋን ፎቶ/Front cover photo

የአምስተኛው ዙር የማስተርካርድ ስኮላርሺፕ ፕሮግራም የምረቃ ሥነስርዓት

The Fifth Cohort Graduation Ceremony

Vision

FAWE-Ethiopia's Vision is to see a country in which there is no gender disparity in the education of the country.

Mission

In line with the vision, FAWE Ethiopia's mission is also derived from the Regional Secretariat's. In partnership with strategic partners, national governments, educators, researchers, influencers and local communities, FAWE Ethiopia Chapter will foster innovations, promote positive policies/practice and provide opportunities for girls and young women, especially those in extreme adversity, to develop skills and competencies that will allow them to be productive members of their societies.

General goal

The general goal is to empower girls and women in Ethiopia with all-rounded employable skills, values and competencies they need to achieve their full potential.

Strategic goal

SO1: Girls and young women including disabled, displaced, Women living with HIV/AIDS, and those marginalized across the regions and city administrations of Ethiopia have access to quality education and training opportunities to develop relevant skills for the world of work.

SO2: Education systems in Ethiopia integrate gender-responsive approaches and policies to nurture skills and competencies for girls and women to contribute to their societies.

SO3: FAWE Ethiopia Chapter has the institutional capacity developed (networking, leadership, technical & financial) to deliver its mandate to the best level

SO4: FAWE Ethiopia Chapter has in place research and knowledge management systems to inform policies, new approaches and set pace for girls' agenda in Ethiopia's development platforms.

Values

FAWE Ethiopia Chapter values professionalism, accountability, and integrity. We are passionate about results, and are dedicated in everything we do.

Governance

- **General assembly**
- **Board**

The board has 7 members 100% female.

Management committee

The management committee has 4 members with 50% female

የፋዌ ኢትዮጵያ ጽ/ቤት ዳይሬክተር መልዕክት



ወ/ሮ ሮማን ደገፋ

አንድ ሃገር በኢኮኖሚም ሆነ በማህበራዊ አንቅስቃሴ በምታደርገው ሁለንተናዊ ለውጥ ውስጥ፣ ለሴቶች ትምህርት የሚሰጠው ትኩረት ከማናቸውም ተግባራት በላቀ ሁኔታ ሁነኛ ሥፍራ ያለው መሆኑ ይታወቃል። በአሁኑ ወቅት፣ ከቀደሙት ጊዜያት በተለየ ሁኔታ፣ የዓለማችን ሃገራት፣ በተለይም በማደግ ላይ ያሉ ሃገራት በመላ፣ ለሴቶች ትምህርት ልዩ ትኩረት እየሰጡ የሚገኙት፣ ሴቶች በማናቸውም የልማትም ሆነ ሌሎች ሃገራዊ ጉዳዮች ውስጥ ያላቸውን ይህን ሁነኛ ስፍራ በመረዳት ነው።

ፋዌ - ኢትዮጵያ፣ ሃገራችን ድህነትን በመዋጋት ወደ እድገት በምታደርገው ግስጋሴ፣ የሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ያለውን ጉልህ ድርሻ እና ጠቀሜታ በመረዳት፣ ሴቶች በትምህርት ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ በሚያሳድጉባቸው፣ በተለያዩ መስኮችም ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያስችሏቸውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን ፕሮግራሞችን በመንደፍ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ያለ ሀገር በቀል የሰቪል ማህበረሰብ ድርጅት ነው። ፋዌ - ኢትዮጵያ እየተገበራቸው ያሉ እነዚህ ፕሮግራሞቹ፣ ሴት ተማሪዎች በእለት ተእለት ኑሮቸው ከሚያጋጥሟቸው አሉታዊ ጫናዎች ራሳቸውንነፃ በማድረግ፣ በትምህርታቸው እንዲገፉ የሚያስችሉ ናቸው። በዚህም ሂደት፣ በርካታ ሴት ተማሪዎች የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጫናዎችን ተቋቁመው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁና በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች መማር የሚችሉባቸውን እድሎች መፍጠር ከመቻሉም በላይ፣ እነዚሁ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወቅት በተደረጉላቸው ሁለንተናዊ ድጋፎች መሰረት ከተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው በተለያዩ የሥራ መስኮች ሃገራቸውን ማገልገል የሚችሉ ዜጎች መሆን ችለዋል። የእነዚህ ወጣቶች ስኬት የሚጠቁመው፣ የሃገራችን ሴት ተማሪዎች ሁኔታዎች ከተመቻቹላቸው የሚፈልጉት ደረጃ ድረስ መድረስ የሚያስችላቸው ቁርጠኝነት እና ብቃት ያላቸው መሆኑን ነው። ፋዌ - ኢትዮጵያ፣ እነዚህ ሴቶችም ሆኑ በተለያዩ ፕሮግራሞቹ የድጋፉ ተቋዳሽ የሆኑ ወንድ ተማሪዎች የተደረጉላቸውን ድጋፎች ወደውጤት በመቀየር፣ ለፋዌ - ኢትዮጵያ ዓለማ ስኬት የበኩላቸውን ሚና መጫወት በመቻላቸው ያለኝን አድናቆት በዚህ አጋጣሚ በፋዌ - ኢትዮጵያና በአጋሮቹ ስም መግለፅ እወዳለሁ።

ፋዌ - ኢትዮጵያ፣ ለበርካታ ዓመታት የተገበራቸው ሴት ተማሪዎች ላይ ያተኮሩ የተለያዩ ተግባሮቹ አኳያ ላስመዘገባቸው ተጨባጭ ውጤቶች፣ ከተለያዩ የሃገር ውስጥና የውጭ አጋር ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር መፍጠር የቻለው ጠንካራ አጋርነት ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። ለዚህም፣ በየዓመቱ ያከናወናቸው ተግባራት እና በተጨባጭም ያስመዘገባቸው ውጤታማ የሥራ እንቅስቃሴዎቹ ሀያው ምስክር ናቸው። በዚህ አጋጣሚ፣ እነዚህ አጋርና ባለድርሻ አካላት፣ የፋዌ - ኢትዮጵያን ዓላማና ራእይ በመረዳት፣ በእስካሁኑ ጉዞውም ያከናወናቸው ተግባራት በውጤት የታጀቡ መሆናቸውን በመገንዘብ፣ በተለያዩ ድጋፎቻቸው ከጎኑ ሆነው ስለዘለቁ፣ በፋዌ - ኢትዮጵያ ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ፤ ይኸው ድጋፋቸውም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያለኝን እምነት በዚህ አጋጣሚ እገልፃለሁ።

ሴትን ማሰተማር ሀብረተሰብን ማሰተማር ነው ! !

የፋዌ ኢትዮጵያ ቻፕተር ዓመታዊ የሥራ ክንውን

ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ መንግስታዊ ያልሆነው የፓን አፍሪካው ሴት የትምህርት ባለሙያዎች ድርጅት (FORUM FOR AFRICAN WOMEN EDUCATIONALISTS/ (FAWE) እ.ኤ.አ. 1994 ዓ.ም በአሀጉር አቀፍ ደረጃ ምስረታው ከተበሰረ ከሁለት ዓመት በኋላ፣ በኢትዮጵያ ሴት የትምህርት ባለሙያዎች የተቋቋመ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ነው። ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ እ.ኤ.አ. 2003 ዓ.ም ላይ በኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር፣ በ2010 ደግሞ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ሲቪል ማኅበራት ኤጀንሲ የተመዘገበ ሲሆን፣ በአዋጅ ቁጥር 1113/2019 መሰረት እንደገና በተዋቀረው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን 2019 ዳግም ተመዝግቦ፣ በሃገራችን ትምህርት ያለምንም ዕታዊ አድልኦ እንዲሰጥ በትኩረት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ ድርጅት ነው።

ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ ለምስረታው መሰረት የሆኑትን ዋና ዋና ዓላማዎቹንና ግቦቹን ዳር ለማድረስ፣ ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር፣ በተለይም ከእናት ማህበሩ ፋዌ አህጉራዊ ጽ/ቤት (FAWE-RS) ጋር በመተባበር በሚቀርፃቸው የተለያዩ ፕሮጀክቶቹና ፕሮግራሞቹ አማካይነት የተለያዩና የሴት ተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎን ያማከሉ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፤ እያከናወነም ይገኛል። ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ አጋር ድርጅቶቹ ድጋፍ፣ እየተገበራቸው ያሉ አራት ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች አሉት፣ ፣ እነዚህም፣ በማስተርካርድ ፋውንዴሽን (MASTERCARD FOUNDATION/MCF) ድጋፍ የሚከናወን የተማሪዎች የስኮላርሺፕ ፕሮግራም፣ ብሬክፍሪ ፕሮጀክት (BREAK FREE PROJECT)፣ ሜክዌይ ፕሮጀክት (MAKE WAY PROJECT) እና የሲቪል ማህበረሰብ ድጋፍ ፕሮግራም 2 (CSSP2) ናቸው። እነዚህ ፕሮጀክቶች እየተተገበሩ ያሉት፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሚገኙት በባህርዳር እና በደብረብርሃን ከተሞች፣ በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሚገኙት አሌልቱ ወረዳና በአዳማ እና ሸኖ ከተሞች፣ በሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መቀመጫ በሆነችው ሃዋሳ ከተማ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲሆን፣ ለዓመቱ ለየፕሮጀክቶቹ አፈፃፀም በተነደፈው የ2022 ዓ.ም. እቅድ መሰረት የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። የእነዚህ ተግባራት የዓመቱ ዋና ዋና አፈፃፀም፣ ቀደም ብለን በጠቀስናቸው ዋና ዋና ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መሰረት፣ እንደሚከተለው ቀርቧል።

የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሺፕ ፕሮግራም

የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሺፕ ፕሮግራም፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጫና ቢኖርባቸውም በትምህርት አቀባበላቸው ጎበዝ የሆኑና የነገ ሃገር ተረካቢ ብቁ ዜጎች ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ተማሪዎችን ለመደገፍ የተመቻቸ የስኮላርሺፕ ፕሮግራም ነው። እ.ኤ.አ. ከ2014 ዓ.ም. ጀምሮ እየተተገበረ ያለው ይህ የፋዌ-ኢትዮጵያ ስኮላርሺፕ ፕሮግራም፣ በማስተርካርድ ፋውንዴሽን ሁለንተናዊ ድጋፍ በባህርዳር፣ በአዳማ፣ በሃዋሳ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እየተከናወነ ያለ ፕሮግራም ነው። በተጠናቀቀው 2022 ዓ.ም.፣ ለፕሮግራሙ በተያዘው እቅድ መሰረት የተለያዩ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን፣ የእነዚህ ተግባራት አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል።

• ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ የሚሰጥ ትምህርት (GENDER RESPONSIVE PEDAGOGY/GRP) የተመለከተ የአሰልጣኞች ሥልጠና (TOT) ከግንቦት 19-21 ቀን 2022 ዓ.ም. ተካሂዷል። ቢሾፍቱ በሚገኘው በኢየሩሳሌም የህፃናትና ማህበረሰብ ልማት ድርጅት (ጀሲሲዶ) ማሰልጠኛ ማዕከል በተካሄደው በዚህ የአሰልጣኞች ሥልጠና፣ ከ8 ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ መምህራን ተሳታፊ ሆነዋል። ሥልጠናው በዋናነት ያተኮረው፣ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ በሚሰጥ ትምህርት ዙሪያ የመምህራንን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ማሰፋት እና የመማር ማስተማር ዘዴያቸውም በዚሁ የትምህርት አቀራረብ የተቃኘ በማድረግ ሁሉንም ተማሪዎቻቸውን ያለምንም ዕታዊ አድልኦና ልዩነት ክፍል ውስጥ እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ በሚችሉባቸው ሁኔታዎች ላይ ነው። ከዚህም ባሻገር፣ የየትምህርት ቤቶቹ አመራሮችም፣ የትምህርት አመራር ሥራቸው፣ የስርዓተ ፆታ ጉዳዮችን ያማከለ እንዲሆን እንዲያደርጉ የማስቻልና ግንዛቤ የመፍጠር ዓላማ ያለው ነው። በሥልጠናው፣ ከአዳማ፣ ከሃዋሳ፣ ከአዲስ አበባ እና ከባህርዳር ከተሞች የፕሮግራሙ አጋር ከሆኑ 8 ትምህርትቤቶች የተውጣጡ 29 (10 ሴቶች እና 9 ወንዶች) መምህራን ተሳትፈዋል። በሥልጠናው የተሳተፉ መምህራን ከሥልጠናው ያገኙትን ግንዛቤ፣ በየከተሞቻቸው ለሚገኙ ሌሎች 289 መምህራን ሥልጠናዎችን በማመቻት እንዲያስተላልፉ ተደርጓል።







ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ የሚሰጥ ትምህርት የአሰልጣኞች ሥልጠና ሂደት

• ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ የቱሰሜ/TUSEME (የስዋሂሊ ቃል ሲሆን፣ LETS'S SPEAK OUT! እንናገር! የሚል ፍቺ አለው) የተመለከተ የአሰልጣኞች ሥልጠና፣ አዳማ ከተማ በሚገኘውና የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም እየተተገበረበት ባለው ጎሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተካሂዷል። ከግንቦት 5-7 ቀን 2022 ዓ.ም. በተካሄደውና ሴት ተማሪዎች በትምህርታቸውም ሆነ በማህበራዊ እድገታቸው ላይ በሚነሱ የተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ሃሳባቸውን በይፋ እንዲገልፁ በሚያስችላቸው የቱሰሜ ፅንሰሀሳብ ላይ፣ በሁሉም ተማሪዎች ዘንድ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ክህሎትና ግንዛቤ በመፍጠር ላይ ባተኮረው በዚህ የአሰልጣኞች ሥልጠና ላይ ፅንሰሃሳቡን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ መፍጠር

ተችሏል። በዚህ የአሰልጣኞች ሥልጠና ላይ የተሳተፉ መምህራን፣ ከሥልጠናው መጠናቀቅ በኋላ፣ በየትምህርት ቤታቸው የቱሰሜ ፅንሰሃሳቦች እንዲሰርፁና እንዲተገበሩ፣ ተማሪዎቻቸውም በማህበራዊ ኑሮቸውም ሆነ በትምህርት አቀባበላቸው ራሳቸውን እንዲያበቁ እና በየትምህርት ቤቶቻቸውም የቱሰሜ ክበባትን የማቋቋም እንዲቋቋሙ የማድረግ ሃላፊነት ተጥሎባቸዋል። በሥልጠናው ላይ፣ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም ከሚተገበርባቸው አዳማ፣ ሃዋሳ፣ ባህርዳር እና አዲስ አበባ ከተሞች ከሚገኙ 8 ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ 18 መምህራን (10 ሴቶችና 8 ወንዶች) ተሳትፈዋል።



የቱሰሜ የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሳታፊዎች

•በተመሳሳይ፣ ይህንኑ የቱሰሜ ፅንሰሀሳብ የተመለከተ ሥልጠና፣ አዳማ በሚገኘው የጎሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለሆኑና ከ10ኛ እና ከ9ኛ ክፍሎች ለተውጣጡ 50 (30 ሴቶችና 20 ወንዶች) ተማሪዎች ተሰጥቷል። ከግንቦት 6-7 ቀን 2022 ዓ.ም. ለሶስት ቀናት በተሰጠው በዚህ የቱሰሜ ሥልጠና፣ ቀደም ብሎ በቱሰሜ የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሳታፊ የነበሩ መምህራን ፅንሰሃሳቡን በተመለከተ ግንዛቤ ከመፍጠራቸውም በላይ፣ በየትምህርት ቤቱ የቱሰሜ ክበባት እንዲቋቋሙ አድርገዋል።

•በፋዌ-ኢትዮጵያ ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ ያተኮረ የባለድርሻ አካላት ስበሰባ (REVIEW MEETING) አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ኤሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል እ.አ.አ መጋቢት 30 ቀን 2022 ዓ.ም. ተካሂዷል። በዚሁ ዓመታዊ የባለድርሻ አካላት ስብሰባ ላይ፣ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም ከሚተገበርባቸው አካባቢዎች/ክልሎች የተወከሉ 33 ያህል ባለድርሻ አካላት የተሳተፉ ሲሆን፣ የፋዌ-ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም የ2021 ዓ.ም. የአቅድ አፈፃፀምና የ2022 ዓ.ም አቅድ ቀርቦ ሰፋ ያለ ውይይት ተካሂዶባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ፣ በዚሁ ስብሰባ ላይ፣ በስኮላርሺፕ ፕሮግራሙ አማካይነት ተጠቃሚ በሆኑ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ የታየውን ለውጥ የተመለከተ የትምህርት ውጤት ከመቅረቡም በላይ፣ የስኮላርሺፕ ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች ስለስኮላርሺፑ ዘርፈብዙ ጥቅም ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፤ በ4ኛው ዙር የስኮላርሺፕ ፕሮግራም ተሳታፊ ለነበሩ እና በከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ማስመዘገብ ለቻሉ 6 ተማሪዎችም (3 ሴቶች ናቸው) የላፕቶፕና የተለያዩ ሽልማቶች በእለቱ ተበርክቶላቸዋል።

•ከዚህ በተጨማሪ፣ ፋዌ-ኢትዮጵያ በየሁለት ዓመቱ ከክልል ባለድርሻ አካላት ጋር የሚያካሂደው የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የስኮላርሺፕ ፕሮግራም አፈፃፀም ግምገማም፣ ፕሮግራሙ በሚካሄድባቸው ክልሎች በሚገኙ ከተሞች፣ ማለትም በባህርዳር፣ በአዳማ፣ በሃዋሳ በአዲስ አበባ ከተማ ተካሂዷል። የአፈፃፀም ግምገማው መካሄድ፣ ከተሞቹ በሚገኙባቸው ክልሎች የሚገኙ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት፣ ከፕሮግራሙ አፈፃፀም አኳያ በአዎንታዊነት ያስተዋሏቸውን ሁኔታዎች እንዲገልፁ እና በቀጣይም ፕሮግራሙ አስከሚጠናቀቅበት ወቅት ድረስ ሊሻሻሉ ይገባቸዋል የሚሏቸውን ሁኔታዎች እንዲጠቁሙ እድል የሰጠ ነበር።

•ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራም በሚካሄድባቸው በሁሉም ክልሎች፣ በየክልሉ ከተቋቋሙ የቀድሞ የስኮላርሺፑ ተጠቃሚ ተማሪዎች ማህበር አባላት ጋር ጉባኤ አካሂዷል። በዚህም መሰረት፣ እ.አ.አ. ሐምሌ 28 እና ነሐሴ 4፣ 10፣ 26/2022 ዓ.ም. በቅደም ተከተል በባህርዳር፣ በሃዋሳ፣ በአዳማ እና በአዲስ አበባ ከተሞች በተካሄዱት ጉባኤዎች፣ በጠቅላላው 129 (72 ሴቶችና 57 ወንዶች) የቀድሞ የስኮላርሺፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች የማህበር አባላት ተሳትፈዋል። የጉባኤው መካሄድ ዋና ዓላማ፣ የየማህበራቱ እንቅስቃሴ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ እና ማህበራቱ በቀጣይም የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ከአስካሁኑ በበለጠ መልኩ ስለሚያጎለብቱበት ሁኔታ ከማህበራቱ አባላት አስተያየት መሰብሰብ ላይ ያተኮረ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ፣ እነዚህ ማህበራት የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች፣ በተቋቋሙባቸው ዓላማዎች መሰረት አጠናክረው መቀጠል እንዲችሉ በየጉባኤዎቹ የየክልሎቹ ማህበራትን የሚመሩ 7 አባላት ያሏቸው የሥራ አስፈፃሚ አባላት ምርጫም በየጉባኤዎቹ ተካሂደዋል።

•የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ፕሮግራምን በመወከል ከኬፕታውን ዩኒቨርስቲ ከመጡ ባለሙያ ጋር የመረጃ መለዋወጫ ውይይት፣ መስከረም 1 ቀን 2022 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ቶፕ ቴን ሆቴል ተካሂዷል። ለግማሽ ቀን በተካሄደውና ከየዩንቨርስቲው ተመራቂ የሆኑ የቀድሞ የፋውንዴሽኑ ስኮላርሺፕ ተጠቃሚዎች በተሳተፉበት በዚህ ስብሰባ፣ 24 (12 ሴቶችና 12 ወንዶች) ተመራቂ ተማሪዎቹ ስኮላርሺፕ እድሎችን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ በባለሙያው ገለፃ ተደርጎላቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ፣ በእለቱ ከተካሄደው የመረጃ መለዋወጫ ውይይት ጎን ለጎን፣ ለእነዚሁ የውይይት ታዳሚዎች፣ ከደረጃ የምክር አገልግሎት በመጡ ባለሙያ በሥራ ቅጥርና ራስን ለሥራ ዝግጁ በማድረግ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ተሰጥቷል።

•አዳማ ከተማ በሚገኙት ናፍያድ እና ጎሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት ብቃት (PROFICIENCY) ማሳደግ ላይ ያተኮረ ሥልጠና፣ በአምስተኛው ዙር የስኮላርሺፕ ፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለሆኑ ተማሪዎች ፕራይም በተሰኘ የስልጠና ተቋም አማካይነት ተሰጥቷል።

•ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ ዲጂታል ኦፖርቹኒቲ ትረስት (DIGITAL OPPORTUNITY TRUST/DOT) ከተባለ በጎ አድራጊ ድርጅት ጋር በመተባበር፣ በንግድ ሥራ ክህሎት እና በሥራ ፈጠራ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ከጥቅምት 10-14 ቀን 2022 ዓ.ም. ድረስ ቢሾፍቱ በሚገኘው በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት የሥልጠና ማእከል አካሂዷል። ለሥራ ፈጠራ በተመደበ ሁለተኛ ዙር የስጦታ የገንዘብ ድጋፍ ለ5 ቀናት በተካሄደው በዚህ የንግድ ክህሎት እና የሥራ ፈጠራ ሥልጠና፣ 10 የቀድሞ የስኮላርሺፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች ተሳታፊ ሆነዋል።

•የቀድሞ የስኮላርሺፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች ዓመታዊ ጉባኤ፣ ቢሾፍቱ በሚገኘው የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት የሥልጠና ማእከል ህዳር

17 ቀን 2022 ዓ.ም. ተካሂዷል። በዚህ ዓመታዊ ጉባኤ ላይ፣ በየክልሎቹ የተቋቋሙ ማህበራት ኮሚቴዎች፣ በዓመቱ በየክልላቸው የተከናወኑ ተግባራትን የተመለከተ ሪፖርት አቅርበዋል። በየክልሉ ከተቋቋሙት የቀድሞ ስኮላርሺፕ ተጠቃሚ ተማሪዎች ማህበራት ውስጥ፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህርዳር ከተማና እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቋቋሙት ማህበራት፣ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው አካል ሆነው መንቀሳቀስ የሚችሉ መሆናቸውን የሚገልፅ ምዝገባ በሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጣቸው ናቸው።

•የአምስተኛው ዙር የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የስኮላርሺፕ ፕሮግራም ተጠቃሚ የ5ኛው ዙር ተማሪዎች የምረቃ ስነስርዓት፣ አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ኤሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል እ.ኤ.አ ህዳር 18 ቀን 2022 ዓ.ም. ተካሂዷል፡ ፡ በዚሁ የምረቃ ስነስርዓት ላይ፣ የማስተርካርድ ፋውንዴሽንን፣ የፋዌ አህጉራዊ ጽ/ቤትን፣ የተለያዩ አጋር ድርጅቶችን እና የተለያዩ የመንግስት ባለድርሻ አካላትን የሚወክሉ እንግዶች፣ በሜንቶርነት የሚያገለግሉ መምህራንና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተመራቂ ተማሪዎች ወላጆች ተሳታፊዎች ነበሩ። በምረቃው ሂደት፣ ስኮላርሺፕ ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው 8ቱ ትምህርት ቤቶች በስኮላርሺፑ የአፈፃፀም ሂደት በሜንቶርነት ተሳታፊ ለነበሩ 14 መምህራን በስኮላርሺፑ አተገባበር ሂደት ላበረከቱት አስተዋፅኦ ለእያንዳንዳቸው የስማርት ስልክ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። እንዲሁም፣ ከተመራቂ ተማሪዎች መካከል በየትምህርት ቤቶቻቸው ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ 16 ተመራቂ ተማሪዎች፣ የምስክር ወረቀትና የስማርት ስልክ ሽልማት በተመሳሳይ ሁኔታ በአለቱ ተበርክቶላቸዋል።





የ5ኛው ዙር ስኮላርሺፕ ተጠቃሚተማሪዎች የምረቃ ስነስርዓት ሂደት



የትምህርት ሚኒስቴር ተወካይ አቶ ሰለሞን ወርቁ በምረቃ ሥነስርዓቱ ላይ ንግግር ሲያደርጉ

ብሬክፍሪ ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት፣ በተለያዩ ባለድርሻ አካላትና አጋር ድርጅቶች ትብብር እየተተገበረ ያለ የአምስት ዓመት ፕሮጀክት ነው። የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ፣ በአፍላ እድሜ ላይ ያሉ ወጣቶች፣ ያለማንም ጣልቃገብነት እና በመረጃ ላይ በተመሰረተ ምርጫ፣ ከወሲብ እና ከስነተዋልዶ ጤና ጋር በተያያዘ በራሳቸው ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ በማድረግ፣ በዚህም ጥንቃቄ የጎደለውን የወሲብ ድርጊትን፣ ያለዕድሜ ጋብቻን፣ በዝቅተኛ ዕድሜ ላይ የሚኖር ልጅ የመውለድ ክስተትን፣ የግዳጅ ጋብቻን እና ያልታሰበ እርግዝናን፣ እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎችም የሚስተዋለውን የሴት ልጅ ግርዛትን የመሳሰሉ ችግሮችን መታገል ላይ ያተኮረ ነበር።

ይህ ፕሮጀክት፣ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ዓላማው መሰረት በተጠናቀቀው 2022 ዓ.ም. የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኗል።

•ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ በአፍላ ወጣቶች እና በወጣቶች ጤና ዙሪያ የተዋቀረው የቴክኒክ ቡድን አባል እንደመሆኑ፣ ከዓለም አቀፍ የትምህርት አገልግሎት ተቋም (INTERNATIONAL EDUCATION/PIE)፣ ከሴቶችና ህፃናት ልማት ድርጅት በኢትዮጵያ (ODWACE) እና ከኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማህበር (FAMILY GUIDANCE ASSOCIATION OF ETHIOPIA/FGAE) ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት፣ በሃገራችን የትምህርት ፖሊሲና በሌሎች ከፖሊሲው በሚመነጩ የትምህርት አቅጣጫዎችና ፖሊሲዎች መሰረት በሴቶች ትምህርት ዙሪያ እየተከናወኑ ያሉ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን የተመለከቱ በማማባትና በተሟጋችነት (LOBBY AND ADVOCACY ACTIVITIES) ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል። በዚህም መሰረት፣ በቤተሰብ እቅድ/ምጣኔ፣ በልጆች ጋብቻ እና በአሥራዎቹ ዕድሜ በሚከሰት እርግዝና ላይ ያተኮረ ውይይት፣ ከኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጤና፣ ማህበራዊ ልማት እና ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ሐምሌ 14 ቀን 2022 አካሂዷል። በዚህ ውይይት፣ የኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር ደረጀ ዱጉማ እና ዶ/ር መሰረት ዘላለም በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የእናቶችና ህፃናት ጤና ዳይሬክተር ተገኝተዋል። በእለቱ በተካሄደው ውይይት ተሳታፊ የሆኑ የምክር ቤቱ አባላት፣ ለእረፍት ወደየምርጫ ክልሎቻቸው ሲሄዱ፣ በውይይቱ በተነሱ ጉዳዮች ዙሪያ ከሚወክሉት ህብረተሰብ ጋር በመወያየት የተጠቀሱትን ጭብጦች በተመለከተ የግንዛቤ ሥራ ለማካሄድ ቃል ገብተዋል።

•በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በህግ አውጪነት ተሳትፎ ያላቸው አባላትን ያሳተፈ እና በአፍላ እድሜ ባሉ ልጆችና በወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና፣ በልጆች ጋብቻ፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ በሚከሰት እርግዝና እና ዖታን መሰረት ባደረገ ጥቃት ዙሪያ የተካሄዱ ተግባራት ያሉበትን ሁኔታ የገመገመ ውይይት፣ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መቀመጫ በሆነችው በባህርዳር ከተማ መስከረም 2 ቀን 2022 ዓ.ም. ተካሄደ። በዚህ ውይይት ላይ፣ በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ወርቅሰሙ ማሞ፣ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር

ቤት አፈጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ፋንቱ ተስፋዬ እና የየምክር ቤቶቹ የጤና፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ አባላት እና የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፈዋል።

በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ)፣ በሴቶችና ህፃናት ልማት ድርጅት በኢትዮጵያ (ODWACE) እና በአፍላ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች ማእከል (CENTRE FOR ADOLESCENT GIRLS) ተባባሪነት 200 ሰዎችን ባሳተፈው በዚህ ውይይት፣ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት የማህበራዊ ዘርፍ ኮሚቴ፣ የክልሉ ጤና ቢሮ እና የባህርዳር ዩኒቨርስቲ በዓመቱ በታዳጊ ወጣቶች እና በወጣቶች የስነ ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ያከናወኗቸውን ተግባራት የተመለከቱ ሪፖርቶችን አቅርበው ውይይት ተካሂደባቸዋል። በአለቱ የተካሄደው ውይይት፣ በወጣቶች ዶታዊ እና ስነ-ተዋልዶ ጤና፣ በልጆች ጋብቻ፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ በሚከሰት እርግዝና እና ዶታን መሰረት ባደረገ ጥቃት፣ በሴት ልጅ ግርዛት፣ እና በአፍላነት እና በወጣትነት ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚከሰቱ የወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤና ችግሮችን በመከላለከል ረገድ የተለያዩ አገልግሎቶች ስለሉበት ሁኔታ፣ ተሳታፊዎች ግንዛቤያቸውን የበለጠ እንዲያሰፉና ተጨማሪ መረጃዎችም እንዲኖራቸው ማድረግ የተቻለበት ከመሆኑም በላይ፣ ተሳታፊ የህግ አውጪ አባላት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ከፍ ተብለው የተጠቀሱትን ችግሮች በመቅረፍ ረገድ እያካናወኗቸው ያሏቸውን ተግባራት ይበልጥ አጠናክረው እንዲቀጥሉ መደላድል ፈጥሮላቸዋል።



በአማራ ክልል በአፍላ እድሜ ላይ ባሉ ልጆችና በወጣቶች ዶታዊ እና ስነ-ተዋልዶ ጤና ዙሪያ የህግ አውጪ አካላት የተሳተፉበት የምክክር ሰብሰባ

•በልጆች ጋብቻ፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ክልል በሚከሰት እርግዝና ምክንያት በሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ላይ በሚኖር ጫና ላይ ያተኮረ ሃገር አቀፍ የእርስበእርስ የመማማሪያ መድረክ ቢሾፍቱ ከተማ ተካሂደ። በዚህ ጉባኤ ላይ፣ የወጣት ወንዶች ክርስቲያን ማህበርን፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽንን፣ የባለተሰጥኦ ወጣቶች ማህበርን (TAYA)፣ በኢትዮጵያ የፐላን ኢንተርናሽናል ጽሕፈት ቤትን፣ በኢትዮጵያ የሴቶች እና ህፃናት ልማት ድርጅትን፣ በአፍላ እድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶች ማእከልን (CENTRE FOR ADOLESCENT GIRLS)፣ ኢንጀንደር ሄልዝን የመሳሰሉ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች እና ሌሎች የሚመለከታቸው የትምህርት ሚኒስቴር ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል። መስከረም 21 ቀን 2022 ዓ.ም. በተካሄደው እና 15 (7ቱ ሴቶች ናቸው) ተሳታዎች በታደሙበት የውይይት መድረክ፣ በኢትዮጵያ የሴቶች እና ህፃናት ልማት ድርጅት ውስጥ የምርምር ፕሮግራም አስተባባሪ የሆኑት ዶ/ር ወርቅነህ አበበ እና በአፍላ እድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶች ማእከል ባለሙያ የሆኑት ዶ/ር አስቴር ተሾመ፣ በተጠቀሱት የአለቱ ውይይት ጭብጦች ዙሪያ ያካሄዷቸውን ጥናቶች ለውይይቱ ተሳታፊዎች አቅርበዋል።

ሜክዊይ ፕሮጀክት

ሜክዊይ ፕሮጀክት፣ በፋዌ-ኢትዮጵያ አማካይነት፣ በዋናነት በወሲብ እና በስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ላይ እንቅፋት በሚሆኑና ከዘር፣ ከዶታ፣ ከአካል ጉዳተኝነት፣ ወዘተ. ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ችግሮችን ሁሉን አቀፍ በሆነ የአካታችነት ስልት (INTERSECTIONAL APPROACH) ባካተተ ሁኔታ መቅረፍ ላይ ያተኮረና በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጥምረት የሚተገበር የፋዌ-ኢትዮጵያ አንዱ ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ፣ የአምስት ዓመት ቆይታ ያለው መርሃ ግብር ሲሆን (እ.ኤ.አ. ከ2021 እስከ 2025 የሚቆይ)፣ ወጣቶች በዘራቸው፣ በዶታቸው፣ በአካል ጉዳተኝነታቸው፣ ወዘተ. የተነሳ በወሲብ እና በስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶቻቸው ዙሪያ ለመብታቸው እንዲቆሙ እና ትክክለኛውን መረጃና አገልግሎት እንዲያገኙ ግንዛቤ የመፍጠር ዐብይ ዓላማ አለው። የዚህ ፕሮጀክት የ2022 ዓ.ም. አፈፃፀም፣ እንደሚከተለው በተለያዩ ተግባራት አፈፃፀም ማሳያነት ቀርቧል።

•በፋዌ-ኢትዮጵያ የሚተገበረው የሜክዊይ ፕሮጀክት ማስጀመሪያ ዐውደጥናት፣ የሜክዊይ አጋር ድርጅቶች የሆኑት የቪኤስኦኢ/VSOE የአይፓስ/IPAS እና የኢፌዲሪ ጤና ሚኒስቴር ተወካዮች በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ ተካሂዷል። በማስጀመሪያው ዐውደጥናት ላይ 53 ሰዎች ተሳታፊ ሆነዋል።

•በተመሳሳይ መልኩ፣ በፕሮጀክቱ ዓለማ ላይ ያተኮረ ፕሮጀክቱን የማስጀመሪያ እና የማስተዋወቂያ ዐውደጥናት፣ በፋዌ የአፍሪካ ጽቤት ትብብር 20 ለሚሆኑ ለፕሮጀክቱ አጋርና ባለድርሻ አካላት፣ ለሃይማኖት ተቋማት ተወካዮች፣ ወጣት አመራሮች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ ለፋዌ-ኢትዮጵያ የዋናው ጽ/ቤት ሠራተኞች በተገኙበት ተካሂዷል።





የሜክዊይ ፕሮጀክት ማስጀመሪያ ሥነስርዓት





የሜክዊይ ፕሮጀክት ማስጀመሪያ ዐውደጥናት

•ወጣቶች በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው ሊተገብሯቸው የሚገቧቸውን የተለያዩ የተሳትፎ ስልቶችን መረዳት ላይ ትኩረቱን ያደረገ የአንድ ቀን ሥልጠና ተካሄደ። የተለያዩ መረጃዎችንና ጭብጦችን መሰረት በማድረግ የተካሄደው ይህ ሥልጠና በዋናነት ትኩረቱን ያደረገው ወጣቶችን በተመለከቱ የተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ሲሆን፣ በዋናነትም በወሲብ እና በስነ ተዋልዶ ጤና እና መብቶች፣ በዓለምአቀፍ ደረጃ ለወጣትነት ስለሚሰጠው ፍቺ፣ ውጤታማ ስለሆነ የወጣቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ይህንኑንም ተሳትፎ ማዘለቅ ላይ፣ ለተለያዩ አድሎዎች፣ ትንኮሳዎች ወይም ስሜታዊና አካላዊ ለሆኑ አሉታዊ ጫናዎች ስለማያጋልጡና የደህንነት ስሜት ስለሚፈጥሩ ስፍራዎችና አካባቢዎች ምንነት፣ ዓይነቶችና የጥራት ደረጃ እና መሰል ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነበር። በዚህ ሥልጠና ላይ፣ ከፕሮጀክቱ ተባባሪ አካላት፣ ከሜክዊይ ወጣት የምክር ክበባት፣ ወጣቶችን የሚወክሉ አካላት፣ የሜክዊይ የኢትዮጵያ ማስተባበሪያ ቡድን ተወካዮች፣ የሜክዊይ ጥምረት ተባባሪ የሆኑት የቪኤስኦኢ፣ የፋዌ-ኢትዮጵያና የአይፓስ ሠራተኞች የሆኑ 34 ተሳታፊዎች ተገኝተዋል።





በወጣቶች የተለያዩ የተሳትፎ ስልቶች ላይ የተካሄደ ሥልጠና

•በቤተሰብ ምጣኔ እና ከፅንስ ማስወረድ ጋር ተዛማጅ በሆኑ ጉዳዮች አንፃር ህብረተሰቡ በተለያዩ መነሻዎች እንደትክክል አድርጎ በቆጠራቸው አስተሳሰቦች ላይ የግንዛቤ እና የአመለካከት ለውጦችን VALUE CLARIFICATION AND ATTITUDINAL CHANGE/VCAT፣ በወጣቶች ተሳትፎና በተለያዩ ስልቶች ማሳደግ ላይ ያተኮረ የ2 ቀን ዐውደጥናት ተካሄደ። የኢፌዲሪ የጤና ሚኒስቴር፣ በእነዚህ ጭብጦች ዙሪያ ባዘጋጀውና እንዲሁም ሜክዊይ ከወሲብ እና ከስነ ተዋልዶ ጤና ጋር በተዛመደ በህብረተሰቡ ዘንድ እንደ ትክክል በተቆጠሩ አሳቤዎች አኳያ ባሰናዳው የግልፅነትና የአመለካከት ለውጥ የአሠራር መመሪያ እና ማኑዋል መሰረት በማድረግ በተካሄደው በዚህ ዐውደጥናት ላይ፣ ዋና ዋና የሥልጠናውን ተተኳሪ ጉዳዮች በተመለከተ፣ የአይፓስ ዋና አሰልጣኝ የሆኑት ዶ/ር ያሬድ እና የፋዌ-ኢትዮጵያ ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ ብሌን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡ ፡ በዐውደጥናቱ ላይ ብዛታቸው 34 የሆኑ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትና አጋር ድርጅቶች፣ የወጣት ተወካዮች፣ የሜክዊይ የኢትዮጵያ የአስተባባሪ ቡድኖች እና የፋዌ-ኢትዮጵያ፣ የአይፓስ እና የቪኤስኦኢ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።





በማህበረሰባዊ አሴቶች የግልፅነትና የአመለካከት ለውጥ ላይ ያተኮረ ስልጠና

•የወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤናን በተመለከተ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና ተካሄደ። ለአምስት ቀናት በቆየው በዚህ ሥልጠና፣ ከወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤና ጋር ተዛማጅ በሆኑ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ በወሲብና ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶችና መብቶች፣ አካል ጉዳተኝነትና የወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤና ችግሮችን የተመለከቱ ጉዳዮች የስልጠናው ትኩረት ነበሩ። የሥልጠናው አመቻች ባለሙያዎች፣ እነዚህን ጭብጦች መሰረት በማድረግ ተገቢውን ገለፃ ከመስጠታቸውም በላይ፣ የተለያዩ አሳታፊ የሆኑ የአሰልጣጠን ስልቶችን በመጠቀም፣ ተሳታፊዎች በሥልጠናው ሂደት የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉና በጭብጦቹ ዙሪያም በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አስችለዋል። ሰልጣኞችም፣ በሥልጠናው ሂደት ባገኙት ግንዛቤ መሰረት በጭብጦቹ ዙሪያ የበኩላቸውን የማዳበሪያ አስተያየቶችን ሰጥተዋል።





የወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤና አቅም ማጎልበቻ ሥልጠና

የሲቪል ማህበረሰብ ድጋፍ ፕሮግራም ሁለት (ሲኤስኤስፒ2) የቁንፅል ቀሚስ ተቃዋሚዋ ለሕግ መምሪያ ምክርቤት እንደገና ተመረጡ

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ድጋፍ ፕሮግራም ሁለት (ሲኤስኤስፒ2)፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን አቅም ለመደግፍ በባለብዙ ለጋሾች ፈንድ የሚተገበር ፕሮግራም ነው። የፕሮግራሙ የመጀመሪያ ምዕራፍ (CSSP1, 2011-2017) ከሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ለተውጣጡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ እና የአቅም ማጎልበቻ እድሎችን በማመቻቸት የተተገበረ ነበር። የመጀመሪያው ፕሮግራም፣ በብሪቲሽ ካውንስል (ኢትዮጵያ) በሚመራው ጥምረት ማለትም፣ በአይሪሽ ኤይድ፣ በዩኬኤድ፣ በካናዳ፣ በደች፣ በዴንማርክ እና ኖርዌይ ኤምኤፍኤ እና SIDAን ጨምሮ በሰባት አለም አቀፍ ለጋሾች ድጋፍ ሲካሄድ የቆየ ነበር።

ሁለተኛው የሲቪል ማህበረሰብ ድጋፍ ፕሮግራም፣ እንደመጀመሪያው ሁሉ በተለያዩ የሃገራችን ክልሎች የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን አቅም ለመደግፍ በባለብዙ ለጋሾች ፈንድ፣ ማለትም በዩናይትድ ኪንግደም፣ በአየርላንድ፣ በስዊዲን እና በኖርዌይ መንግስታት፣ እ.ኤ.አ. ከ2018 ጀምሮ በብሪቲሽ ካውንስል (ኢትዮጵያ) በኩል እየተተገበረ ያለ ፕሮግራም ነው። ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ እንደሲቪል ማህበረሰብ ድርጅትነቱ፣ የዚህ ፕሮግራም አካል በመሆን በፕሮግራሙ ግብ መሰረት በተጠናቀቀው 2022 ዓ.ም. ከነሐሴ እስከ ህዳር ባሉ ወራት የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል። የእነዚህ ተግባራት አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል።

•በስርዓተ ፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን ለመከላከል የሚካሄደው የ16 ቀናት ዓለም አቀፍ ዘመቻን የተመለከቱ የፓናል ውይይቶችን ጨምሮ የተለያዩ ተግባራት፣ የተለያዩ የማህበረሰብ እና አጋር አካላትን ባሳተፈ ሁኔታ ደብረብርሃን ከተማ ተካሂደዋል።

•ከመስከረም 2022 ዓ.ም. ጀምሮ "ብቁ ሴት" የሚል የሬዲዮ ፕሮግራም፣ በደብረ ብርሃን ፋና ኤፍ ኤም 94.0 ላይ ዘውተር ሐሙስ ሐሙስ ለግማሽ ሰዓት እየተላለፈ ይገኛል። ፕሮግራሙ፣ የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ማሳደግ ላይ በዋናነት ያተኮረ ሲሆን፣ ከታሰበው በላይ በርካታ ሴቶችን እያሳተፈ የሚገኝ የሬዲዮ ፕሮግራም ነው።

•አጋርነት መፍጠር ላይ፣ ውጤታማ የተልእኮ አውታሮችን መገንባት ላይ፣ ከአዳዲስ እውነታዎች ጋር ራስን ማስማማት ላይ እና የተለያዩ ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና፣ ህዳር 21 ቀን 2022 ዓ.ም. ተካሂዷል። በዚህ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና፣ በሴቶች መብቶች ዙሪያ እንቅስቀሴ የሚያደርጉ ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና በአካል ጉዳተኝነት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ማህበራትን የወከሉ፣ ባጠቃላይም 20 ያህል ሴቶች ተሳትፈዋል።

•በሴቶች መብቶች ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች፣ በተለያዩ ሴቶችን በሚመለከቱ ጥያቄዎች እና የተለያዩ አጀንዳዎች ዙሪያ በ2013 ኢትዮጵያ ውስጥ በተካሄደው ሃገራዊ ምርጫ በየሚገኙባቸው የምርጫ ክልሎች አሸናፊ ከሆኑ ሴት ተመራጮች ጋር ውይይት የሚያደርጉባቸው መድረኮች በፕሮጀክቱ አማካይነት ህዳር 20 ቀን 2022 ዓ.ም. እንዲመቻቹላቸው ተደርገዋል።

•ማህበረሰብ አቀፍ የሀሳብ መለዋወጫ የውይይት መድረኮች፣ በደብረብርሃን አራት ክፍለ ከተሞች ውስጥ በሚገኙ አምስት ቀበሌዎች ውስጥ ከነሐሴ እስከ ህዳር ባሉት ጊዜያት ተካሂደዋል። ነሐሴ 5 ቀን 2022 ዓ.ም. በተጀመረውና በየቀበሌው በሁለት ሁለት ቡድኖች በተደራጁ ሴት የማህበረሰብ ክፍሎች በየወሩ በየቡድኖቹ በተካሄዱ ሁለት ሁለት የማህበረሰብ ውይይቶች፣ ባጠቃላይ 500 ሴቶች ተሳታፊ መሆን ችለዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ከፍ ተብለው ከተጠቀሱ ቀበሌዎች የተውጣጡ 250 ሴቶች ተሳታፊ የሆኑባቸው ማህበረሰብ አቀፍ የሀሳብ መለዋወጫ የውይይት መድረኮች፣ መስከረም 7 ቀን 2022 ዓ.ም. ተካሂደዋል።

የቁንፅል ቀሚስ ተቃዋሚዋ ለሕግ መምሪያ ምክርቤት እንደገና ተመረጡ

ከዘመኑ ወጣቶች እንደሌሎች አውሮፓውያን እህቶቻችን አጭር ቀሚስ እንለብሳለን ብለው ባጭር ታጥቀው የተነሱ አሉ። እነዚህ ሴቶች ሚኒስከርት ወይም ቁምጣ ቀሚስ በመልበሳቸው ብዙ ያልተደሰቱበት ሰዎች አሉ። ከጥቂት ወራት በፊት ወይዘሪት አሥመራ ሚኒስከርት ለብሳ ድሬዳዋን ስትጎበኝ የከተማው ፖሊሶች በአለባበሷ ስለአልተደሰቱ፣ ለግማሽ ሰዓት ያህል ፖሊስ ጣቢያ አቆይተዋት ነበር። ከሚኒስከርት ተቃዋሚ ከሆኑት አንዷ፣ የተከበሩ ወይዘሮ ራቢያ አብድርቃድር ናቸው። አሳቸው እንዲህ እንደሌሎቹ በቃል መቃወም ብቻ ሳይሆን፣ ሚኒስከርት መልበስ በሕግ እንዲከለከል በማለት ለሕግ መምሪያ ምክርቤት አቅርበዋል። የሕግ መምሪያ ምክርቤቱም ሃሳባቸውን በአንድ ቃል ደግፎ በማፅደቅ ወደሕግ ኮሚቴ አስተላልፎታል።

የሃያ ዘጠኝ ዓመት ወይዘሮ የሆኑት የተከበሩ ወይዘሮ ራቢያ አብድር ቃድር፣ በ1957 ዓ.ም. በሊሙ (ከፋ) አውራጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕግ መምሪያ ምክር ቤት ተወዳድረው

በ3260 የምርጫ ድምፅ ሁለተኛነትን አግኝተው ተመረጡ። ከፍ ባለ የድምፅ ብልጫ ለመመረጥ ይችሉ ነበር። ነገር ግን፣ ጥቂት ሰዎች ተወዳዳሪያቸውን ለመርዳት እኔን ለአንድ ሰውዬ "'አንተም ጠጣ፣ ለመራጩም ህዝብ አጠጣ ብለ ገንዘብ ሰጥታለች' ብለው በሃሰት ስላስከሰሱኝ ሳጥኔ ለጥቂት ቀኖች ተነስቶ እኔም ለአንድ ቀን ያህል ታሰሬ ነበር።" በማለት የመራጮቻቸውን ቁጥር ማነስ አስረዱ። ይህ የሆነው በሶስተኛው ምርጫ ዘመን ነበር።

አሁን በአራተኛ የምርጫ ዘመን ለሁለተኛ ጊዜ ሲመረጡ፣ 7214 ድምፅ አግኝተው አሸናፊ የሆኑት እንዲሁ በቀላሉ አይደለም። ሰባት ወንዶች ተወዳዳሪዎቻቸውን በማሸነፍ ነው። በእኛ አስተያየት ሰባቱ ወንዶች የተሸነፉበት ዋናው ምክንያት፣ ሚኒስከርት የሚለብሱትን ሴቶች አንቃወምም በማለታቸው ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም የተከበሩ ወይዘሮ ራቢያ፣ "ከመጣሁበት አውራጃ ሴቶች እንዲያውም በጣም ረጅም ቀሚስ ነው የሚለብሱት። ቁምጣ ቀሚስ አዲስ አበባ መግባቱንና እኔም መቃወሜን ስነግራቸው፣ እንኳን የኔን ሀሳብ ሊቃወሙ ይቅርና እንዲያውም መርቀውኛል። አዲስ አበባም ቢሆን ብዙ ሰው በሃሳቤ ተደስቷል። " ብለው በደስታ ገልፀዋል።

"ሚኒስከርትን የሚቃወሙት ለምንድን ነው?"

"እኔ በበኩሌ ቋንጃ ሲታይ ደስ አይለኝም።"

"የወንድም ቢሆን?" ወንዶችም ቁምጣ ሁልጊዜ የሚለብሱበት ዘመን የመጣ እንደሆነ በማለት።

"የወንድም ቢሆን። እንዲያውም የወንዶች ቋንጃ ይበልጥ ያስጠላ ይሆናል።"

"እርስዎ ቋንጃ ሲያዩ መጥለትዎ ብቻ ሊሆን አይችልም ሚኒስከርት እንዲጠፋ እንዲህ የሚታገሉት? ከዚህ የተሻሉ ምክንያቶች መኖር አለባቸው።"

"አዎን!" አሉ። "መጀመሪያ ቀደም ብዬ ልነግራችሁ እንደሞከርኩት ኢትዮጵያውን ሴቶች በተፈጥሮም ሆነ በአስተዳደግ ቅብጠት የማይሆንላቸው ከመሆኑም ሌላ ሚኒስከርት በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ ያልተወደደ፣ በአባቶችና በእናቶች የተወገዘ ነው።

"ማንኛዋም ወይዘሮ ወይም ወይዘሪት ከጉልበትዋ በላይ የምትለብሰው ሁሉ ለጌጥ ሳይሆን፣ ለቅብጠት ነው ብዬ አምናለሁ።"

"ሚኒስከርት የምትለብሰው ልጃገረድ ቀበጥ ነች ብለን ብንቀበልዎ፣ የርሷ ቅብጠት በጠቅላላ በህብረተሰቡ ላይ ምን ዓይነት ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል?" ብለን ጠየቅናቸው። የተከበሩ ወይዘሮ ራቢያ ሲመልሱ፣ "ራቁታቸውን ሲኒማ እያሳዩ መሄድ ነውር መስሎ አይታያችሁም? ሚኒስከርት የሚያስከትለው ራቁት መሄድ ይመስለኛል። ይህም ሲሆን ትዳር ይጠፋል ማለት ነው። ወንዱ የሌሎቹን እግር በየመንገዱ እያየ ቤቱም አይገባም። ይህም የሚያስከትለው መፋታትን ነው።"

"ትዳር የሚፈልግ ወንድ ሚስቴ ራቁቷን ትሂድ የሚል ያለ አይመስለኝም።" በማለት ማብራሪያቸውን የቀጠሉት የተከበሩ ወይዘሮ ራቢያ፣ "አጭር ቀሚስ የምትለብሰው ሴት ባለጌ ነች ብዬ ነው የማስበው። ረጅም ቀሚስ የምትለብሰው ግን ማንም ባለጌ ነች ብሎ ቢነግረኝ በፍፁም መስለ አትታየኝም።" ብለዋል።

"ሚኒስከርት መልበስ የሚያስደስታቸውና የሚፈልጉ ወይዛዝርት እርስዎ ልብሱን የሚቃወም ሕግ ለማውጣት ሲጣጠሩ የግል መብታችንን ነኩብን ብለው የሚቃወሙዎት አይመስልዎትም?" በማለት ለተጠየቁት ጥያቄ በሰጡት መልስም፣

"ይሉ ይሆናል። ግን እኔ የሴቶች መብት ብዬ የምቆጥረው ሚኒስከርት መልበስን አይደለም። የሴቶች መብት ማንኛውንም ሥራ ከወንዶች እኩል ተወዳድረው እንዲያገኙ፣ በደመወዛቸውም ቢሆን ከወንዶች አንዳያንሱ፣ ሹመትም እንዲሁ።"

"ሚኒስከርት ቢከለከል የሴቶች መብት የሚቀነስ አይመስለኝም። ከዚህም በላይ ሚኒስከርት ኢትዮጵያ ውስጥ ቢከለከል፣ ኢትዮጵያ ይህን አርምጃ ለመውሰድ የመጀመሪያዋ አትሆንም። በአፍሪካና በአንዳንድ የእስያ አገሮችም አለባበሱ እንዳይስፋፋ ህጋዊ እርምጃ የወሰዱ አሉ። በእኛም አገር ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ቢቀር ጥሩ ይመስለኛል።"

ባለፈው የአራተኛው የፓርላማ ምርጫ አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ ሴቶች ተወዳዳሪ ሆነው ነበር። የማሸነፍ እድል ግን ሁሉንም ሸሽቷቸዋል። በጠቅላላው፣ ለአራተኛው ምርጫ ከተከበሩ ወይዘሮ ራቢያ ጋር አራት ሴቶች ተመርጠዋል። ሁሉም የመመረጥ እድል ያገኙት ከአዲስ አበባ ውጭ ነው።

ሚኒስከርት ከሌሎች ከተማዎች ይበልጥ የሚታየው አዲስ አበባ ውስጥ በመሆኑ፣ መራጮቹ ሴቶቹን ባለመደገፋቸው ሚኒስከርት አንዳይከለከል የማለት ስሜታቸውን መግለፃቸው ይሆን?

የተከበሩ ወይዘሮ ራቢያን ስለዚህ ጉዳይ ሃሳባቸውን እንዲገልፁን ብንጠይቃቸው፣ "ለምን እንዳልተመረጡ እነሱን ጠይቋቸው። እኔ እንዴት አውቃለሁ? ስለእኔ ጠይቁኝ በደስታ እግልፅላችኋለሁ።" ሲሉ መልሳቸውን ዘጉ።

ምንጭ፡- መነን መጽሄት ነሐሴ 21 ቀን 1961 ዓ.ም.

ከዚህም ከዚያም ፩

• የሴቶች ቀሚስ የት ይደርስ ይሆን!

አንድ ህፃን ልጅ ከእናቱ ጋር ፒያሳ ወጣና በሰው መሃል እናቱ በድንገት ጠፋችበት። ጥግ ቆሞ እንባውን ሲያነባ ፖሊስ ደረሰና "ምን ሆነህ ነው የምታለቅሰው?" ብሎ ጠየቀው። "እናቴ ጠፍታብኝ" ነው አለውና እንዴት ከእናቱ ጋር እንደተጠፋፉ ሳይፈራ ነገረው። ፖሊሱ ተገረመና "እሷ እጅህን ባትይዝህ አንተ ቀሚሷን ይዘህ አትከተልም ኖሯል?" ሲለው፣ ልጁ ቀና አለና "የእናቴን ቀሚስ ተንጠራርቼ አልደርስበትም።" ብሎ ችግሩን አጫወተው።

መነን መጽሄት፣ 13ኛ ዓመት ቁጥር 8 ሚያዚያ 1961

• ስለሴቶች የተባሉ አወንታዊ ምሳሌያዊ ንግግሮች

የታደለች ሴት፣ በፊት ትወልዳለች ሴት
ሴት የሌለበት፣ ወንድ አይበቅልበት
ያዋቂ ሴት ቤት፣ አለው ውበት
የሴት ምክር፣ የሾህ አጥር
እንጀራ ይጋግረል እማድቤት፣ መለ ያማክረል ለሴት
ጠመንጃ ያለጥይት ዱላ፣ ወንድ ያለሴት ቀውላላ
ያለሴት ቤት፣ ያለበሬ መሬት
እንጀራ ያለወጥ፣ ቤት ያለሴት፣ ከብት ያለበረት

• "አሁን ታዲያ የአዲስ አበባን ጉዳይ አሰብ ሳደርገው እዚህ መድረሷ ደስ ያሰኝኛል። ከጣሊያን በፊት እንዲህ ሆነ። አንድ ግርማ የሚባል አረቄ የሚሸጥ ነበር። ያን ጊዜ ቴፕ የለም፤ በእጅ እየተሞላ የሚሠራ ዲስክ ነው ያለው። የዚያን ጊዜ ዘፋኝ በዘፈናቸው ውስጥ የሚወዱትን ሰው ስም ጠቅሰው የሚያወድሱበት ሁኔታም ነበርና ያ ዲስክ ሲጫወት ከጠጪዎች ውስጥ አንደኛው የሚወደው ሰው በዘፈን ውስጥ ሲወሳ ይሰማል። አምስት ብሩን አውጥቶ ከዲስኩ ላይ ቁጭ አደረገው። አዝማሪ እንደሚሸለመው፣ እሱም ዲስኩን መሸለሙ እኮ ነው።

ሌላው የሚስጥር ዘበኞች ነገር ነው። አቆባቸው ላይ የምስጢር ዘበኞች የሚል ጽሁፍ አለው። እነሱን ሰው ሲያይ 'መጡ ዘወር በሉ' ይባል ነበር። አንዲያው የዚያን ጊዜውን የዋህነት ሳስበው ይደንቀኛል፤ ከመለዮ ላይ ማንነታቸውን እየጻፉ 'የምስጢር ዘበኞች' ብሎ ነገር!"

ምንጭ፡- ከበካር አርቲስቶች አንዱ የነበሩት በሻህ ተ/ማርያም 1979 ዓ.ም. እንደገለፁት፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲ መጽሄት የካቲት 1985 ዓ.ም.

• የሰው ልጅ አካል ሲፈጠር፣ ሁሉም የሰውነት ክፍሎች አለቃ ለመሆን ይፎካከሩ ጀመር። አእምሮ፣ "የአካላችንን አጠቃላይ ስለምቆጣጠር አለቃ መሆን ያለብኝ እኔ ነኝ" አለ። አግርም በበኩሉ፣ "አእምሮንም ሆነ ሌላውን የሰውነት ክፍል ወደተፈለገው ቦታ የማደርሰው እኔ ስለሆንኩ፣ አለቃ እኔ ነኝ" ሲል፣ እጅም፣ "ሁሉንም ሥራ በመሥራት ገንዘብ የምናስገኘው እኛ ስለሆንን፣ አለቃ መሆን ያለብን እኛ ነን" አለ። ... ሁሉም የሰውነት ክፍሎች በየተራ አለቃ የመሆኛ ምክንያታቸውን አቀረቡ። በመጨረሻም፣ መቀመጫ የሁሉም አለቃ መሆን እንደሚገባው ሲናገር፣ የሰውነት ክፍሎች በሙሉ ሳቁበት። በዚህ ሁኔታ የተናደደው መቀመጫ፣ ራሱን በመዝጋት የሥራ ማቆም አድማ አደረገ። በደቂቃ ውስጥ አይኖች ፈጠጡ፤ እጆች ዛሉ፤ እግሮች ተንቀጠቀጡ፤ የልብ ምት ተዛባ፤ አእምሮ በጭንቀት ተናጠ። ወዲያው፣ መቀመጫ አለቃቸው እንዲሆን በሙሉ ድምጽ ተስማሙ። መቀመጫ ሥራውን ጀምሮ የሰውነት አካላት እንቅስቃሴ ቀጠለ። አለቃው ቁጭ ብሎ እየተፀዳዳ፣ ሌላው ሁሉ ቀን ከሌት መሥራቱን ቀጠለ።

ምንጭ፡- ማዕደ ኪን መጽሄት፣ ሚያዚያ 2000 ዓ.ም.

• "አባቴ ሙሴ ሰርኪስ ተርዝያን ከምኒልክ ጋር በመመካከር ወደ እንግሊዝ አገር ሄዱና በ1987 የሰርኪስን ባቡር በመርከብ ይዘው በጆቡቲ በኩል አድርገው ወደ አዲስ አባበ ተነሱ። ባቡሩ እየተነዳ፣ አንዳንዴም እየተገፋና እየተጎተተ ደወሌ ሲደርስ፣ ለራስ መኮንን ተነገረ። ራስም ይህን እንደሰሙ ወዲውኑ አገረገኘዎቹ ሁሉ በየበኩላቸው የሚረዳ የሰው ሃይል እንዲያስተባብሩ አዘዙ። እጅግ በጣም ብዙ ህዝብ ቀረበ። ከዚያም ባቡሩ እየተነዳ፣ እየተገፋና እየተጎተተ ቢሾፍቱ ደረሰ። ባቡሩ ሳይታሰብ አንድ ማጥ ውስጥ ተዘፈቀ። አሁን ከዚህ ማጥ ማን ጎትቶ ያውጣው! አስቸገረ። በዚህን ጊዜ ነበር ይህን ያ አዝማሪ፡-

'ቢነግሩሽ ቢነግሩሽ አታጠናቅሪ
እንደሰርኪስ ባቡር ተገትረሽ ቅሪ'
ብሎ የገጠመው።"

ምንጭ፡- የካቲት መጽሄት መስከረም-ጥቅምት/1979 ዓ.ም.

የትማር እንግዳ፣ወ/ሮ አልማዝ ገ/ዮሃንስ

የዚህ ዓመት የመጽሄታችን እንግዳ ከሆኑት መካከል አንዷ ወ/ሮ አልማዝ ገ/ዮሃንስ ናቸው። ወ/ሮ አልማዝ፣ በትምህርቱ ዓለም በመምህርነትና ከትምህርት ጋር ተዛማጅ በሆኑ የተለያዩ ሙያዎች በአማራ ክልል በሚገኙ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች በጡረታ እስከተገለሉበት ጊዜ ድረስ ክልላቸውንና ሃገራቸውን አገልግለዋል። ወ/ሮ አልማዝ፣ ከዋናው ሙያቸው በተጨማሪ፣ ፋዌ-ኢትዮጵያ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ የፋዌ-ኢትዮጵያን ዓላማዎች ዳር ለማድረስ የበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል። በተለይም፣ የፋዌ-ኢትዮጵያ የአማራ ክልል ንዑስ ቅርንጫፍ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ፣ ንዑስ ቅርንጫፉን በአስተባባሪነት በመምራትና በተለያዩ ሃላፊነቶች በመሳተፍ፣ ፋዌ-ኢትዮጵያ በክልሉ በተለያዩ ዓመታት የተገበራቸው ፕሮጀክቶች ግባቸውን እንዲመቱ የበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል። በትምህርቱ ዓለም ሰፊ ተሳትፎ ካላቸው ከእኚህ ባለሙያ ጋር ያደረግነው ቆይታ እንደሚከተለው ቀርቧል።



ትማር፡- ራስዎን ለአንባቢዎቻችን ቢያስተዋውቁ?

ወ/ሮ አልማዝ፡- ወ/ሮ አልማዝ ገ/ዮሃንስ እባላለሁ። የተወለድኩት 1944 ዓ.ም ነው። የትውልድ ሥፍራዬ ሰሜን ሸዋ ሲሆን፣ ያደግሁት አዲስ አበባ ቀበና አካባቢ ነው። የትምህርት ደረጃዬን በተመለከተ፣ በላይብረሪ ሳይንስ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ ዲፕሎማ አግኝቻለሁ። ትዳር መስርቼ የ6 ልጆች እናት ነኝ። አባቴ የፖሊስ ሻለቃ ስለነበር፣ የደብረማርቆስ ፖሊስ ም/አዛዥ ሆኖ ወደ ደብረማርቆስ ተቀይሮ ከእነቤተሰቡ ሲሄድ፣ በዚያን ወቅት የ2 ዓመት ልጅ ነበርኩ። ሰባት ዓመት ሲሞላኝ፣ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ትምህርት ቤት ገብቼ ከ1ኛ-8ኛ ክፍል ከተማርኩ በኋላ፣ አባቴ እንደገና ወደ ወለጋ ተዛውሮ የነቀምት ፖሊስ አዛዥ ሆኖ በመቀየሩ፣ እኔም ከቤተሰቦቼ ጋር አብሬ ስለሄድኩ፣ ከ9ኛ-11ኛ ያሉትን የክፍል ደረጃዎች ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተብሎ በሚጠራው ትምህርት ቤት ተምሬአለሁ። ከዚያም፣ 1963 ዓ.ም. ሐረር መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ገብቼ የሁለት ዓመት የመምህርነት ኮርስ ተከታትዬ ማጠናቀቅ በመቻሌ፣ ሲዳሞ ክፍለሃገር አለታ ወንዶ በሚገኘው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት ለ5 ዓመታት በመምህርነት አገልግያለሁ። በመቀጠልም፣ 1970 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ወደባህርዳር በቅያሪ በመምጣቴ፣ ለአንድ ዓመት ሽምብጥ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ካስተማርኩ በኋላ፣ ከ1971-1989 ድረስ የጣና ሃይቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የቤተመጻህፍት ሃላፊ በመሆን አገልግያለሁ። ሆኖም፣

ወደማስተማር ሙያዬ መመለስ እፈልጋለሁ ብዬ ባቀረብኩት ጥያቄ መሰረት፣ ጡረታ እስከወጣሁበት እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ ሠርፀ ድንግል አንደኛ እና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመምህርነት ሙያዬ ማገልገል ችያለሁ።

ትማር፡- ለበርካታ ዓመታት በትምህርቱ ዓለም እንደማሳለፍዎ፣ ያጋጠሙዎትን ውጣውረዶች ወጣት ሴቶችን ታሳቢ በማድረግ ቢያካፍሉን?

ወ/ሮ አልማዝ፡- ባሳለፍኳቸው ጊዜያት ያጋጠሙኝ ችግሮች በርካታ ቢሆኑም፣ ሴት ተማሪዎች እነሱ ሳይፈልጉ በወለጆቻቸው ፍላጎት ብቻ ሊድሯቸው ሲሉ፣ እኔ ጋር መጥተው በሚያለቅሱበት ወቅት፣ ከቤተሰቦቻቸው/ወላጆቻቸው ጋር በመወያየት የጋብቻቸው ሁኔታ እንዲቀር አደርግ የነበረው ጥረት ሳይሳካ በሚቀርበት ጊዜ ይሰማኝ የነበረው የሃዘን ስሜት እስካሁን ድረስ ከእኔ ጋር አለ። ከዚሁ ጋር በማያያዝ የማነሳው ሌላው ችግር፣ በጣም ጎበዝ የሆኑ ሴት ተማሪዎች በአቻ ግፊት የተነሳ ወዳልሆነ የኑሮ ህይወት ውስጥ ሲገቡ ሳይ እነሱን ለመመለስ የማደርገው ትግል ሴኬታማ ሆኖ ሳይ ቢያስደስተኝም፣ ሳይሳካ በሚቀርበት ወቅት ግን ሃዘን ውስጥ ይከተኝ ነበር።

ት ማ ር ፡ - በ ፋ ዌ - ኢ ት ዮ ጵ ያ ፣ በአባልነትም፣ በአመራርነትም ለበርካታ ዓመታት (በተለይ በንዑስ ቻፕተር ደረጃ) በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ። የቻፕተሩ አባል ለመሆን ምን አነሳሳዎት? አባል የሆኑበት አጋጣሚስ ምን ነበር?

ወ/ሮ አልማዝ፡- ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ በአማራ ክልል ንዑስ ቻፕተሩን ከመሠረተበት ጊዜ አንስቶ እየተሳተፍኩ እገኛለሁ። ምክንያቱም፣ ከልጅነቴ ጊዜ አንስቶ በበጎ አድራጎት ተግባራት የተለያዩ ተግባራት ላይ እሳተፍ ስለነበር፣ በቻፕተሩ መሳተፌን ያንን በጎ ልማዴን የበለጠ እንዳጠናክር፣ እንዳጎለብት ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሮልኛል፣ በውስጤ ያለውን ፍላጎት ይበልጥ እንዳጎለብት አድል ሰጥቶኛል፤ ፍላጎቴን የበለጠ አጠናክሮልኛል፤ አመቺ ሁኔታም ፈጥሮልኛል። ስለሆነም፣ በንዑስ ቻፕተሩ ውስጥ በአባልነት መንቀሳቀስ ከጀመርኩ ጊዜ አንስቶ፣ በችግር ምክንያት ሴት ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ባለኝ አቅም በተለያየ መልኩ ከመርዳት አንስቶ፣ ሌሎችንም በማስተባበር የገንዘብም ሆነ የትምህርትና የሌሎች ቁሶች እርዳታ ለእነዚህ ሴቶች እንዲደርሱ በተቻለኝ አቅም ተንቀሳቅሻለሁ።

ትማር፡- ፋዌ-ኢትዮጵያ ከምስረታው ጊዜ አንስቶ ስለከናወናቸው ተግባራት የቅርብ ምስክር እንደመሆንዎ፣ ስለስኬታማነቱ ቢገልፁን? በዚህ የስኬታማነት ጉዞው እንዲቀጥልስ ምን መደረግ አለበት ብለው ይመክራሉ?

ወ/ሮ አልማዝ፡- የፋዌ-ኢትዮጵያ የክልላችን ንዑስ ቻፕተር፣ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን አከናውኗል። ለምሳሌ፣ ሴት ተማሪዎች ከየትምህርትቤቱ የላቀ ውጤት ያመጡትን በመሸለም፣ ለሌሎች ሴት ተማሪዎች አርአያ እንዲሆኑ ከማድረግ ባሻገር፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ሆነው በትምርታቸው ግን ጎበዝ የሆኑ ወንድ እና ሴት ተማሪዎችን ከ8ኛ ክፍል የማጠናቀቂያ ፈተና ውጤት በኋላ በመመልመል፣ ከ9-12ኛ ድረስ ያሉትን የክፍል ደረጃዎች በባህርዳር አካዳሚና በጣና ሃይቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሙሉ ወጪያቸው ተሸፍኖላቸው እንዲማሩና ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት እንዲበቁ ማድረግ ተችሏል። በዚህ ተግባሩም፣ በባህርዳር ከተማ በሚገኙ ማህበረሰቦች ዘንድ ከፍተኛ እውቅና ሊያገኝ ችሏል።

ትማር፡- በሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ረገድ፣ በሁለንተናዊ መልኩ አሁንም እየተስተዋሉ ያሉ ተግዳሮቶችን በዘላቂነት ለመቅረፍ ያስችላሉ የሚሏቸውን ቁልፍ ጉዳዮች/ተግባራት ቢጠቁሙን?

ወ/ሮ አልማዝ፡- የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ በማሳደግ ረገድ፣ በዘላቂነት ቢቀረፉ ብዬ በራሴ በኩል ከማምንባቸው ጉዳዮች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው። እንደሚታወቀው፣ በዛ ባሉ ወላጆች ዘንድ፣ በተለይም ገጠር አካባቢ፣ የተለያዩ የቤት ውስጥም ሆኑ ሌሎች ሥራዎችን ወንድ ሴት ሳይሉ በእኩል ደረጃ በማሠራት በኩል የምናስተዋለው ክፍተት አለ። ይህም ሁኔታ፣ በሴት ተማሪዎቻችን ላይ የሥራ ጫናን የሚፈጥር እና ለትምህርታቸውም ተገቢውን ትኩረት እንዳይሰጡ ስለሚያደርግ፣ በትምህርት ውጤታቸው ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ማድረጉ ግልፅ ነው። ስለሆነም፣ ወላጆች የቤት ውስጥ ሥራዎችንም ሆነ ሌሎች ሥራዎችን ለልጆቻቸው በሚሰጡበት ወቅት፣ በልጆቻቸው መካከል ልዩነት በማይፈጠርበት ሁኔታ እንዲሆን ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ለዚህም፣ በተገኙ አጋጣሚዎች ሁሉ ተከታታይነት ያለው ትምህርት መስጠት እጅግ ጠቃሚ ይሆናል እላለሁ።

እንደሚታወቀው፣ አንዳንድ ወላጆች ሴት ልጆቻቸው በትምህርታቸው በሚወድቁበት ጊዜ፣ "እንዴትና ለምን ወደቅሽ? ምን ችግርስ አጋጥሞሽ ነበር?" የሚሉትን ጥያቄዎች የሚያቀርቡት፣ ልጆቻቸውን በከፍተኛ አሉታዊ ጫና ውስጥ በማስገባት ነው። ይህም አቀራረብ፣ ልጆች ተስፋ እንዲቆርጡና ያለፍላጎታቸው ትዳር (አስፈላጊ ወዳልሆኑ ሌሎች ሁኔታዎችም ጭምር) ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል። በመሆኑም፣ ይህን ለማስቀረት፣ ወላጆች ራሳቸው፣ ማህበረሰቡና የትምህርት ማህበረሰቡም ጭምር የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችን/ዘዴዎችን በመቀየስ ለዚህ አሉታዊ ጫና መቀረፍ የበኩላቸውን ጥረት ማድርግ ይጠበቅባቸዋል።

ትማር፡- በግል ስኬታማ ጉዞዬ ህይወት ለዋጭ ክስተት (TURNING POINT) ነበር የሚሉት አጋጣሚ (ግለሰብን ጨምሮ) ምን ነበር? አብራርተው ቢገልፁልን።

ወ/ሮ አልማዝ፡- በ11 ዓመታቸው ገጠር አካባቢ ያሉ ሁለት ሴት ልጆች ሊዳሩ መሆኑ ጥቆማ ሲደርሰኝ፣ በተለያየ ጊዜ እነዚህን ልጆች እኔ ወዳለሁበት ከተማ በማምጣት በተለያየ መልኩ አገዛ ለማድረግ የበኩሌን ጥረት አድርጌአለሁ። በመሆኑም፣ አንዷን ሴት ልጅ ከተማ ከሚኖር ወንድሟ ጋር በማገናኘት፣ ትምህርቷን እንድትቀጥል በማድረጌ፣ ልጅቷ አሁን የ3ኛ ዓመት ትምህርቷን በመከታተል ላይ ትገኛለች። አንዷን ደግሞ፣ እራሴ ቤት በማስቀመጥ፣ ከ4ኛ-10ኛ ድረስ እንድትማር አድርጌአለሁ። ሆኖም፣ ይህቺ ልጅ በ10ኛ ክፍል የአጠቃላይ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና ተፈላጊውንና መሰናዶ ትምህርቷን ሊያስቀጥላት የሚችለውን ውጤት ማምጣት ባለመቻሏ፣ የሙያ ትምህርት ስልጠና እንድትወስድ አድርጌ፣ ዛሬ በአንድ ትልቅ ሆቴል ውስጥ በወሰደችው ስልጠና መሰረት በሥራው ዓለም ተሠማርታ ትገኛለች፤ ራሷን ችላ ኑሮዋንም በመምራት ላይ ትገኛለች።

ት ማ ር ፡ - ፋ ዌ - ኢ ት ዮ ጵ ያ ፣ የተቋቋመበትን ዓላማ መሰረት በማድረግ እያበረከተ ያለውን ሀገራዊ አስተዋፅኦ እንዴት ይገልፁታል? ለወደፊትስ ይህ አስተዋፅኦው እንዴት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለው ይመክራሉ?

ወ/ሮ አልማዝ፡- ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ ፍሬያማ ሥራዎችን አከናውኗል ብዬ መመስከር እችላለሁ። ምክንያቱም፣ ለበርካታ ዓመታትም አብሬው ስለተጓዝኩም ያከናወናቸውን ተግባራት በዝርዝር አውቀዋቸዋለሁ ባይ ነኝ፤ ተጨባጭነት ባላቸው ማስረጃዎችም ሊረጋገጡ የሚችሉ ውጤታማ ተግባራቱንም መግለፅ እችላለሁ ባይ ነኝ። ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ በተለያዩ የሃገራችን ክፍሎች በርካታ ተግባራትን በማከናወን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎችን (በተለይም ሴት ተማሪዎችን) ለውጤት አብቅቷል። በክልላችንም፣ በአሁኑ ወቅት በፋዌ ድጋፍ ትምህርታቸውን ባማባቡ ያለምንም ችግር እየተማሩ ያሉ 200 ተማሪዎች ለዚህ ውጤታማ ሥራው ህያው ምስክር ናቸው። ይህ ማለት ግን፣ ሥራው የተሟላ ነው፣ በቂ ነው ማለቴ አይደለም። አቅሙን በማጎልበት፣ ከአሰካሁኑ የበለጡና በተለያዩ ፕሮግራሞች የታገዙ ተግባራትን አየቀረፀ ለውጤት የሚያደርገውን ጉዞ አጠናክሮ መቀጠል አለበት የሚለውን ማሳሰቢያ/ምክር በዚህ አጋጣሚ ልሰጥ እወዳለሁ።

ትማር፡- በአሰካሁኑ የህይወት ተሞክሮዎ ባደረኩት ብለው የሚቆጩበት ጉዳይ አለ? ካለ እንደህይወት ተሞክሮ ይጠቅማልና ቢጠቅሱልን?

ወ/ሮ አልማዝ፡- ከበፊት ጀምሮ፣ ቀደም ብዬ እንደጠቆምኩት፣ ያቋረጥኩትን ትምህርቴን በመቀጠል የትምህርት ደረጃዬን ወደከፍተኛ ደረጃ ማድረስ በጣም እፈልግ፤እመኝ ነበር። ነገር ግን፣ ይህ ፍላጎቴና ምኞቴ በተለያዩ ቤተሰባዊ ጉዳዮች የተነሳ ዳር ሊደርስልኝ አልቻለም። በጣም የሚቆጨኝ ይህ ነው።

ትማር፡- የትርፍ ጊዜዎን በምን ያሳልፋሉ?

ወ/ሮአልማዝ፡- በአሁኑሰዓት፣ ትርፍ ጊዜዬን ለማሳለፍ የምመርጣቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ። በዋናነት፣ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ አሳተፋለሁ፤ ቤተክርስቲያን አሄዳለሁ፤ ዜናዎችን ከተለያዩ ምንጮች አከታተላለሁ፤ የቤት ውስጥ ሥራዎችን አከናውናለሁ። እንዲሁም፣ የተለያዩ መጻህፍትን፣ መጽሄቶችን፣ በተለይም የተለያዩ ወቅታዊ መጽሄቶችን አነባለሁ።

የአብክመ ትምህርት ቢሮ እና የፋዌ-ኢትዮጵያ ትብብር

*ከአቶ ለዓለም መኩሪያው

የአማራ ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ፣ ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ፣ በትምህርት ተሳትፎና በተገቢነት ዙሪያ፣ እንዲሁም ትምህርትን ለዘጎች በፍትሃዊነት እና በጥራት በማዳረስ ረገድ በርካታ ውጤታማ ተግባራትን እያከናወነ የሚገኝ የመንግስት ተቋም ነው። በተለይም፣ የልጃገረዶችን የትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነት ለማሳደግ በልዩ ትኩረት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። የቢሮው ዋና ተልእኮ፣ በክልሉ ትምህርትና ሥልጠናን በስፋት፣ በጥራት እና በፍትሃዊነት በማዳረስ፣ የህብረተሰቡን የአመራር ተሳትፎ ባረጋገጠ አደረጃጀት ተነሳሽነቱ የጎለበተ፣ በመብቱ የሚጠቀም፣ ግዴታውን የሚወጣ፣ ምርታማነቱ የዳበረ፣ ለአጠቃላይ ልማት መምጣትም ምክንያት የሚሆን ሰብዓዊ ሃብት ማፍራት ነው። ይህንን ተልእኮውንም ዳር ለማድረስና ለማሳካት፣ ከቅድመ አንደኛ እስከ መምህራን ትምርት ኮሌጅ ድረስ ያሉትን ተቋማት ያስተዳድራል። የተቋማትን መረጃ ስንመለከት፣ 9303 ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ 9510 አንደኛና መካከለኛ፣ 665 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና 10 መምህራን ትምህርት ኮሌጆችን በስሩ ያስተዳድራል።

የአብክመ ትምህርት ቢሮ፣ ከፋዌ-ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር፣ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል ዋና ዋና ከሚባሉት ተግባራቱ መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ። በመሆኑም፣ ረቂቅ የፕሮጀክት ሰነዶች ላይ አስተያየት በመስጠትና ስምምነት በመፈፀም፣ የተጠቃሚ ተማሪዎች ምልመላና መረጣ ላይ በመሳተፍ፣ የማጠናከሪያ ትምህርትና የማማከር አገልግሎት በመስጠት፣ በመስክ ምልከታ ድጋፍ በማድረግ፣ የተለያዩ የስልጠና ማኑዋሎች ዝግጅት ላይ በመሳተፍ፣ የማዳበሪያ አስተያየት በመስጠትና ስልጠናዎችን ለተጠቃሚዎች በማመቻቸት፣ ባጠቃላይም ድርጅቱ ለሚጠይቀን ድጋፍ ሁሉ በቅርበት በመወያየት ምላሽ በመስጠት ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ አድረገናል፣ እያደረግንም እንገኛለን።



ትምህርት ቢሮችን፣ ከፋዌ ጋር በመተባበር ያከናወናቸውን ተግባራት ሲገመግም፣ ድርጅቱ ከትምህርት ቢሮው የትኩረት መስክ ጋር የተገናኘ በመሆኑ በቅርበት የባለቤትነት ስሜት በማሳደር በየደረጃው ካለው አመራር፣ ባለሙያ፣ መምህራንና ተማሪዎች ጋር ተቀራርቦ በመደገፍና ቀና ምለሽ በመስጠት እየሠራ ሲሆን፣ ለቀጣዩም በትኩረት የሚሠራው ጉዳይ ይሆናል። ለአብነት፣ የልጃገረዶችን የትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነትን ለማሳደግ፣ በክበባት እንዲደራጁና በራስ መተማመን መንፈስ እንዲያዳብሩ በትምህርት ቤቶች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ተችሏል።

የአብክመ ትምህርት ቢሮ፣ ከፋዌ-ኢትዮጵያ ጋር አስካሁን ሲያደርጋቸው የነበሩትን ድጋፎችና ክትትሎች በማጠናከር፣ የአጋርነቱን ሚና የሚቀጥል ይሆናል። በቀጣይም፣ የተማሪዎች ቤተሰቦች ስለሴት ልጅ መማር ጠቀሜታ እንዲያውቁና እንዲገነዘቡ፣ የበጎ ፈቃደኝነት ሥራ በትምህርት ቤቶች እንዲቀጥል፣ ለልዩ ልዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎች በስነልቡና እና በቁሳቁስ እንዲደገፉ፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ የማበረታቻ ስልቶች እንዲዘጋጁና የሴቶች የትምህርት ፍትሃዊነት እንዲረጋገጥ፣ እንዲሁም ሴቶች በትምህርታቸው የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የማድረግ ሥራ ይጠበቅብናል።

የአብክመ ትምህርት ቢሮ፣ ከፋዌ-ኢትዮጵያ ጋርም ሆነ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር የሴት ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነት ከፍ እንዲል፣ በአሰር ዓመቱ መሪ እቅድ ውስጥም እነዚህ ተግባራት እንዲካተቱ በማድረግና የተለያዩ ስትራቴጂዎችንም በመንደፍ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። ከዚህ አንፃር፣

ትምህርት ቤቶች ለሴት ተማሪዎች ምቹ እንዲሆኑ፣ ሴት ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡና ከመጡ በኋላም በትምህርት ቤት እንዲቆዩ እና እንዲዘልቁ ለማድረግ፣ ትምህርት ቤቶች ለሴት ተማሪዎች ደህንነት የሚያገለግሉ ግብዓቶችንና መሰረተ ልማቶችን ያሟሉ እንዲሆኑ ማድረግ እና ለዚህም በትብብር መሥራት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም፣ ሴት ተማሪዎች በትምርት ቤቶች ውስጥ ባሉ ክበባት ውስጥ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ፣ የንፅህና መጠበቂያ እና የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎችን በመገንባትና የውስጥ ቁሳቁስ በማሟላት፣ የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት፣ የልጅነት ጋብቻና ዖታዊ ጥቃትን መከላከል ላይ ትክረት ባደረጉ ፕሮግራሞች (የህይወት ክህሎት፣ የስርዓተ ዖታ እኩልነት ግንዛቤና ጥቃትን መከላከል እና የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ) አኳያ በየደረጃው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አጋር ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራርን የበለጠ ማጎልበት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎና ውጤታማነትን የሚገድቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ተፅእኖዎችን መለየትና አካባቢዊ መፍትሄዎችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ፣ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የሚመጡና ድጋፍ የሚሹ ሴቶችን በመለየትና ባለሃብቶችን፣ ረጂ ድርጅቶችንና ማህበረሰቡን በማስተባበር፣ የትምህርት ቁሳቁስ፣ ዩኒፎርምና የንፅህና መጠበቂያ ድጋፎችን እንዲያገኙ ማድረግ፣ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በቅንጅት በመሥራት ከማህበረሰቡ ጋር የንቅናቄ መድረኮችን ማዘጋጀት፣ እንዲሁም ከድርጅቶች ጋር ኔትዎርክ መዘርጋት በትኩረት ሊሠራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ሊሆኑ ይገባል፡፡

ከሃገራችንም ሆነ ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ፣ የሴቶች የትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነት ላይ አሁንም ያልተፈቱ ብዙ ተግዳሮቶች አሉ፡፡ ለአብነትም፣ ወደትምህርት ቤት እንዳይመጡ የሚከለክሉ የትምህርት ቤቶች ተደራሽነት ችግር መኖር፣ ተገቢና ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት ያለመኖር፣ ስርዓተ ትምህርቱና የመማር ማስተማሩ ሂደት ስርዓተ ዖታ ተኮር አለመሆን፣ የመማሪያ አካባቢዎች ምቹ አለመሆን፣ በሴቶች ተማሪዎች ላይ የሚፈፀሙ የሃይል ጥቃቶች ስጋት መኖር፣ የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ ፋሲሊቲዎች በአብዛኛው ትምህርት ቤቶች ያለመኖር፣ በዖታ የተለየ መፀዳጃ ቤቶች አለመሟላታቸው፣ ተማሪዎች በተለያዩ ጉዳዮች ተገቢ መረጃ አለማግኘት/ ያለመብቃት፣ ለሴት ተማሪዎች ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ ድጋፍ ውስንነት ያለበት መሆኑ፣ ችግሮቻቸውን መሰረት ያደረገ ድጋፍ (የስነልቡና፣ የህክምና፣ የህግና የደህንነት) በሚፈለገው ልክ አለመኖር፣ ኢኮኖሚያዊ ነክ የተለያዩ ችግሮች፣ ሴት ተማሪዎች በመማሪያ አድሜያቸው ላለአድሜ ጋብቻ ተጋላጭ መሆናቸው፣ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ በተግዳሮትነት የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ፣ እንደ መፍትሄ መወሰድ ያለባቸው በርካታ ተግባራት ያሉ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥም በመጀመሪያ ደረጃ በቁልፍነት ሊከናወን የሚገባና ሴት ተማሪዎችን ወደትምህርት ቤት እንዲመጡ የሚያስችሉ ስልቶችን መንደፍና መተግበር ያስፈልጋል፡፡ ከስልቶቹ መካከልም፣ የአቅርቦትና የፍላጎት ችግሮችን ሊፈታ የሚችልና ሴት ተማሪዎችን ወደትምህርት ቤት ሊያመጣ የሚያስችል እቅድ ማዘጋጀት፣ ትምህርት ቤቶችን ተደራሽ ማድረግ፣ በየደረጃው ከሚገኙ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የንቅናቄ ሥራዎችን በተለያዩ ስልቶች፣ ማለትም በውይይት መድረክ፣ በሚዲያ ተደራሽ ማድረግ፣ የኢኮኖሚ አቅም የሌላቸውን ቤተሰቦችና ተማሪዎች በተለያዩ ፕሮግራሞች መደገፍ፣ በሴቶች ትምህርት ጠቀሜታና ተግዳሮቶች ዙሪያ ለልጃገረዶችና ወላጆች እንዲሁም ለማህበረሰቡ ግንዛቤ መፍጠር፣ ለችግረኛ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ፣ የንፅህና መጠበቂያ፣ የምገባ መርሃግብርና ሌሎች አማራጮችን ማመቻቸት፣ በሴት ልጆች ትምህርት ጠቀሜታ ዙሪያ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ መፍጠር፣ ሴት ተማሪዎችን ትምህርት ቤት ለማቆየትና ውጤታማ ለማድረግ ስርዓተ ትምህርቱን ስርዓተ ዖታ ተኮር ማድረግ፣ የሴት መምህራንን፣ የርእሳነ መምህራንንና የሱፐርቫይዘሮችን ቁጥር ማሳደግ፣ የመማሪያ አካባቢን ምቹ ማድረግ፣ በትምህርት ቤት ደረጃ የስርዓተ ዖታ ትንተና በማድረግ የትምህርት ቤት አካባቢንና የመማር ማስተማር ሂደቱን ፍትሃዊና ለስርዓተ ዖታ ምላሽ ሰጭ ማድረግ፣ የማህበረሰቡን በተለይም የወላጆችን ተሳትፎ ማጠናከር፣ የስነልቡናና የማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረግ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ትስስር በመፍጠር የቅብብሎሽ አሠራሮችን ማጠናከር፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከል፣ ሴት ተማሪዎች ራሳቸውን የሚያበቁባቸውን መድረኮች መፍጠር፣ ለሴት ተማሪዎች የሜንቶሪንግ አገልግሎትን ተደራሽ ማድረግ፣ በተለያዩ ችግሮች ትምህርት ሊያቋርጡ የሚችሉ ህፃናትን በየጊዜው መለየትና ፍላጎታቸውን ማሟላት፣ የመምህራንን ብቃት ማሻሻል፣ ምሳሌ ለሚሆኑ ሴት ተማሪዎች፣ ወላጆችና ባለድርሻ አካላት በየጊዜው አውቅና መስጠት እና የመሳሰሉት በሴቶች ሁለንተናዊ የትምህርት ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ለመቅረፍ እንደመፍትሄ በመቀየስ መንቀሳቀስ ተገቢ ይሆናል፡፡

ሴቶችን በሃገራችንም ሆነ በክልላችን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተገቢው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ የሚኖረውን ጠቀሜታ በመረዳት፣ በርካታ ሥራዎችን ማከናወን ተገቢነቱ አያጠያይቅም፡፡ ከዚህ አኳያ በተለይ፣ የሴቶችን በራስ መተማመንና በራስ የመወሰን አቅምን ለማሳደግ፣ ሥርዓተ ትምህርቱ ለስርዓተ ዖታ ምላሽ ሰጭ ሆኖ ሴት ተማሪዎች እኩል ተሳታፊና ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል፣ እንዲሁም የተመጣጠነና ጥራት ያለው ትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ለሃገር እድገት ከፍተኛ ፋይዳ ያለው መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡ ለዚህም፣ የመንግስትና እንደፋዊ - ኢትዮጵያ ያሉ የሌሎች ባለድርሻ አካላት የጋራ ርብርብ እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በመጨረሻም፣ የማስተላለፈው መልእክት፣ የሴቶችን ትምህርት መደገፍ፣ የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት ቢሆንም፣ ፋዊ - ኢትዮጵያ፣ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሆኖ፣ በክልላችን ሴት ተማሪዎችን በሁለንተናዊ መልኩ ለመደገፍ እያደረገ ያለውን ውጤታማ የሆነ ድጋፍ በዚህ አጋጣሚ ላመሰግን እወዳለሁ፡ ፡ ሌሎች አጋር አካላትም፣ ልክ እንደፋዊ - ኢትዮጵያ ሁሉ በሴቶች ትምህርት ዙሪያ ድጋፍ ቢያደርጉ፣ የመማር እድል ያላገኙትን እንዲማሩ፣ ቤት ውስጥ ሲውሉ ከሚደርስባቸው ጥቃት መከላከል የሚችሉ፣ በራሳቸው የሚተማመኑና ለሃገር ግንባታ የበኩላቸውን ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ፣ የነገ ሃገር ተረካቢ ዜጎችን ማፍራት ላይ አሻራ ማሳረፍ ነው ብዬ እመክራለሁ፡፡

ሴት ልጅን ማስተማር ማለት፣ ሃገርን ከፍ ወዳለ እና ወደላቀ የእድገት ደረጃ ማሸጋገር ነው!

**አቶ ለዓለም መኩሪያው፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምርት ቢሮ፣ በአቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት፣ በፕሮጀክት ዝግጅት ክትትልና ግምገማ እና ሃብት ማፈላለግ ባለሙያነት በማገልገል ላይ የሚገኙ ባለሙያ ናቸው፡፡*

አርአያዎቻችን

ሰዓሊ ደስታ ሐጎስ

አንዳንዶች "የስዕል ንግስት" ይሏቸዋል። የስዕል ጥበብ ገና ምንም አውቅና ባላገኘበት ወቅት ነበር የህይወት ጥሪያቸውን፣ የስዕል ጥበብን ሞያዬ ብለው ለመከተል የወሰኑት። ሰዓሊ ደስታ ሐጎስ፣ ለሙያቸው ባላቸው ጽኑ ፍቅር እና ቁርጠኝነት በስዕል የገጠሟቸውን ፈተናዎች በድል አልፈው፣ አንቱ የተባሉ ሰዓሊ ለመሆን በቅተዋል። ሽልማትና እውቅና ማግኘት የጀመሩት፣ ገና የአስራ አንድ ዓመት ታዳጊ ሳሉ ነበር። መንፈሰ ብርቱዋና በመልካም ሥነምግባር የታነፀት ሰዓሊ ደስታ ሐጎስ፣ ዛሬ ለበርካታ የጥበብ ሰዎች በአርአያነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ሥራን የመውደድ መሰረቴ ቤተሰቦቼ ናቸው። ለዛሬ ማንነቴ ከወላጆቼ የወረስኳቸው በርካታ መልካም ነገሮች አሉ። በፍቅር እያሳደጉ በፍቅር መንገድን አሳዩኝ። ባሳለፍኩት ማህበራዊ ህይወት እና የሥራ ዓለም ውስጥ መልካም ሥነምግባር እና ግንኙነት እንዲኖረኝ፣ ከወላጆቼ የወረስኩት ልምድና ባህርይ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው ማለት እችላለሁ። ከወላጆቼ በሥራ ማመንን፣ ቀናነትን፣ ሃቀኝነትን ፣ በራስ መተማመንን ፣ በትምህርት ማመንን፣ ሥራን ያለመናቅን፣ ሰውን መውደድን ተምሬአለሁ። ከዚህ ጎን ለጎን በትምህርት ቤት የግብረገብ ትምህርት ይሰጥ ነበር። በዚያ ትምህርት የራስ ያልሆነን ንብረት አለመንካት፣ ጥሩነት የሚያስከብር መሆኑን ስማር ነው ያደግሁት።

በስዕል ሽልማት ማግኘት የጀመርኩት፣ የአስራ አንድ ዓመት ልጅ ሆኜ ነበር። በ1953 ዓ.ም. እኔ ባለወቅሁበት ሁኔታ፣ የሥዕል ሥራዎቼ በህንድ ፋውንዴሽን ለተዘጋጀ ዓለም አቀፍ የህፃናት ስዕል ውድድር ተልከው አሸንፈዋል። ያኔ እድሜዬ ገና አስር ዓመት ነበር። በህንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጃዋሃራላል ኔሩ ፊርማ የተፈረመበት የብር ዋንጫ ሽልማት አግኝቻለሁ። ሽልማቱም በወቅቱ የትምህርት ሚኒስቴር የነበሩት ዶ/ር መንገሻ ገብረህይወት ህንድ ሀገር ሄደው ተቀብለው አምጥተዋል።

ለችግሮች እጅ መስጠት አልወድም፤ ከስዕል ትምህርት ቤት ከተመረቅሁ በኋላ በመምህርነት ለመቀጠር ከአምስት ጓደኞቼ ጋር ወደትምህርት ሚኒስቴር ነበር ያቀናሁት። ከወንዶች እኩል መሥራት አትችልም የሚል ስጋት የነበራቸው የወቅቱ የትምህርት ሚኒስቴር የሥራ ሃላፊዎች፣ አልም ወዳለ ገጠር "ብንመድብሽ ሄደሽ ትሠሪያለሽ?" ሲሉ ጥያቄ አቀረቡልኝ። የመጀመሪያ ፈተና መሆኑ ነው። እኔም፣ የትም ሆዶ ለመሥራት ልቤ ሙሉ ስለነበር፣ "ለምን አልሄድም!" ነበር መልሴ። ይሁንና፣ በአዲስ አበባ ውስጥ ካሉት ትምህርት ቤቶች መካከል በአንዱ ውስጥ ተመድቤ አስተምሬአለሁ። ከተማሪዎቼ ጋር በእድሜም ተቀራራቢዎች ስለነበርን፣ እንደ ጓደኛም እንደ መምህርንም ጥሩ የሥራ ጊዜ አሳልፌአለሁ።

እኔ በተፈጥሮዬ ለችግሮች እጅ መስጠት አልወድም። በርካታ ፈተናዎች ቢጋረጡብኝም፣ ሁሉንም በድል ተወጥቻለሁ ብዬ አምናለሁ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ልጄን በጥሩ ሥነምግባር አሳድጌ፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢኮኖሚክስ/ማኔጅመንት እንድትመረቅ በማድረግ ለቁም ነገር ማብቃቴና የምወደውን ሥነጥበብ ማስቀጠል መቻሌ የምኮራባቸው የህይወት ድሎቼ ናቸው። ሌላው በህይወቴ ፈታኝ የነበረው ነገር፣ ሴት በመሆኔ የሚሰጠኝን ሃላፊነት ትወጣለች ብሎ አለማመንና ለመተባበር እና ለማገዝ ፈቃደኛ ያለመሆን ሁኔታ ነበር። ይሁንና፣ በሥራ በማሳየት፣ ብቃት እንዳለኝ በማስመስከር፣ ይህን ፈተና ልወጣው ችያለሁ።

እኔ ከብዙ ገንዘብ ይልቅ፣ የስዕል ሙያንና እውቀቴን እያዳበርኩ ከሥነጥበብ ጋር ሁሌ መኖር ያስደስተኛል። ይህ ጽኑ አቋሜ ነው። በእርግጥ፣ በእንደዚህ ዓይነቱ የህይወት ጎዳና ለመዝለቅ መወሰን ቀላል አይደለም፤ ትልቅ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። ይሁንና፣ ከዚህ ውሳኔዬና ቁርጠኝነቴ ውስጥ የህይወት ደስታና እርካታን አግኝቼበታለሁ።

ሴቶች ጠንካራ ሁኑ! ታማኝነትን ጨምሩ፤ ለችግሮች እጅ አትስጡ። የማንም ጥገኛ አትሁኑ። ማንኛውም ነገር ለማከናወን፣ "ብቻዬን በቂ ነኝ" ብላችሁ አስቡ። የህይወት አጋራችሁም ቢሆን፣ ይረዳኛል ብላችሁ ተስፋችሁን አትጣሉ። በተለይ ደግሞ፣ ሰዓሊ ለመሆን ከወሰናችሁ ሙያውን ውደዱት። የሰውን ሀሳብ ለመኮረጅ አትሞክሩ፤ ራሳችሁን ሁኑ፤ ሰውን ለመምሰል መሞከር ራስን ማወናበድ ነው! በመጨረሻም ሀገራችሁን ውደዱ!

ጋዜጠኛ አሌኒ መኩሪያ

ከግማሽ በላይ የሚሆነውን እድሜያቸውን በጋዜጠኝነት ሙያ ያሳለፉት ወ/ሮ አሌኒ መኩሪያ፣ ከሃምሳ ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መስኩት ብቅ በማለት "የኢትዮጵያ ህዝቦች ሆይ በአዜ ኃይለሥላሴ መልካም ፈቃድ ዛሬ ቴሌቪዥን ጀምሯል። እንኳን ደስ አላችሁ!" የሚለውን የምስራች ያበሰሩ ቀዳሚ ጋዜጠኛ ናቸው።

ወላጆቼ፣ በልጅነቴ በመልካም ሥነምግባር እንድታነፅ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ትልቅ ሰው ማክበር፣ ለሚደረግልኝ ሁሉ ማመስገን እና ለወላጆች መታዘዝ እንዳለብኝ አስተምረውኛል፤ ትህትና እንዲኖረኝም ዘውትር ይነግሩኝ ነበር። ትምህርት ቤቶቻችንም እንዲሁ፣ በመልካም ሥነምግባር ታንፀን እንድናድግ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጡ ነበር። የተማርኩባቸው ትምህርት ቤቶችም፣ መልካም ሥነምግባር እንዲኖረኝ ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ ነበራቸው። ይህ ደግሞ፣ ከእኔም አልፎ ወደወላጆቼ ተሻገረ መሰለኝ ልጆቼም መልካም ሥነምግባር ያላቸው ናቸው።

የተሻለ ህይወት ለመኖር፣ ለሃገርና ለወገን የሚጠበቅብንን ለማበርከት፣ ጥረትና ትጋት ለውጤት የሚያበቁን መንገዶች ናቸው። ይህ ደግሞ፣ በመልካም ሥነምግባር መታገዝ አለበት። መልካም ያልሆነ ሥነምግባር፣ በጥረትና በትጋት የሚገኘውን ውጤት ያኮሰሳል። መልካም ሥነምግባር ደግሞ አብሮ ካለደገ፣ ድንገት ደርሶ የሚዳብር ባህርይ አይደለም። እኔ ደግሞ፣ በዚህ ረገድ ሳይሳካልኝ አይቀርም። ያልዘሩት አይበቅልም። ሰው በልፋትና በትጋት ነው የድካሙን ፍሬ የሚያገኘው። ሳይደክሙ የሚገኝ ምንም ነገር የለም። ትውልዱም በዚህ እውነት ውስጥ ተቃኝቶ እንዲያድግ፣ በርትቶ ማስተማር ያስፈልጋል። ሰዎችን የመርዳት ባህርይ እንዲያዳብር መሥራት ያስፈልጋል። ሰዎችን መርዳት በአለኝ አቅም ያለኝን ነገር በማካፈል መስጠት በህይወቴ ደስ የሚለኝ ጉዳይ ነው። ሰዎች ተቸግረው ሳይ የሚያስጨንቀኝ፣ "እኔ ለምን ምንም ነገር ማድረግ አልቻልኩም" የሚለው ሀሳብ ነው።

ገና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለሁ፣ ያኔ ሬስ ክለብ (RACE CLUB) በአሁኑ ጃን ሜዳ የፈረስ አሽቅድድም ውድድር አንደኛ በመውጣቴ ያገኘሁትን አውቅናና

ደስታ አልረሳውም። "THE CHILD BIRDES" (ህፃናቱ ሙሽሮች) የሚል ዶክመንተሪ ፊልም ላይ በአቅራቢነት "CHANNEL 4" ከተባለ የእንግሊዝ ሚዲያ ጋር ሰርቻለሁ። በዚህም ሽልማት አግኝቻለሁ። ብስራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ ሳለሁ በስደተኞች ላይ በሠራሁት ፕሮግራም አማካይነት ከዓለም አቀፉ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (ዩ.ኤን.ኤች.ሲ..አር) ሽልማት አግኝቻለሁ።

ሥራ ስጀምር በድንገት ስለሆነ ወደጋዜጠኝነት ሙያ የገባሁት፣ አርአያ ልለው የምችል ሰው አልነበረኝም በመስኩ። ነገር ግን፣ ባሳለፍኩት ህይወት፣ ሞዴል የሆነችኝ እናቴ ናት።እናቴ የሴት ወይም የወንድ የሚባል የሥራ ዓይነት አታውቅም። ሁሉንም መሥራት ነው። ነፃ ሆኜ ስለደከ ሴት በመሆኔ የደረሰብኝና የማስታውሰው ነገር የለም። ይህ ማለት ግን ሴቶች ላይ ችግር የለም ማለት ግን አይደለም። ሌሎች ሲያማርሩ፣ ቅሬታቸውን ሲግልፁ አሰማለሁ። የሆነ ሆኖ ይህ ችግር ብርቱ በመሆኑ፣ ሴቶች በጥረትና ራሳቸው ሰርቶ በማሳየት ሊታገሉት ይገባል። አሁን ዘመኑ ተቀይሯል፤ ካሰቡበት ለመድረስ የሚችሉበት ሰፊ እድል አለ፤ ይህንን በብልሃት መጠቀም ያስፈልጋል።

ያልዘሩት አይበቅልም። ሰው በልፋትና በትጋት ነው የድካሙን ፍሬ የሚያገኘው፣ሳይደክሙ የሚገኝ ምንም ነገር የለም። ትውልዱም በዚህ እውነት ውስጥ ተቃኝቶ እንዲያድግ፣በርትቶ ማስተማር ያስፈልጋል። ሰዎችን የመርዳት ባህርይ እንዲያዳብሩ መሥራት ያስፈልጋል።ሰዎችን መርዳትና በአለኝ አቅም ያለኝን ነገር በማካፈል መስጠት፣ በህይወቴ ደስ የሚለኝ ጉዳይ ነው። ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት፣ ሰዎች ተቸግረው ሳይ የሚያስጨንቀኝ ነገር "እኔ ለምን ምንም ነገር ማድረግ አልቻኩም" የሚለው ሀሳብ ነው።

ልጆችን በመልካም ሥነምግባር አንፆ በማሳደግ ሂደት፣ የሁሉም አስተዋፅኦ የግድ ቢሆንም፣ ወላጆች በተለይም እናትና አባት አርአያ ሆነው መገኘት፣ በየትምህርት ቤቶቹ የሚገኙ መምህራን ሙያውን የሚወዱና ለተማሪዎቻቸው ምሳሌ መሆን አለባቸው። የአካባቢው ህብረተሰብም፣ የራሱን ድርሻ መወጣት አለበት። ወደሥራ ዓለም የሚሰማራው ይኸው ትውልድ ነው። በመሆኑም፣ የሥራ ዲስፕሊን ያለው፣ በቅንነት ለማገልገል የሚተጋ ዜጋ ለማፍራት፣ ከስር መሰረቱ ከትኩቶ ማሳደግ የግድ ይሆናል አላለሁ።

ዘመኑ የመረጃና ቴክኖሎጂ በመሆኑ፣ መልካም ነገር የሚያስገኙትን ያህል ትውልዱን በቀላሉ ወደተሳሳተ መንገድ የሚወስዱ መልካም ያልሆኑ ሁኔታዎች መኖራቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም፣ ወጣቶች መልካም ስብእናቸውን የሚያጎለብት፣ የእውቀት አድማሳቸውን የሚያሰፋውን መረጃ መምረጥና መጠቀም እንጂ፣ ያዩትን ሁሉ ከማድረግና ከመፈለግ መቆጠብ ይኖርባቸዋል። ጊዜያቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ አመክራለሁ። ምርጫቸው ላይ መጠንቀቅ አለባቸው። ሌላው ዓለም ያደረገው ነገር ሁሉ ልክ ነው ማለት አይደለም።

ቤተሰብም፣ ከልጆቹ ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር አለበት። ወላጆች ከልጆች ጋር ጥሩ ግንኙነት ከሌላቸው፣ የሚያደርጉትን ማወቅ አይቻልም። ለልጆች ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። ማቅረብ፣ መረዳትና የቅርብ ክትትል ማድረግ ጠቃሚ ነው። ብዙ ጊዜ፣ ለመቅጣትና ለመቆጣት ሲሆን ጊዜ ይኖራል። በአንፃራዊ ሁኔታ፣ በተለያዩ ምክንያቶች ትውልዱ ፈጣን ነው። ይህንኑ በመረዳት፣ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር፣ ለሃገርና ለወገን የሚጠቅሙ ዜጎች እንዲሆኑ ማድረግ ይችላሉ የሚል አምነት አለኝ።

ምንጭ፡-ፌለግ፣ የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረሙሰና ኮሚሽን፣ ጥር 2008 ዓ.ም.

አፍሪካዊቷ ማዘር ቴሬዛ - የክብር ዶ/ር አበበች ጎበና (1928-2013)

"አራሴ የወለድኳቸው ልጆች የሉኝም፤ ግን በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ልጆች አንዲሁም ቤተሰብ አፍርቻለሁ፤ ስለዚህ ምንም አይቆጨኝም።" የክብር ዶ/ር አበበች ጎበና

የክብር ዶ/ር አበበች ጎቦና (በልጆቻቸው "እዳዬ" ተብለው ይጠራሉ) ፣ በህይወት ዘመናቸው ላበረከቱት አርአያነት ያለው አኩሪ ሥራ፣ የሰብዓዊነትና የሴቶች ህያው አርአያ የበጎ ተግባር ከተለያዩ ሀገርአቀፍና ዓለምአቀፍ ተቋማት ታላላቅ ሽልማቶችንና እውቅናዎችን አግኝተዋል። ከሽልማቶቹም መካከል፡-

- ከጅማ ዩኒቨርስቲ፣ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ በሂውማኒቲ
- ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፣ ሜዳሊያ እና የክብር የምስክር ወረቀት
- በሁለተኛው የዓለም ምግብ ፕሮግራም፣ ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን የክብር ተሸላሚ
- በCCRDA የብር አዮቤልዩ ክብረ በዓል ላበረከሩቱት ከፍተኛ አስተዋፅኦ፣የእውቅና ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት
- ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ የክብር የምስክር ወረቀት እና ዋንጫ
- ከኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የክብር የምስክር ወረቀት፣ ሜዳሊያና ዋንጫ
- ከኢንተር ሪሊጂየስ ኤንድ ኢንተርናሽናል ፌዴሬሽን ፎር ዎርልድ ፒስ፣ የሰላም አምባሳደርነት የምስክር ወረቀት
- ለአፍሪካ ዘላቂ ልማት ፋይዳ ላለው አርአያነትና ተነሻነት ሥራዎች የማእከላዊ አፍሪካ የክልል አሸናፊ በመሆን፣ የምስክር ወረቀት እና ዋንጫ
- ዓለምአቀፍ ሽልማት፣ ከለንደን ወርልድዊር ቢዝነስ አዋርድ
- በአፍሪካ ደረጃ፣ እናት አፍሪካ (MOTHER AFRICA) ከደቡብ አፍሪካ
- ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት፣ በተለያዩ ጊዜያት ዋንጫዎችንና ምስክር ወረቀቶችን
- ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ከንቲባ ጽ/ቤት፣ በተለያዩ ጊዜያት ልዩ ልዩ ሽልማቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

ዶ/ር አበበች ጎበና ለህዝብ ላበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ በርካታ ተቋማት በስማቸው ተሰይመዋል። ለአብነትም፡-

- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሀገራችን የመጀመሪያ የሆነው፣ "አበበች ጎበና የእናቶችና ህፃናት ሆስፒታል"
- በሰላሌ ዩኒቨርስቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ "አበበች ጎበና ካምፓስ"
- በአምቦ ዩኒቨርስቲ፣ "አበበች ጎበና ግብርና ምርምር ማእከል"
- በአዲስ አበባ ፣ሁለት የግል ባንኮችና አንድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎችን በስማቸው መሰየማቸውን መጥቀስ ይቻላል።

ክብርት ዶ/ር አበበች (እዳዬ)፣ "ድህነትን በተለይም የህፃናት ጉስቁልናን መቅረፍ የሚቻለው፣ በግለሰብ ደረጃ ለምፅዋት በሚወረወሩ ሽርፍራፊ ሳንቲሞች ሳይሆን፣ በአንድነት በማበር እና ያለንን አቅም በማሰባሰብ በችግር ላይ ያሉ ወገኖቻችንን በተለይም ሴቶችን ስናበቃ ነው።" የሚል አምነት ነበራቸው።

ምንጭ፡- አበበች ጎበና የህፃናት ክብካቤና ልማት ማህበር (አጎህልማ)

ለፋዌ-ኢትዮጵያ ፕሮግራሞች ስኬት የባለድርሻ አካላት አስተዋፅኦ- ቆይታ ከአቶ ሙሉጌታ መኩሪያው ጋር

ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ የሴት ተማሪዎችን ወጤታማነት ከፍ ማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ በተለያዩ የሃገራችን ክልሎች ውጤታማ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል። ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ በአስካሁኑ ውጤታማ ጉዞው እንዲቀጥል፣ በየደረጃው ያሉ የፊዴራልና የክልል ተቋማት የነበራቸው አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ነው። እነዚህ አካላት፣ ለፋዌ-ኢትዮጵያ ስኬታማ ጉዞ ስለነበራቸው ጉልህ ሚና የመጽሄታችን አንባቢዎች ግንዛቤ ይኖራቸው ዘንድ፣ የአማራ ክልል ገንዘብ ቢሮ ውስጥ በከፍተኛ ባለሙያነት እያገለገሉ ከሚገኙት ከአቶ ሙሉጌታ መኩሪያው ጋር እንደሚከተለው ቆይታ አድርገናል።



ትማር፡- ራስዎን ለመጽሄታችን አንባቢዎች ቢያስተዋውቁ?

ሙሉጌታ መኩሪያው፡- ሙሉጌታ መኩሪያው እባላለሁ። በሥራው ዓለም 18 ዓመት የሥራ ልምድ አለኝ። በአሁኑ ወቅት፣ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብ ቢሮ ውስጥ በመሥራት ላይ እገኛለሁ። በፕሮጀክት አቅድና አመራር የማስተርስ ዲግሪ አለኝ።

ትማር፡- የፋዌ አጋር ስለሆነው ድርጅትዎ አጭር ማብራሪያ ቢሰጡን?

ሙሉጌታ መኩሪያው፡- የክልላችን ገንዘብ ቢሮ፣ ፋዌ-ኢትዮጵያን ከመሰሰሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት በመሥራት፣ ከብድርና እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝን ሃብት ለተባለለት ዓላማ እንዲውል ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፣ በመከታተል፣ በመደገፍ ላይ ይገኛል።

ትማር፡- ድርጅትዎ ከፋዌ-ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል። በእስካሁኑ ሂደት ያከናወናቸውንና በማከናወን ላይ ያላቸውን ተግባራት ባጭሩ ቢዘረዝሩልን?

ሙሉጌታ መኩሪያው፡- ቢሮችን ከፋዌ-ኢትዮጵያ ሁለት ጊዜ ባደረገው የፕሮጀክት አፈፃፀም ስምምነት መሰረት፣ ባለፉት ተከታታይ አስር ዓመታት በርካታ ሴት ተማሪዎችን ተጠቃሚ ያደረጉ ተግባራት እንዲከናወኑ የበኩሉን አገዛ አድርጓል። በአሁኑ ወቅትም፣ 150 ሴት ተማሪዎችን እና 50 ወንድ ተማሪዎችን፣ በድምሩም 200 ተማሪዎችን ተጠቃሚ ያደረገ ፕሮጀክት በመተግበር ላይ ይገኛል። ፕሮጀክቱ በየአፈፃፀም ዘመኑ እጅግ ውጤታማ እንደነበር በክትትልና ግምገማ፣ እንዲሁም በማጠናቀቂያ ግምገማዎች ማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን፣ በዚህም ተጠቃሚ ተማሪዎች በራስ የመተማመን መንፈስ መፍጠራቸውን፣ በትምህርት ውጤታቸውም የተሻሉ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል። እንዲሁም፣ በፕሮጀክቱ ለአካል ጉዳተኞች ትኩረት ተሰጥቶ ድጋፍ ተደርጓል። እንደአጠቃላይ፣ ፋዌ ኢትዮጵያ ካስቀመጠው ግብ አንፃር፣ በአስቸጋሪ የኑሮ ደረጃ ውስጥ ሆነው በትምህርታቸው ግን ጎበዝ የሆኑ ሴት ተማሪዎችን ውጤታማ ከማድረግ አኳያ ግቡን ዳር ማድረስ ችሏል ብሎ መመስከር ይቻላል። ይህንንም፣ በተማሪዎች አንደበትና በደረሱበት ውጤታማ የትምህርት ስኬታማ ሂደት ማረጋገጥ የሚቻል ነው። ስለዚህ፣ ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ በመደበው ውስን ሃብት ውጤታማ ሥራ መሥራቱን ቢሮችን በዚህ አጋጣሚ ያረጋግጣል።

ትማር፡- ድርጅትዎ ከፋዌ-ኢትዮጵያ ጋር አስካሁን ያከናወናቸውን ተግባራት እንዴት ይገመግሟቸዋል?

ሙሉጌታ መኩሪያው፡- ካካሄድናቸው የፋዌ-ኢትዮጵያ የፕሮጀክት ውጤታማነት ግምገማዎች እንደተገነዘብነው፣ በጣና ሃይቅ እና በባህርዳር አካዳሚ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች፣ ተጠቃሚ ካልሆኑት ተማሪዎች ይልቅ በውጤት ደረጃ በ4.4% ብልጫ እንዳላቸው ማረጋገጥ ተችሏል። ስለዚህ፣ በፕሮጀክቱ አማካይነት ለተጠቃሚ ተማሪዎች በተለያየ መልኩ የሚደረጉ ድጋፎች (ቱቶሪያል፣ የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ፣ ስልጠናዎች፣ወዘተ.)፣ ለጠቀስነው የትምህርት ውጤት መሻሻል የበኩላቸውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳደረጉ መረዳት ይቻላል።

ትማር፡- ፋዌ-ኢትዮጵያ የሚያከናውናቸው ተግባራት በውጤታማነታቸው እንዲቀጥሉ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

ሙሉጌታ መኩሪያው፡- ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ በክልላችን እየተገበረ ያለው ፕሮጀክት ውጤታማነት፣ ከአካዳሚያዊ ጉዳዮች ባሻገር፣ የሴቶችን መብትና ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮችም (CROSS-CUTTING ISSUES) የሚሳተፍ መሆኑ ይታወቃል። ስለሆነም፣ ፕሮጀክቱ ከአስካሁኑ የበለጠ ውጤት እንዲመዘገብበት፣ ከሌሎች በሴቶች ጉዳዮች ላይ ከተሰማሩ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት መሥራቱን ይበልጥ ቢያጠናክር፣ እንደቢሮም እኛም ብንደግፍ፣ እንዲሁም ፕሮጀክቱ ከታች የክፍል ደረጃዎች ጀምሮ የሚሠራበት ሁኔታ ቢፈጠር፣ በጥቅሉም የፕሮጀክቱን ዓላማንና ግብን ከፖሊሲ ጋር በማስተሳሰር በትብብር በየደረጃው ቢተገብር የተሻለ ይሆናል፤ ለበለጠ ውጤታማነትም ጠቃሚነት ይኖረዋል በማለት ማስገንዘብ እወዳለሁ።

ትማር፡- በሀገራችን ሴቶች ላይ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች አሁንም በስፋት የሚስተዋሉ ከመሆናቸው አኳያ፣ ከቢሮዎ ዓላማ አንፃር በቀጣይ ምን መከናወን አለበት ይላሉ?

ሙሉጌታ መኩሪያው፡- የሴቶች ጉዳይ በክልላችን በፖሊሲ ማእቀፍ የተካተተ እንደመሆኑ፣ እንደገንዘብ ቢሮ በሴቶች ዙሪያ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን እንገኛለን። ዓመታዊ እቅዳችን ውስጥ ስርዓተ ፆታን ማእከል ያደረጉ ተግባራት ይካተታሉ፤ ለትገበራቸውም ተገቢው ትኩረት ይሰጣል። በክልላችን የሚገኙ ተቋማትም፣ ሴቶች ላይ ያተኮሩ ተግባራትን በእቅዳቸው ውስጥ እንዲያካትቱ በየጊዜው እናሳስባለን፤ እንዲተገብሩም የበኩላችንን ጥረት እናደርጋለን። ሆኖም፣ እነዚህን ተግባራት የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ፣ ከፍ ብዬ በገለፅኩት መሰረት፣ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በትብር መሥራት (በCONSORTIUM ደረጃ) እጅግ ጠቃሚና ሊጠናከር የሚገባው ጉዳይ ይሆናል።

ትማር፡- ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር፣ በሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ረገድ አሁንም ቁልፍ ተግዳሮቶች ናቸው፣ ትኩረትንም ይሻሉ ከሚሏቸው ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ከአነመፍትሄያቸው ቢጠቁሙን?

ሙሉጌታ መኩሪያው፡- የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ከወንዶች ጋር በንፅፅር ሲታይ፣ የሚበረታታና ውጤታማ ነው። በውጤት ደረጃ ግን፣ ወደ ዩኒቨርሲቲ ከሚገቡት ጋር ሲነፃፀር (ተወዳዳሪ ከመሆን አኳያ) የሚቀሩ ነገሮች እንዳሉ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በመሆኑም፣ ይህን የውጤት ልዩነት ለመቀልበስ፣ በየደረጃው ባሉ አካላት ትብብርና ቅንጅት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል የማድረጉን ሥራ ከአሳከሁኑ በበለጠ አጠናክሮ መቀጠል ያሻል። ከዚህ አኳያ፣ ቢሮችን ሴቶችን በተመለከተ ከወንዶች አኩል ተወዳዳሪነታቸው አስኪረጋገጥ ድረስ የበኩሉን ሚና ለመጫወት ዝግጁ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ አስታውቃለሁ።

ትማር፡- ሴቶችን በተመለከተ በሚከናወኑ ተግባራት ዙሪያ ርብርብ ማድረግ ስለሚኖረው ፋይዳ፣ ለተለያዩ አካላት የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ ቢያካፍሉን?

ሙሉጌታ መኩሪያው፡- ሴቶችን በተመለከተ በሚከናወኑ ሁለንተናዊ ተግባራት ላይ የሃገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ምሁራን፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ወዘተ. በተለያየ መልኩ በሴቶች ላይ ለሚስተዋሉ ተግዳሮቶች መቀረፍ የበኩላቸውን አገዛ በማድረግ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ እንደመሆኑ፣ ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከሌሎች ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት የእነዚህን አካላት ሚና ማጎልበት በሚያስችሉ ጉዳዮች ዙሪያ በትኩረት መንቀሳቀስ ጠቀሜታ አለው። እንዲሁም፣ በየደረጃው ከሚገኙ የትምህርት አካላት ጋርም የተቀናጀ አሠራርን ይበልጥ ማጎልበት፣ በትምህርት ቤቶች ክበባትን ማጠናከር፣ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋርም ትስስር መፍጠር፣ ፋዌ - ኢትዮጵያ ለሚተገብራቸው መሰል ፕሮጀክቶች የበለጠ ውጤታማ መሆን ጠቀሜታ አለቸው። ስለሆነም፣ ለእነዚህና መሰል ተግባራት፣ ተገቢው ትኩረት በመስጠት መንቀሳቀስ እንደሚገባ በዚህ አጋጣሚ ላሳስብ እወዳለሁ።

በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚከሰት እርግዝና በህብረተሰቡ ላይ የሚያሳድራቸው 11 ተፅእኖዎች

ገና በለጋ እድሜ መፀነስ በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኘውን አካላዊ እና አእምሮዊ ጤንነት የሚጎዳ ከመሆኑም በላይ፣ በህብረተሰቡ ላይም እጅግ አስከፊ ጉዳት ያስከትላል። ያላገቡ እና በታዳጊነታቸው የሚያረግዙ ሴቶች፣ ማህበራዊ መድልዎ ሊደርስባቸው ይችላል። ብዙ ጊዜ ትምህርታቸውን ለመጨረስ የሚያስችላቸውን ድጋፍ ያጣሉ፤ ሥራም ለማግኘት እና በህብረተሰቡ ውስጥ የተረጋጋ ኑሮ ለመኖርም ይቸገራሉ።

ማህበራዊ መገለል እና ድህነት ለአደገኛ ባህርያት ተጋላጭ ያደርጋቸዋል። ይህም፣ በተራው ደግሞ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ እናቶች እና ልጆቻቸውን መልሶ ለማቋቋም እና ደህንነታቸውን ለመጠበቅ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ በሚያስፈልገው መንግስት ላይ የኢኮኖሚ ጫና ስለሚፈጥርበት፣ ለህብረተሰቡ ጠቀሜታ ባላቸው ሥራዎች ላይ የሚሰጠውን ትኩረት ይቀንስበታል፤ ይህም በህብረተሰቡ ላይ የሚያስከትለው ተፅእኖ ቀላል አይሆንም።

በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ያለ እርግዝና በህብረተሰቡ ላይ ስለሚያሳድረው ጫና፣ እንዲሁም በወላጆች እና በታዳጊዎች ላይ ስለሚኖረው ተፅእኖ የሚከተሉትን 11 ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በትምህርት መስፋፋት ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ፡-

በለጋ እድሜያቸው የሚያረግዙ በአሠራዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ታዳጊዎች፣ ከእርግዝናቸው ጊዜ አንሰቶ ለተጨማሪ ሀላፊነት ስለሚዳረጉ፣ ትምህርታቸውን ካሉበት ደረጃ ለመቀጠል አዳጋች ይሆንባቸዋል። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ ከሆኑ ደግሞ፣ አንዳንዶቹ ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ከመገደዳቸውም በላይ፣ እና በደረሰባቸው ተጨማሪ ጫና የተነሳ ኑሯቸውን ለመደጎም ሲሉ ሥራ ፍለጋ ይወጣሉ። እነዚህ ሌሎች ሁኔታዎች፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የመሃይማንን ቁጥር ይበልጥ እንዲጨምር ያደርጋሉ።

ለከፍተኛ ትምህርት ዝግጅት የነበራቸው ታዳጊ ወጣቶች፣ ስለእርግዝናቸው፣ ወልደውም ከሆነ ስለልጃቸው፣ ከእኩዮቻቸው የሚሰነዝሩባቸውን ስድቦችን፣ ስሜት ሸንቋጭ አስተያየቶችን እና የአብሪት አነጋገሮችን የመሸከም አዳ አለባቸው። ስለሆነም፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ እናቶች የከፍተኛ ትምህርት የመከታተል ፍላጎቱም ዝግጅቱም ቢኖራቸውም፣ እነዚህን ሁኔታዎች መቋቋም ስለማይችሉ፣ ትምህርታቸውን ከመከታተል ታቅበው በህፃናቸው ላይ ለማተኮር ወይም ለማግባት ያቅዳሉ።

በጉዳዩ ዙሪያ ያጠኑ ባለሙያዎች፣ አብዛኞቹ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ለአርግዝና የተጋለጡ ሴት ልጆች፣ ትምህርት ለማቋረጥ ከሚገደዱባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋናው፣ ከጓደኞቻቸውና ከትምህርት ባልደረቦቻቸው የሚደርስባቸው የማዋረድና ትንኮሳ አዝል ትችቶች ናቸው።

በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ስለሚያጋጥሙ እርግዝናዎች በተለያዩ ጊዜያት የወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ባልተገባ እርግዝና ለእናትነት የተዳረጉ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ከሚገኙ እናቶች መካከል አንድ ሶስተኛዎቹ ብቻ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ፣ የከፍተኛ ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ የዲግሪ ምሩቃን የሚሆኑት ደግሞ እጅግ ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው።

መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ መዳረጉ፡-

በአብዛኛዎቹ በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት የሚገኙ መንግስታት፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ እናቶችን እና ልጆቻቸውን ለመደገፍ በሚል የተለያዩ የበጎ አድራጎት መርሃ ግብሮችን በመዘርጋት አንቅስቃሴ ያደርጋሉ። በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ እናቶች፣ በትምህርታቸው መግፋት ካለመቻላቸው የተነሳ በተለያዩ የገቢ ማስገኛ የሥራ መስኮች ለመሰማራት የሚያስችል ብቃት ስለማይኖራቸው፣ ወይም ዝቅተኛውን የብቃት ደረጃ ስለማያሟሉ፣ የራሳቸውንም ሆነ የወለዱትን ልጅ ፍላጎት ማሟላት የሚያስችላቸውን ገቢ ማግኘት ስለማይችሉ፣ ኑሯቸውን ለማሻሻሉ በመንግስትም ሆነ በተለያዩ በጎ አድራጊዎች በሚሰጣቸው መሰል የበጎ አድራጎት ተግባራት ላይ ሙሉ በሙሉ ጥገኛ ይሆናሉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ አሜሪካ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ በሚያጋጥሙ አርግዝናዎች የተነሳ፣ ለእናቶችና ለህፃናት ጤና እንክብካቤ ፣ አሳዳጊ የሌላቸውን ልጆች የሚንከባከቡ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ለመደገፍ፣ ባጠቃላይም ልጆች በተገቢው መንገድ በጥሩ ሁኔታ በእንክብካቤ እንዲያድጉ ለማድረግ በሚል በየዓመቱ ወደ 7 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ወጪ ታወጣለች። የአሜሪካ መንግስት የተለያዩ ድጋፎችን በተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ እናቶች ቀደም ብለን በጠቀስናቸው ምክንያቶች የተነሳ፣ ግብር ከፋይ ስለማይሆኑ፣ እንዲከፍሉም ስለማይጠበቅ መንግስት ከፍተኛ የገቢ ኪሳራም እንደሚያጋጥመው ግልፅ ነው።

ማህበራዊ ግዴታዎች፡ -

በአሥራዎቹ ዕድሜ ለእናትነት የሚጋለጡ ልጆች/ታዳጊዎች ለተለያዩ ማህበራዊ ጫናዎችና ግዴታዎች ይጋለጣሉ። የሚመጥናቸውንም የሥራ መስክ የሚያገኙበት እድል በጣም የጠበበ ነው። ከጓደኞቿቸው እና ከቤተሰቦቻቸው ጭምር ተገቢው ክብር አይሰጣቸውም። ያለእድሜዋ እና ባልተጠበቀ ሁኔታ በሚያጋጥማት እርግዝና የተነሳ ምክንያት፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የምትገኝ እናት ሙሉ ማኅበራዊ ህይወቷ ይበላሻል። እናም፣ በቀላሉ በማትወጣው በስሜት መጎዳት ውስጥ ሆና ህይወቷን ለማሳለፍ ትገደዳለች።

የገንዘብ ድጋፍ እጦት፡ -

በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የምትገኝ እናት ከወላጆቿ ወይም ከጓደኞቿ ተገቢውን የገንዘብ ድጋፍ የማታገኝ ስለሆነ፣ በከፍተኛ የገቢ እጦት ውስጥ ሆና ኑሮዋን እንድትገፋ ትገደዳለች። ከዚህ የተነሳም፣ ይህች እናት አዲስ ለወለደችው ህጻን መሰረታዊ የሆኑ ነገሮችን፣ አልባሳትን እና ለህፃናት እንክብካቤ የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ ለማሟላት ከፍተኛ ችግር ውስጥ ትገባለች ማለት ነው።

የድህነት ስጋት መጨመር፡ -

በአሥራዎቹ ዕድሜዋ ለእርግዝና በመጋለጧ ለእናትነት የተዳረገች ሴት፣ ትምህርቷን መቀጠል ያዳግታታል። ይህም፣ መሠረታዊ የሆኑ ብቃቶችን እንዳታገኝ እንቅፋት ስለሚሆንባት፣ ሥራ እንኳን ብታገኝ የሚከፈላት ክፍያ በእጅጉ ዝቅ ያለ ነው።

በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች ውስጥ ይህች እናት፣ የልጇ ተፈጥሮአዊ አባት ለልጁ እወቅና ስለማይሰጥ ወይም ራሱን ገሸሽ ስለሚያደርግ፣ ልጇን የማሳደግ ሃላፊነት በእርሷ ትከሻ ላይ ብቻ የወደቀ ስለሚሆን፣ አሷም ሆነች ልጇ በከፋ ድህነት ውስጥ ሆነው ኑሯቸውን እንዲገፉ ይገደዳሉ። ይህም ሁኔታ፣ በአሷም ሆነ በልጇ ህይወት ውስጥ ቀጣይነት ኖሮት ሊዘልቅ የሚችልበት እድል በጣም የሰፋ ነው።

በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ጥቂት እናቶች ተገቢው የትምህርት ደረጃ መማፋት የሚችሉበት ሁኔታ እንዲሁም ዝቅተኛ ደረጃ ለሚገኙ ሥራዎች ተገቢዎቹን የብቃት መመዘኛዎች ማሟላት የሚችሉበት አጋጣሚ እንኳን ቢኖርም፣ የገንዘብ አቋማቸውን ማሻሻል የሚችሉባቸውን ጥሩ ክፍያ እና ምቹ የሥራ አካባቢ ያላቸውን ሥራዎች ለማግኘት መቸገራቸው አይቀርም።

በአጠቃላይ፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚከሰት እርግዝና አብዛኛውን ጊዜ ከእናትየው ዝቅተኛ ዓመታዊ ገቢ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት አለው። ከዚህ የተነሳም፣ 80% የሚሆኑት በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ እናቶች፣ በየሀገራቸው በታቀዱ የማህበራዊ የድጋፍ ፕሮግራሞች ላይ መተማመናቸው የሰፋ ይሆናል።

የሕክምና ችግሮች፡ -

በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚከሰት እርግዝና፣ እናቲቱንም ሆነ የምትወልደውን ልጅ ለተለያዩ ከጤና ጋር ለተያያዙ ውስብስብ ችግሮች ያጋልጣል። በተለይም፣ ተገቢው የቅድመ ወሊድ ክትትልና እንክብካቤ ምርመራ ባልኖረበት ሁኔታ እነዚህ ጤና ነክ ችግሮች እጅጉን ጎልተው የሚታዩ ይሆናሉ። ብዙውን ጊዜ፣ እንደ ደም ግፊት፣ ደም ማነስ እና ያለጊዜው ልጅ መወለድን የመሳሰሉ የከፋ ጤና ነክ ችግሮች የሚከሰቱት ከዚህ የተነሳ ነው። በህክምናው ዓለም ከሚመከሩ ጉዳዮች መካከል አንዱ፣ የቅድመ ወሊድ ክትትልና እንክብካቤ ምርመራ ማድረግ ቢሆንም፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የምትገኝ እናት በተለያዩ ሰበቦች የተነሳ መደበኛ ጤና ነክ ክትትል እና ምርመራ ከማድረግ ይታቀባሉ። ይህም፣ ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው፣ እናቱቱንም ሆነ የሚወለደውን ልጅ ለተለያዩ ጤና ነክ ችግሮች የሚኖራቸውን ተጋላጭነት የበለጠ ያጎላዋል። በተለይም፣ ህፃኑ ላይ የሚከሰቱ የሕክምና ችግሮች በጣም ውስብስብ ስለሚሆኑ፣ በሚወለዱ አንዳንድ ልጆች ላይ ከእድሜ ጋር ባልተዛመደ ሁኔታ ዝቅተኛ ክብደት፣ ዓይነ ስውርነት፣ ከመስማት እና ከመተንፈስ ጋር የተዛመዱ እክሎች፣ እንዲሁም ሌሎች ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ።

የስሜት መቃወስ፡ -

ገና በለጋ እድሜዋ በማርገዝ እናት የምትሆን ልጅ፣ ከቤተሰቦዋ ልታገኝ የሚገባትን ሁለንተናዊ ድጋፍ የምታጣበት ሁኔታ ስለሚከሰት፣ ታዳጊዋ እናት ለተለያዩ ውስብስብ የስሜት ቀውሶች ትጋለጣለች። እነዚህና ሌሎች ከፍተኛ የስሜት ቀውሶች እና የአእምሮዊ መዛነፍ ምልክቶች፣ ታዳጊዋ ራሷን ለማጥፋት እንድትሞክር ወይም ያረገዘችውን ልጅ በራሷ ተነሳሽነት የማስወረድ ሙከራ እንድታደርግ እና የተለያዩ መሰል አኩይ ባህርያትን እንድታሰብ መነሻ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ይህች በአሥራዎቹ ዕድሜ ላይ የምትገኝ ታዳጊ እናት፣ ስለእርግዝናዋ ከህብረተሰቡ በሚሰነዘሩ አሉታዊ ግብረመልሶች የተነሳ ከባድ የመንፈስ ጭንቀት ውስጥ ትገባለች።

የተለያዩ ንጥረነገሮችን ያለግባብ መጠቀም/ መጋለጥ፡ -

የተለያዩ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቋቋም በሚል የሚወሰዱ ንጥረ ነገሮች፣ ከእውነታው ጋር ራስን ለማስተካከል፣ ተጨባጩን እውነታ ለመቀበል እና የውስጥ ቁስልን ለማከም ጥሩ ሊሆኑ የሚችሉበት አጋጣሚ ሊኖር የሚችልበት ሁኔታ አለ። ስለሆነም፣ ገና በለጋ እድሜያቸው በማርገዝ እናት የሚሆኑ ልጆች፣ ከማህበረሰቡ የሚመጣባቸውን እጅግ የከፋ የአለት - ተ - አለት አሉታዊ ጫና ለማርገብ ወደንጥረ ነገሮች መጠቀም ማዘንበላቸው የሚገርም አይሆንም። ጥናቶች፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ በሚከሰት እርግዝና የተነሳ ለተለያዩ አሉታዊ ጫናዎች የሚጋለጡ ታዳጊ እናቶች የተለያዩ ንጥረነገሮችን ለመጠቀም የሚገደዱበት ሁኔታ መኖሩ፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ በሚገኙ

የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኝነት ተጠቃሚዎች መጠን ላይ የራሱ የጎላ ድርሻ እንዳለው ያመለክታሉ። ከሌሎች የበለጠ ጠንክሮ መሥራት፣ -

ልጅን ማሳደግ የወላጅነት ተግባር መሆኑ ቢታወቅም፣ ልጅን በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ በሚኖር አርግዝና የምታሳድግ ታዳጊ እናት፣ በተለያዩ ማህበረሰባዊ ጫናዎች የተነሳ ልጇን ያለ ምንም ድጋፍ እና አይዘሽ ባይነት የማሳደግ ትግሏ በከባድ ፈተና ውስጥ ሆኖ የምታልፈው በቀጣይ የህይወት ጉዞዋ ውስጥም ለብዙ መዘዞች የሚያጋልጣት መሆኑ ግልፅ ነው። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ፈታኝ ሁኔታዎች ይህችን እናት እንደአለት የሚያጠነክሯት፣ ፈተናዎችን የመቋቋም የደነደነ ትከሻ እንዲኖራት እና ጠንክራ እንድትሠራ ተነሳሽነት እንዲኖራትም የሚያደርጓት ይሆናል።

ለአሉታዊ አስተያየት መጋለጥ፣ -

ህብረተሰቡ፣ ብዙውን ጊዜ በአሥራዎቹዕድሜውስጥየሚከሰትን አርግዝናን እንደ ማህበራዊ ችግር ይቆጥረዋል። እናም፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ በሚኖር አርግዝና የተነሳ ወላጅ የሚሆኑ ልጆች፣ ከአካባቢያቸው ሰዎች ለከፍተኛ የማዋረድና እና አሉታዊ አስተያየት የተጋለጡ ናቸው። በህብረተሰቡ ዘንድ ማህበራዊ መገለል ይደርስባቸዋል፤ ከማህበረሰቡ ወግ እንዳፈነገጡ ተቆጥረውም ህብረተሰቡ ይጠየፋቸዋል፤ መጥፎ ስም ይሰጣቸዋል። ስለሆነም፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ እናቶች፣ እነዚህን ሁሉ ማህበረሰባዊ መገለሎች የመጋፈጥ ሸክም አለባቸው።

ራስን የማጥፋት ምጣኔ መጨመር፣ -

በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ያሉ እናቶች፣ ከማህበረሰቡ በሚደርስባቸው የማዋረድና እና የማሸማቀቅ ተግባር፣ እንዲሁም የማህበራዊ ድጋፍ እጦት የተነሳና በሚደረሱባቸው የተለያዩ የመንፈስ ጭንቀቶች የተነሳ አራሳቸውን በራሳቸው ለማጥፋት በጣም በከፍተኛ ደረጃ ይገፋፋሉ።

በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ በሚገኙ እናቶች ዘንድ ራስን ለማጥፋት ከሚዳርጉ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ስሜታዊ ውጥረት፣ የገንዘብ ቀውስ እና በህብረተሰቡ የሚደረግ መገለል እንደ ዋና ዋና ምክንያቶች ተደርገው ከሚጠቀሱ ውስጥ ይገኙበታል።

ምንጭ፣ - ሳዲያ ቀመር፣ ሰኔ 20 ቀን 2022 ዓ.ም.

የፋዌ - ኢትዮጵያ ንዑስ ቻፕተሮች ዓመታዊ ሪፖርት (2013 - 2014 / 2022 ዓ.ም.)

ፋዌ - ኢትዮጵያ፣ በተለያዩ የሃገራችን ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት ንዑስ ቻፕተሮችን በማቋቋም፣ በሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ይበልጥ ማሰፋት የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል። ፋዌ - ኢትዮጵያ በእስካሁኑ ሂደት ላስመዘገባቸው ውጤታማ ተግባራት፣ የእነዚህ ንዑስ ቻፕተሮች መቋቋም የነበረው አስተዋፅኦ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፣ በተለይም፣ ፋዌ - ኢትዮጵያ በተለያዩ የሃገራችን ክፍሎች ያሉ ሴት ተማሪዎችን ሁለንተናዊ ችግሮች በቅጡ በመረዳት ዓላማውን መሰረት ያደረጉ ተግባራትን ተደራሽ እንዲያደርግ የንዑስ ቻፕተሮቹ ድርሻ ከፍተኛ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ፣ የየአካባቢው ህብረተሰብ፣ የፋዌ - ኢትዮጵያን ራዕይና ግብ በተመለከተ ተገቢው ግንዛቤ እንዲኖረውና ለዓላማው ስኬትም የበኩሉን ሚና በተለያየ መልኩ መጫወት እንዲችልና የፋዌ - ኢትዮጵያ የድጋፍ መሰረትም እንዲሰፋ አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥረዋል።

የፋዌ - ኢትዮጵያ ንዑስ ቻፕተሮች፣ በ2014 በጀት ዓመት አቅዳቸው መሰረት የተለያዩ ተግባራትን አከናውነዋል። የተግባራቱን የአፈፃፀም ሁኔታ የተመለከተ ሪፖርትም፣ መጋቢት 22 ቀን 2014 ዓ.ም. ለተከናወነው የፋዌ - ኢትዮጵያ ዓመታዊ ጉባዔ አቅርበዋል። ንኡስ ቻፕተሮቹ፣ በተወካዮቻቸው አማካይነት ያቀረቡት ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፋዌ - ኢትዮጵያ ንኡስ ቻፕተር

የሲዳማ ብ/ክ/መንግስት የፋዌ - ኢትዮጵያ ንኡስ ቻፕተር ጊዜያዊ ጽ/ቤት አስተባባሪ ወ/ሮ ሙሉ ኪዳኔ፣ የንኡስ ቻፕተራቸውን የሥራ እንቅስቃሴ የተመለከተ ዓመታዊ ሪፖርት፣ በዓመቱ ከተያዙት ዋና ዋና ግቦችና ከተከናወኑ ተግባራት አኳያ አቅርበዋል። የሪፖርቱ ዋና ዋና ይዘቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የነፃ ትምህርት እድል ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች ተጠቃሚነት 100% ተሳክቷል። በመሆኑም፣ የሶስተኛ እና የአራተኛ ዙር የነፃ ትምህርት እድል ተጠቃሚ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርስቲ እንዲገቡ የተያዘውን እቅድ ማሳካት ተችሏል። እነዚህን ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርስቲ የመሸኘት ፕሮግራም በማዘጋጀትም፣ የፋዌ - ኢትዮጵያ "ከገርል ፓወር እስከ ማስተር ካርድ ስኮላርሽፕ" ድረስ ባከናወናቸው ተግባራት ያስመዘገባቸውን ስኬቶች የተመለከተ ገለፃ ተሰጥቷል። እንዲሁም፣ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ቆይታቸው ወቅትም ሆነ ከዚያ በኋላ ከእነሱ ስለሚጠበቁ የተለያዩ አካዳሚዊና ማህበራዊ ሃላፊነቶች፣ በተለይም ለሚደረግላቸው በጎ ተግባር ሁሉ እነሱም በበኩላቸውን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው፣ ይህንንም ባህል ማድረግ እንደሚገባቸው፣ ባጠቃላይም ህዝባዊ፣ ወገናዊ፣ ሃገራዊ ባለደራነታቸውን ምንጊዜም መዘንጋት እንደሌለባቸው ግንዛቤ መፍጠር ተችሏል።

የነፃ ትምህርት እድል ተጠቃሚ ተማሪዎችን ሁለንተናዊ እርካታ (ከትምህርትና ከግብዓት አንፃር) በተመለከተ 100% ማሳካት ተችሏል። በዚህም መሰረት፣ -

- በፋዌ - ኢትዮጵያ ማስተር ካርድ የነፃትምህርት እድል በመጠቀም ዩኒቨርስቲ ገብተው ትምህርታቸውን አጠናቀው ለመጡ ተማሪዎች፣ ተቋማት እንዲቀጥሯቸው የድጋፍ ደብዳቤ የመስጠትና ክትትል የማድረግ ተግባር ተከናውኗል።
- የተለያዩ ስልጠናዎችን ሲሰጡ ክትትል በማድረግ፣ ስልጠና ሲጠናቀቅም በማጠቃለያ ፕሮግራም ላይ በመገኘት፣ በየሂደቱም ተማሪዎች ያገኙትን ሁለንተናዊ ድጋፍና ለቀጣይ መሰል ተግባራትም ግብዓት የሚሆኑ ነገሮችን መሰብሰብ ተችሏል። የመጨረሻው ዙር የነፃ ትምህርት እድል ተጠቃሚ ተማሪዎችን መረጃ በማሰባሰብና በማደራጀት፣ ከዋናው የፋዌ - ኢትዮጵያ ጽ/ቤት ለሚመጣው ቡድን ምቹ ሁኔታን መፍጠርና የቡድኑ ተልእኮም ውጤታማ

እንዲሆን አቅም የፈቀደውን ሁሉ በማድረግ ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል።

•የነፃ ትምህርት እድል ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎችን በተመለከተ፣ ትምህርትቸውን በሚከታተሉባቸው ትምህርት ቤቶች፣ በትምህርት አሰጣጥ፣ በቱቶሪያል አተገባበር፣ ለተማሪዎች በሚሰራጩ የትምህርት፣ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ ስርጭትን እንዲሁም ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር ባላቸው መስተጋብር ዙሪያ ተገቢውን ድጋፍን ክትትል ማድረግ ከመቻሉም በላይ፣ የስኮላርሺፑን አተገባበር በተመለከቱ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ከተጠቃሚ ተማሪዎችና ከየትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር ጠቃሚ ውይይቶች ተካሂደዋል።

•በየወቅቱ በሚደረጉ የስኮላርሺፕ ፕሮግራሙ አፈፃፃም ግምገማ ሂደት፣ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር ወቅታዊ ግንኙነት መፍጠር ተችሏል።

•በመንግስት በኩል፣ ሴት ተማሪዎች በትምህርት ዙሪያ ልዩ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው በመገንዘብ ሥርዓት በመዘርጋት፣ ባለቤትም በመስጠት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ እንደሆነ ይታወቃል። ይህንን የመንግስት ፖሊሲ ከማጠናከር አንፃር፣ የክልሉ የፋዌ-ኢትዮጵያ ንኡስ ቻፕተር አመራሮችና አባላት በሚገኙባቸው ትምህርት ቤቶች ይህ ለሴት ተማሪዎች የሚደረግ የትምህርትና መሰል ልዩ ልዩ ድጋፎች፣ በተሻለ ሁኔታ እንዲከናወኑ የበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል።

•በተለያዩ ጊዜያት ከዋናው ጽ/ቤት ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት፣ ጽ/ቤቱ በክልሉ ለሚተገብራቸው የተለያዩ ተግባራት ተገቢው የድጋፍ ተግባራት ተከናውነዋል፤ ምቹ ሁኔታዎችም ተፈጥረዋል።

•የተማሪዎችን አጠቃላይ የትምህርትና ሥነምግባር ሁኔታዎችን ከማሻሻል አኳያ፣ ከተማሪ ሜንተሮች፣ ከበጎ ፈቃድ አስተባባሪዎችና ከየትምህርት ቤቱ ርእሰመምህራን ተገቢውን ግንኙነት በመፍጠር፣ በተለያዩ መንገዶች ክትትል የማድረግ ተግባር እየተከናወነ ይገኛል።

አማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፋዌ-ኢትዮጵያ ንኡስ ቻፕተር

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተቋቋመው የፋዌ-ኢትዮጵያ ንኡስ ቻፕተር፣ በዓመቱ የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል። በመሆኑም፣ ቅርንጫፍ ንኡስ ቻፕተር ኢረሐ ከተባለ መንግስታዊ ካልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር፣ በየትምህርት ቤቱ ለሚገኙ ሴት ተማሪዎች ለቀጣይ ህይወታቸው የሚጠቅሟቸውንና ከሥራ ባህል ማዳበር ጋር የተዛመዱ፣ በራስ የመተማመን መንፈሳቸውን የሚያጠናክሩ ርእሰጉዳዮችን የተመለከቱ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል።

•በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ የንፅህና መጠበቂያ ሞዴሶች ስርጭት ተከናውኗል።

•የችግረኛ ቤተሰብ ለሆኑ ሴት ተማሪዎች፣ የትምህርት ቁሳቁስና የትምህርት ቤት የደንብ ልብሶች ተሰጥተዋል።

•በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች፣ ከ7ኛ-8ኛ ክፍል ከሚማሩ ሴት ተማሪዎች ውስጥ ልዩ እገዛ የሚያስፈልጋቸውን በመምረጥ፣ በ"PINC GIRLS" አስተባባሪነት የቀለም ትምህርት እገዛ እንዲያገኙ ተደርጓል።

•በሁሉም ትምህርት ቤቶች፣ እድሜያቸው ከ9-14 ላሉ ሴት ተማሪዎች የህይወት ክህሎት ስልጠና ተሰጥቷል።

•በባህርዳር ዩኒቨርስቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተማሪዎች፣ የሞዴስ መቀየሪያ ክፍል ማመቻቸት ተችሏል። በክፍሉ ውስጥ የማረፊያ ፍራሽ እና መታጠቢያ በማዘጋጀት፣

•የሞዴስ መቀየሪያ ግብዓቶችን በማሟላት ረገድም አስፈላጊው እገዛ በመደረግ ላይ ነው።

•በሃገራችን በተከሰተው የሰላም እጦት የተነሳ፣ በተለይም በአማራ እና በአፋር ክልሎች ብዙ ትምህርት ቤቶች ስለወደሙ፣ በዚያ ይማሩ ከነበሩ ሴት ተማሪዎች ውስጥ የተወሰኑትን ሰላም ወደአለበት አካባቢ በማምጣትና ተቀባይ ቤተሰብ በማመቻቸት፣ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች እንዲቀበሏቸውና ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ እየተደረገ መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ሂደት ውስጥ፣ ንዑስ ቻፕተራችን የአለባሳት፣ የየትምህርት ቤቶቹን ማህበረሰብ እና ሌሎች አርዳታ ሰጪ አካላትን በማስተባበር የተለያዩ የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ እገዛ እያደረገ ይገኛል።

•የዓለም የሴቶች ቀንን "ማርች 8"፣ በየትምህርት ቤቶቹ ተከብሮ መዋሉን መነሻ በማድረግ፣ በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል ግጭት የተነሳ ለተፈናቀሉ ተማሪዎች አርዳታ በማሰባሰብ እና በተለያዩ ርእሰጉዳዮችም በባለሙያ የታገዘ ስልጠና በማመቻቸት ተከብሮ እንዲውል ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪም፣ በአለቱ የተካሄደውን ስልጠና መነሻ በማድረግ፣ የኮረና ቫይረስ ያደረሰብንን ጉዳት የተመለከተ የግንዛቤ ሥራ በመሥራት፣ ከ12 ዓመት በላይ የሆኑ ተማሪዎች ዛሬ ነገ ሳይሉ መከተብ እንዳለባቸው፣ ያልተከተቡ ቤተሰቦቻቸውም አካባቢያቸው ወደሚገኙ ጤና ጣቢያዎች በመሄድ ክትባቱን እንዲወስዱ የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ቅስቀሳ ተካሂዷል።

•እንደሚታወቀው፣ አማራ ክልል ከሰሜኑ የሃገራችን ግጭት የተነሳ በብዙ ችግሮች ውስጥ ላይ የነበረ እንደመሆኑ፣ ከእዚህ በላይ በተጠቀሰው መሰረት ለተፈናቃይ ተማሪዎች በተካሄዱ የተለያዩ የድጋፍ አሰባሰብ ሂደቶች ውስጥ፣ በንኡስ ቻፕተራችን አስተባባሪነት ሴት መምህራን ህብረተሰቡን በማስተባበር በኩሉ ከፍተኛ ሥራ ሠርተዋል። ንኡስ ቻፕተራችን፣ ከእነዚሁ መምህራን ጋር በመተባበር፣ ቁስለኛ ለሆኑ ወገኖች ምግብ በማዘጋጀትና አልባሳት በማሰባሰብ ሆስፒታል ድረስ በመሄድ ቁስለኞችን በመንከባከብ ላይ ይገኛል። እንዲሁም፣ ከተለያዩ አካላት የተለያዩ የአርዳታ ቁሶችን በማሰባሰብ ግንባር ድረስ በመሄድ /በመገኘት የማድረስ ሥራ ሠርቷል፤ ቁስለኛ ወታደሮችን በማበረታታት እና በማገዝ የሚፈለገውን አርዳታ በተለይ በፋዌ ጽ/ቤት አባላት ግንባር ቀደምትነት ጥረት ተደርጓል። ወደፊትም ለሚከሰቱ መሰል ችግሮች ሁሉ ወደኋላ እንደማንል የንኡስ ቻፕተራችን አባላት አቋም ወስደናል።

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋዌ-ኢትዮጵያ ንኡስ ቻፕተር (ደራርቱ ቱሉ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት)

በደራርቱ ቱሉ ሁለተኛ ደራጃ ትምህርት ቤት የፋዌ-ኢትዮጵያ ስኮላርሺፕ ፕሮግራምን መሰረት በማድረግ፣ በ2013-2014 ዓ.ም. ተማሪ ተኮር የሆኑ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። እነዚህን ተግባራትንና ያጋጠሙ ችግሮችን ከእነመፍትሄያቸው የያዘው ዓመታዊ ሪፖርት፣ በወ/ሮ ቅድስት ንጉሤ፣ የደራርቱ ቱሉ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት መሻሻል ምክትል ርእሰ መምህርት አማካይት ቀርቧል። የሪፖርቱ ይዘት እንደሚከተለው ቀርቧል።

•በአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር፣ በአቃቂ ቃልቲ ክፍል ከተማ ወረዳ 8 ውስጥ የሚገኘው የደራርቱ ቱሉ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለተማሪዎች ምቹ የመማር ሁኔታ በመፍጠር፣ ብዙ ውጤታማ ተማሪዎችን ማፍራት የቻለ ትምህርት ቤት ነው። ትምህርት ቤቱ፣ በ2014 ዓ.ም. የትምህርት ዘመንም 1076 ወንድና 12204 ሴት ተማሪዎችን፣ በድምሩም 2300 ተማሪዎችን በመቀበል የቀለም ትምህርት የሰጠ ሲሆን፣ በተለይም ለሴት ተማሪዎች የተለያዩ ድጋፎችንና ማበረታቻዎችን በማድረግ፣ ተማሪዎቹ በትምህርታቸው ውጤታማ ሆነው እንዲዘልቁ የማድረግ ጥረት በማደረግ ላይ ይገኛል።

ፋዌ-ኢትዮጵያ፣ ደራርቱ ቱሉ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን መሰረት በማድረግ፣ በትምህርት ቤቱ በቷቋቋመው የሥርዓተ ጾታ ክበብ አማካይት ከ2013 ዓ.ም. ሁለተኛ መንፈቅ ዓመት እስከ 2014 ዓ.ም አንደኛ መንፈቅ ዓመት የትምህርት ዘመን መጨረሻ ድረስ፣ የፋዌ-ኢትዮጵያን ዓለማዎችን መሰረት ያደረጉ ከዚህ በታች የተገለፀ ተግባራት ተከናውነዋል።

•በትምህርት ቤቱ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት 11 ወንድና 14 ሴት ተማሪዎች በድምሩም 25 ከፍተኛ የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን በመለየት፣ እነዚህ ተማሪዎች በምግብ ማጣት ምክንያት ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ማድረግ ተችሏል።

•ከእነዚህ 25 ተማሪዎች ውስጥ፣ 9 ወንዶችና 11 ሴት ተማሪዎችን በድምሩም 20 ተማሪዎችን የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በየቀኑ ከደሞዙ ላይ በሚያዋጣው 20 ብር፣ እንዲሁም፣ በማህበራዊ አገልግሎት ክበብ ተጠሪ አለቆች አማካይነት በወላጆች ስብሰባ ወቅት ከወላጆች አለታዊ መዋጮ በመሰብሰብ (በየወሩ እስከ ብር 5000/አምሰት ሺህ ብር) ለካፍቴሪያ አገልግሎት በመክፈል፣ እነዚህ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ውስጥ የምሳ ድጋፍ እንዲያገኙ ሲደረግ፣ ቀሪዎቹ 5 ተማሪዎች ደግሞ በአንድ በጎ ፈቃደኛ ግለሰብ አማካይት ወጪያቸው እየተሸፈነ በየእለቱ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ምሳ እንዲመገቡ በመደረግ ላይ ይገኛል። ከእነዚህ ተማሪዎች አንዷ የሆነችው እና በእድሜዋም አነስተኛ የሆነችው ተማሪ፣ በትንሽ አድሜዋ ለቤተሰቧ ጭምር የምታስብና የምትጨነቅ መሆኗን በመረዳት፣ ወ/ሮ ሳራ ከተባሉ አንዲት በጎ አድራጊ ግለሰብ ጋር አንድትገናኝ በማድረግ ለተማሪዋ እናት በሶስት ወር አንዴ የ1000 ብር ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል፤ በተጨማሪም የአልባሳት ድጋፍ እንድታገኝ ተደርጓል።

•ሴት ተማሪዎች፣ በወር አበባ ምክንያት በትምህርታቸው ላይ የሚፈጠረውን ተፅእኖ ለመቀነስ፣ ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ላይ እያሉ ለሚከሰት የወር አበባ በየእለቱ የሞይስ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። በተጨማሪም፣ በየወሩ ሞይስ ለመግዛት አቅም ለሌላቸው ተማሪዎች የአጠቃቀም ስልጠና በመስጠት "ስቱዲዮ ሳሙኤል" በተባለ የግል ድርጅት አማካይነት የሚታጠብ የሞይስ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። በወር አበባ ወቅት በከፍተኛ ህመም የሚሰቃዩ ተማሪዎችን በመደገፍ በኩል፣ ልዩ የማረፊያና ክፍልና የህመም ማስታገሻ መድሃኒቶች እንዲያገኙ ተደርጓል።

•የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች፣ በተለይም ሴቶች፣ በግንዛቤ እጥረት ምክንያት፣ ለተለያዩ የጤና፣ የስነልቡና እና ማህበራዊ ችግሮች እንዳይጋለጡ ለመከላከል፣ ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አምስተኛ ዓመት የህክምና ተማሪዎች ጋር እና እንዲሁም ሰፕላሽ ኢትየጵያ በተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት በተገኘ ድጋፍ፣ የሰርዓተ ጾታ ክበብ አባል የሆኑ ተማሪዎች በተለያዩ የስነተዋልዶ ጤና ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል።

•የሴት ተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት ለማበልፀግና የመሪነት ሚናቸውንም ለማሳደግ፣ የዶታ ተዋፅኦን ባመጣጠነ መልኩ በትምህርት ቤቱ የተለያዩ ምርጫዎች እንዲካሄዱ የሚያስችል ሥራ ተሠርቷል። በዚህም መሠረት፣ በትምህርት ቤቱ ባሉ 42 መማሪያ ክፍሎች የተማሪ ተወካዮች ምርጫ የተካሄደ ሲሆን፣ ከ42 የየክፍሉ ተወካዮች ውስጥ 21ዱ ሴቶች መሆን ችለዋል። እንዲሁም፣ ከ7 የተማሪዎች መማክርት ሥራ አስፈፃሚዎችም 4ቱ ሴቶች ሆነዋል። በተለያዩ ክበባትና አደረጃጀቶችም የሴቶች ተሳትፎ የጎላ እንዲሆን ለማድረግ ተችሏል።

•በየክፍሉ ከሚገኙ የደረጃ ተማሪዎች (TOP TEN STUDENTS) ውስጥ፣ 85% የሚሆኑት ሴት ተማሪዎች ናቸው።

•የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች እርስ በእርስ የመደጋገፍ እና የመረዳዳት ባህልን እንዲያጎለብቱ ከማድረግ አንፃር፣ ተማሪዎች በጦርነት ምክንያት ተፈናቅሎ የመጣን አንድን ተማሪ ለመደገፍ የበኩላቸውን እርዳታ የማሰባሰብ ሥራ አከናውነዋል። በመሆኑም፣ በድጋፉ አማካይነት የተማሪውን የምሳ ወጪ መሸፈን እና የሁለት ወር የቤት ኪራይ መክፈል ተችሏል። ተማሪው ወደአካባቢዬ መመለስ እፈልጋለሁ ባለ ጊዜም፣ የትራንስፖርት ወጪውን በመሸፈን ወደአካባቢው እንዲመለስ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች አድርገዋል። እንዲሁም፣ ተማሪዎች በቀይመስቀል ክበብ በመደራጀት፣ በትምህርት ገበታ ላይ ራሳቸውን ስተው የሚወድቁ ተማሪዎችን (በአብዛኛው ወይም ሁሉም በሚባል ደረጃ ሴቶች ናቸው) ተማሪዎችን ተሸክመውና ደግፈው ወደማረፊያ ክፍል በመውሰድና የከፋ የጤና ችግር የደረሰባቸውን ተማሪዎችንም በአንቡላንስ ወደህክምና ተቋማት በማድረስ፣ የህክምና ወጪያቸውን እስከመሸፈን በሚደርስ ድጋፍ እርስ በእርስ የመረዳዳት ተግባር ፈፅመዋል። እነዚሁ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ በተለያየ ችግር እርዳታ ፈልገው ወደትምህርት ቤቱ የሚመጡ ሰዎችን ካላቸው ላይ በመቀነስ፣ በገንዘብም በጉልበትም ከሌሎች የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በበለጠ ሁኔታ እገዛ ያደርጋሉ።

•ከዚህ በፊት በፋዌ-ኢትዮጵያ ስኮላርሺፕ ፕሮግራም አማካይነት፣ በትምህርት ቤቱ የኢኮኖሚ ድጋፍ እየተደረገላቸው ተምረው ወደከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከገቡ ተማሪዎች ውስጥ፣ በፋዌም ሆነ በተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች የሚደረገው ድጋፍ የተቋረጠበት በመሆኑ የተነሳ ትምህርቱን ለመቀጠል ላቻለ አንድ ተማሪ፣ ወ/ሮ ሳራ ሃይሌ በተባሉ በጎ አድራጊ ግለሰብ አማካይት የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኝ ተደርጓል። ተማሪው ባገኘው በዚህ ድጋፍ፣ በአንድ ኮሌጅ ውስጥ ነፃ የትምህርት እድል በማግኘቱ በአካውንቲንግ ትምህርት ዘርፍ እየተማረ የሚገኝ ሲሆን፣ ድግሪውን ለመያዝም በመጨረሻው የትምህርት ዓመት ላይ ይገኛል።

ሐረሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፋዌ-ኢትዮጵያ ንኡስ ቻፕተር

የሐረሪ ብሄራዊ ክ/መ የፋዌ-ኢትዮጵያ ንኡስ ቻፕተር፣ በተለያዩ ምክንያቶች ባጋጠሙ የተለያዩ ሳንካዎች የተነሳ በ2013-2014

ዓ.ም. ያን ያህል አመርቂ ሥራዎች ተሠርተዋል ባይባልም፣ የፋዌ-ኢትዮጵያን ዓለማ ያደረጉ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። ከእነዚህም መካከል፡-

•በዚህ ዓመት መጀመሪያ ላይ፣ በክልሉ በሚገኝ አንድ ትምህርት ቤት የተወሰኑ ሴት ተማሪዎችን መማሪያ ደብተር እንደሚያስፈልጋቸው በመረዳት፣ በንኡስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤታችን ስም ደብተሮችና እስክሪብቶዎች ማሟላት ተችሏል።

•በሐረር ከፍተኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት "ተማሪዎችና ኤችአይቪ ኤድስ" በሚል ርእስ የተካሄደውን ትምህርታዊ ፕሮግራም መነሻ በማድረግ፣ ጽ/ቤታችን "ሴቶችና ኤችአይቪ" በሚል ርእስ የዋናው ፋዌ-ኢትዮጵያ መልእክት ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግ ተችሏል።

•በዚሁ በሐረር ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የሴቶች ላይቭረሪ ውስጥ የፋዌ-ኢትዮጵያ መልእክት የያዘችውን "ትማር" የተሰኘችውን መፅሄታችን እንዲገኝ በማድረግ፣ ተማሪዎች ስለፋዌ-ኢትዮጵያ ተገቢው ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ የሚቻልበትን እድል መፍጠር ችለናል።

•በሴት ክበባት ውይይት ላይ በመገኘት፣ ለሴት ልጆች መማር ፋዌ ኢትዮጵያ የሰጠውን ትኩረት፣ እንዲሁም ዓለማውን እና ተግባሩን የተመለከተ የማሳወቅ እና ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ተሰርቷል።

•በተለምዶ አንድ የሚደረግ ተግባር አለ። ይኸውም፣ ከ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን የሚያጠናቅቁ ሴቶች የትምህርት ቤት የደንብ ልብሶችን በመሰብሰብ፣ በቀጣይነት ሁለተኛ ደረጃ የሚገቡ ሴት ተማሪዎች በዩኒፎረም እጦት የተነሳ ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ የተሰበሰቡትን ዩኒፎርሞች በመስጠት፣ ትምህርታውን እንዲቀጥሉ የማድረግ ባህል አሁንም እንዲቀጥል በማድረግ ረገድ የበኩላችንን ሚና ተጫውተናል። በዚህም መሰረት፣ ዘንድሮም ይህ መልካም ተግባር ቀጥሎ፣ በንኡስ ቻፕተራችን ስም የደንብ ልብሶቹ ተሰብስበው ለተጠቀሱት ችግረኛ ተማሪዎች እንደሰጣቸው እና እነዚሁ ችግረኛ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ተደርጓል።

ኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፋዌ-ኢትዮጵያ ንኡስ ቻፕተር

የፋዌ-ኢትዮጵያ ኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ንኡስ ቻፕተር፣ በተለይ በአዳማ ከተማ በሚገኙ ስምንት መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በ2 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንቅስቃሴ የሚያደርግ ቢሆንም፣ የእነዚህን ትምህርት ቤቶች በጎ ተሞክሮዎችን መሰረት በማድረግ፣ እንደ ሃገር አቀፍ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች እና በማህበረሰብ ደረጃ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል። በመሆኑም፣ በዚሁ በአዳማ ከተማ ትምህርት ቤቶች ከተቋቋሙ ክበባት ጋር በመሆን፣ ለሴት ተማሪዎች በሚደረገው ሁለንተናዊ የድጋፍ እንቅስቃሴ ውስጥ ጽ/ቤቱ በተለያዩ ሥራዎች ተሳትፎ በማድረግ የሀሳብና የምክር አገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል። ስለሆነም፣ በፋዌ-ኢትዮጵያ ኦሮሚያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል በዓመቱ የተከናወኑ ተግባራትን የተመለከተ ዓመታዊ ሪፖርት የንኡስ ቻፕተሩ አስተባባሪ በሆኑት በወ/ሮ ምሳነሽ አሰፋ በኩል እንደሚከተለው ቀርቧል።

•በየትምህርት ቤቱ ለሴት ተማሪዎች የሴት ንፅህና መጠበቂያ ማቴሪያል/ሞዴስ የማቅረብ/የማዘጋጀት አገልግሎት ተሰጥቷል። እንዲሁም፣ ሴት ተማሪዎች በመማር ላይ አያሉ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሚያጋጥማቸው ድንገተኛ ችግር የተነሳ ልብሳቸው ሊቆሽሽ መቻሉን ታሳቢ በማድረግ፣ ፋዌ በሚንቀሳቀስባቸው ትምህርት ቤቶች ከ10 ያላነሰ የተማሪ የደንብ ልብሶችን ዝግጁ እንዲሆኑ ተደርጓል። በዚህም፣ ሴት ተማሪዎች ባጋጠማቸው ችግር ምክንያት ሳይሳቀቁ ልብሳቸውን በመቀየር ትምርታቸውን በወጉ እንዲከታተሉ የሚችሉበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር ተችሏል።

•ሴት ተማሪዎችን ለማብቃት፣ የሴት ክበባበት አባላት የሆኑ ሴት ተማሪዎች በክበባቱ አማካይነት በሥነምግባር፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ጋር በተያያዙ የተለያዩ ጉዳዮች እና በሥነተዋልዶ ዙሪያ ውይይት ያደርጋሉ፣ ምክሮችንም ይለዋወጣሉ። የውይይት መድረኮቹ፣ ሴት ተማሪዎች በራሳቸው ችግሮች ዙሪያ ያለፍርሃት እንዲወያዩ አመቺ ሁኔታዎችን ከመፍጠራቸውም በላይ፣ በተለያዩ ርእሰጉዳዮች ዙሪያ የልምድ መለዋወጫ እና የእርስበእርስ መወያያ መድረኮች በመሆን አገልግለዋል፤ ለአቅም ማጎልበቻነትም ዓይነተኛ ሚና ተጫውተዋል።

•ለችግረኛ ተማሪዎች የደብተር እና የስክሪብቶ እንዲሁም የቦርሳ እገዛ ተደርጓል። በተጨማሪም፣ በቤት ውስጥ በጣም ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት በየወሩ የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል።

•ሴት ተማሪዎች፣ አራሳቸውን መርዳት እንዲችሉ እና ልምድ እንዲኖራቸው ወርሃዊ መዋጮ እንዲያደርጉ እና ከራሳቸው ባሻገርም ችግረኛ የሆኑ ተማሪዎችን የመርዳት ባህል እንዲያዳብሩ በተለያዩ ክበባት በተለይም በሴት ክበባት አማካይነት ጥረት ተደርጓል፤ ውጤትም ተገኝቶበታል።

•በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች፣ ሴት ተማሪዎች የቤተመጸህፍት ክበባቸውን በጥንካሬ በመምራት የቤተመጸህፍት አገልግሎት አሰጣጡ እንዲሻሻል ማድረግ ተችሏል።

•ሰርዓተ ጾታ በተመለከተ ግንዛቤ ለመፍጠር፣ ወንዶችን ባሳተፈ መልኩ የአቻ ውይይቶች እንዲካሄዱ የሚያስችል ሥራ ተሠርቷል።

•በትምህርት ውጤታቸው ከ1-3ኛ የወጡ ሴት ተማሪዎች፣ ለወደፊቱ የበለጠ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እና ለበለጠ ውጤት እንዲነሳሱ ለማድረግ በማሰብ የሽልማት ፕሮግራም ተካሂዷል።

ህፃናትን ከወሲባዊ ጥቃት ለመከላከል

ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወሲባዊ ጥቃቶች፣ የሚያስከትሏቸው ጉዳቶች ምንድን ናቸው?

በአንድ ጥናታዊ ጽሁፍ እንደተገለፀው፣ በህጻንነት እድሜያቸው የወሲብ ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች ምንም እንኳን የአዕምሮ ህክምና እርዳታ ቢደረግላቸውም፣ የሚከተሉት ችግሮች ይታይባቸዋል ብለዋል።

የድርጊቱ ሰለባ የሆኑ ህፃናት ከሚስተዋልባቸው የጤናና የባህርይ ችግሮች መካከል ሱሰኝነት፣ ድብርት፣ የአባላዘር በሽታ፣ ያለአድሜ ያልተፈለገ እርግዝና፣ ሴትኛ አዳሪነት፣ ለተደጋጋሚ የወሲብ ጥቃት የመጋለጥ፣ ከትምህርት የመፈናቀል፣ ጋጠወጥነት፣ አይናፋርነትና ተናዳጅ መሆን፣ በህይወት ተስፋ የመቁረጥና ራስን የማጥፋት ስሜት፣ በሥራዎች ሁሉ ምርታማ ያለመሆን፣

በቀለኝነት፣ ግብረሶዶማዊነት፣ የከፋ በሽተኛ የመሆን፣ እየከፋም ሲሄድ ለሞት መዳረግ ይገኙባቸዋል።

በህፃናት ላይ ጥቃት የሚፈፅሙ እነማን ናቸው?

ዘመዶች (የአጎት፣ የአክስት ልጅ፣ አያት)፣ የእድሜ አቻዎቻቸው፣ እንግዶች በተለይ ከፍተኛውን አዳጋ የሚያመጡት ታማኝና ጥሩ የሚባሉት ሰዎች፣ የሴት ወይም የወንድ ጓደኛ መስለው የሚመጡ ግለሰቦች፣ ጎረቤቶች፣ ሥራቸው ከህፃናት ጋር የሚያገናኛቸው ሰዎች ዋነኞቹ ጥቃት አድራሾች እንደሆኑ ጥናቶች ይጠቁማሉ።

ወሲባዊ ጥቃት አድራሾች ለምን ጥቃቱን ይፈፅማሉ?

አንዳንድ አዋቂዎች የበላይነት ስለሚሰማቸው፣ በልጅነት ጊዜ የተፈፀሙ ወሲባዊ ጥቃት ትዝ ሲላቸው ወይንም ብሶት ስላለባቸውና በተለይ በተመሳሳይ ጾታ የተደፈሩ ከሆኑ፣ እነሱም ሲያድጉ ያንኑ ዓይነት ጥቃት በሌሎች ላይ ለመፈፀም እንዲገፋፉ ያደርጋቸዋል።

በተጨማሪም፣ የአደንዛዥ እፅ ወይም መጠጥ ተጠቃሚ መሆን፣ በልጅነት የደረሰ መገለል፣ በሀመምና በሞት የትዳር አጋርን ማጣት፣ ከሥራ አሊያም ከሌላ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በድንገት የሚፈጠር ቅርበትና የመሳሰሉት አጋጣሚዎች፣ ሰዎችን የወሲብ ጥቃት ለመፈፀም የሚያነሳሱ ምክንያቶች እንደሆኑ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

ወሲባዊ ጥቃቶችን የሚያደርሱ ግለሰቦች የጥቃት ስልቶች ምንድን ናቸው?

በቃል ወይም በንግግር ማታለል ወይም ለመግባበት የተለያዩ ስጦታዎችን በመስጠት ማታለል፣ የተለያዩ የአቀራረብ ስልቶችን በመጠቀም መገፋፋት፣ አደንዛዥ እፆችን እንዲወስዱ ማድረግ፣ የአልኮል መጠጦችን እንዲጠጡ በማድረግ ማፍዘዝ፣ በሃይል ወይም በጉልበት ጥቃትን ማድረስና ሌሎች መሰል ተግባራት፣ ወሲባዊ ጥቃትን የሚያደርሱ ግለሰቦች የሚጠቀሙባቸው ዋና ዋና ስልቶች ናቸው።

ወሲባዊ ጥቃቶችን በመከላከል፣ በድጋፍና ክብካቤ ደረጃ ምን ይደረግ?

ልጆች፣ ስለችግሩ ለመናገር ስለሚያፍሩ፣ ወላጆች፣ ህብረተሰቡና የሚመለከታቸው ሁሉ በችግሩ ዙሪያ ላይ በግልፅ በመወያየት የጋራ መፍትሄ ማፈላለግ ትልቁን ድርሻ ይይዛል። ህፃናት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከተደረገ፣ ራሳቸውን ከአደጋ ለመጠበቅ ይችላሉና የሰውነት ክፍሎችን ስምና ስላላቸው አገልግሎት የህፃናትን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ማስረዳት፣ አግባብ ስላልሆኑ ግንኙነቶች፣ መነካካቶችና ጨዋታዎች ከእነምክንያታቸው ጭምር እንዲያወቁ ማድረግ፣ ችግር በሚያጋጥማቸው ጊዜም ህፃናቱ ያለስጋት እንዲናገሩ ትምህርት መስጠትና ማበረታታት ያስፈልጋል።

በሌላ በኩልም፣ ህፃናትና ትላልቅ ልጆች አንድ ላይ እንዳይተኙና በሚጫወቱበት ጊዜም ከሌሎች እይታ ውጪ እንዳይሆኑ ማድረግ ለጥንቃቄ ይረዳል። ብዙ ወላጆች፣ ለወንጀሉ ክብደት ካለመስጠት በመነጨ፣ አሊያም የተጠቂውን ህፃንና የቤተሰብን ስም አደባባይ ላለማውጣት ሲሉ አጥቂውን የማይከሱበት፣ ጥቃት አድራሾችም ወደህግ የማይቀርቡበት ሁኔታ በመኖሩ፣ ወንጀሉ በተደጋጋሚ በብዙ ህፃናት ላይ ሲፈፀም ይስተዋላል። በዚህም የተነሳ፣ በርካቶችን ለከፋ ማህበራዊ ቀውስ እየዳረገ ይገኛል። ስለዚህ፣ ድርጊቱ የህፃናቱን የወደፊት ህይወት የሚያጨልም በመሆኑ፣ ለጉዳዩ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ መሥራትና ስርዓት ማበጀት ለነገ የሚተው ተግባር አይሆንም።

ምንጭ፡- "ትውልድ" በሴቶች ፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የተዘጋጀ መጽሄት፣ መጋቢት 2005 ዓ.ም.

ቆይታ ከቀድሞ የፋዌ - ኢትዮጵያ ስኮላርሺፕ ፕሮግራም ተሳታፊዎች ጋር

ፋዌ - ኢትዮጵያ፣ ከምስረታው አንስቶ በቀረፃቸውና በተገበራቸው የተለያዩ ሴት ተማሪዎች ላይ ባተኮሩ የስኮላርሺፕ ፕሮግራሞቹ አማካይነት፣ በቤተሰቦቻቸው የኑሮ ችግር የተነሳ ከትምህርታቸው ሊስተጓጎሉ የሚችሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን በትምህርታቸው እንዲዘልቁ አስችሏል። እነዚህ ተማሪዎች፣ በስኮላርሺፕ ፕሮግራሙ ውስጥ የተመቻቹላቸውን የተለያዩ የድጋፍ ስልቶችን (ቱቶሪያሎች፣ የማጣቀሻ መጻህፍት፣ ስልጠናዎች፣ ወርሃዊ የገንዘብ ድጋፍ፣ ወዘተ.) በመጠቀም፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ከፍተኛ ለውጥ ማሳየት ችለዋል። አብዛኞቹም፣ በከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተናዎች ላይ በመቀመጥ በመግቢያ ፈተናዎቹ አስፈላጊውን ውጤት ማስመዝገብ በመቻላቸው፣ በተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን በሚገባ በመከታተል በመጀመሪያ ድግሪ ሊመረቁ ችለዋል። በተለያዩ የሥራ መስኮች በመሰማራትም፣ ሃገራቸውን በማገልገል ላይ ይገኛሉ። በመሆኑም፣ እነዚህ ተማሪዎች፣ በስኮላርሺፕ ፕሮግራሙ ተጠቃሚ መሆናቸው አሁን ለደረሱበት ደረጃ ስለነበረው ድርሻ፣ በፋዌ - ኢትዮጵያ የማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሺፕ ፕሮግራም ተጠቃሚ ከነበሩ ሁለት ተማሪዎች ጋር ትማር መጽሄት ቆይታ አድርጋለች። እንደሚከተለው ቀርቧል።

ትማር ፡- ራሳችሁን ለመጽሄታችን አንባቢዎች ብታስተዋውቁ?

ቤዛዊት ፍቃዱ ፡- የተወለድኩት በጋምቤላ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጋምቤላ ከተማ ውስጥ ነው። ቤተሰቦቼ መኖሪያቸውን ወደአዲስ አበባ እስኪቀይሩ ድረስ እዚሁ ጋምቤላ ከተማ ውስጥ ቆይቻለሁ። አዲስ አበባ መኖር ስጀምር፣ እድሜዬ ሰባት ዓመት ሆኖ ነበር። አዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎች ኖሬአለሁ። አሁን በቋሚነት የምኖረው፣ አስኮ የተባለው አካባቢ ነው። እናትና አባቴ/ቤተሰቦቼ፣ ለትምህርት የተለየ ትኩረት የሚሰጡ ናቸው። የማንበብ ፍቅር ያሳደሩብኝ እነሱ ናቸው። ከልጅነቴ ጀምሮ፣ ለሥራ የተለየ ትኩረት እንድሰጥ አድርገውኛል። ነገሮችን በነፃነት እንድሞክር አበረታተውኛል።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴን የተከታልኩት፣ አስኮ በሚገኘው ቃሌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን የተከታተልኩት ደግሞ፣ ባሸዋም ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ነው። የተለያዩ ፈተናዎችን ውጤት በተመለከተ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና 95%፣ በአጠቃላይ ትምህርት ማጠናቀቂያ (10ኛ) ፈተና 3.7፣ በከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ደግሞ 490 አምጥቻለሁ።

በከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ባስመዘገብኩት ውጤት መሰረት፣ የከፍተኛ ትምህርቴን እንድከታተል የተመደብኩት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን፣ በዩኒቨርሲቲውም በቲያትር ጥበባት የትምህርት ክፍል የአራት ዓመት ትምህርቴን ተከታትዬ በ3.7 አማካይ ውጤት በዲግሪ ተመርቄአለሁ።



ቤዛዊት ፍቃዱ

ከምረቃ በኋላ፣ የራሴን ማንነት መቅረፅ፣ የወደፊቱን የህይወቴን አኪያሄድ መመርመር ላይ የበለጠ ትኩረት ሰጥቻለሁ። በመሆኑም፣ ህይወቴን በአዲስ መንገድ የምመራበትን ሁኔታ መፈጠሩን መረዳት ችያለሁ። ነገሮችን ለየት ባለ መንገድ መረዳት እንዳለብኝ፣ ሃገሬን በይበለጥ ማገልገል የምችልባቸውን ሁኔታዎች ማሰላሰል እንዳለብኝ ተረድቻለሁ። በዚሁ መሰረትም፣ ከምረቃ በኋላ በተለያዩ መንገዶች እነዚህን ሁኔታዎች የተመለከቱ የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ጥረት አድርጌአለሁ፤ አያደረኩም እገኛለሁ። በአሁኑ ወቅት፣ በሥራው ዓለም በሙያዬ "አዲስ አርቲስት" በሚባል የፊልምና የድራማ ድርጅት ውስጥ በጸሃፊነትና በዳይሬክተርነት በማገልገል ላይ እገኛለሁ።

አብዱላዚዝ ሳዶ፡- የትውልድ ስፍራዬ፣ አርሲ ዞን ከበቆጂ 17 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘው መሮ በምትባል ስፍራ ነው። አንደኛ ደረጃ ትምህርቴን፣ አዳማ ከተማ በሚገኙ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች ነው የተከታተልኩት። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናን 83% በማምጣት በማለፌ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን እዚያው አዳማ በሚገኘው ጎሮ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትያለሁ። የአጠቃላይ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና ውጤቴም 3.8 ነበር። በዚህ ውጤቴም፣ የመሰናዶ ትምህርቴን እዚያው ጎሮ መሰናዶ ትምህርት ቤት ተከታትዬ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ውጤት ማስመዝገብ ችያለሁ። ሆኖም፣ በተለያዩ ችግሮች የተነሳ፣ በመደበኛው የትምህርት መርሃግብር የዩንቨርስቲ ትምህርቴን መከታተተል አልቻልኩም። በመሆኑም፣ አርሲ ዩኒቨርስቲ አዳማ ቅርንጫፍ በማታው መርሃግብር የኢኮኖሚክስ ትምህርቴን በመከታተል ላይ እገኛለሁ። የ3ኛ ዓመት ተማሪ ነኝ። ቤተሰቦቼ መራሮ በምትባል ከተማ ውስጥ ይኖራሉ። አባቴ፣ በፊት በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ነበሩ። አሁን በእድሜ ምክንያት የሃገር ሽማግሌ ናቸው። ተጫሪ ሆነዋል ማለት ነው።

ትማር ፡- የፋዌ ስኮላርሽፕ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆናችሁበትን አጋጣሚ ብትገልፁልን?

ቤዛዊት ፍቃዱ ፡- የፋዌ-ኢትዮጵያ፣ ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሺፕ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆንኩት፣ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርቴን ባጠናቀቅሁበት ወቅት ነበር። ማስታወቂያው፣ መጀመሪያ በትምርት ቤታችን በተለጠፈበት ወቅት እምብዛም ትኩረት አልሰጠሁትም ነበር። መምህራኖቼ ናቸው እንድመዘገብ የገፋፉኝ። በወቅቱ፣ በወጣው ማስታወቂያ መሰረት፣ ለምዝገባ የወጡትን መስፈርቶች፣ በተለይም ጥሩ የትምህርት ውጤትና በኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተነሳ ትምህርትን ባማባቡ የመከታተል ችግር ውስጥ መሆን የሚሉትን በማሟላቴ፣ በፕሮግራሙ ልታቀፍ ችያለሁ። የስኮላርሺፑ አወዳዳሪ ባለሙያዎች፣ በአርግጥም ኢኮኖሚያዊ ችግር ውስጥ ሆኜ ትምህርቴን ለመከታተል የምታትር መሆኔን ለማረጋገጥ፣ ቤት ድረስ በመምጣት በተጨባጭ ያሉብኝን ችግሮች ማየት ችለዋል።



አብዱላዚዝ ሳዶ

አብዱላዚዝ ሳዶ ፡- የፋዌ-ኢትዮጵያ ስኮላርሺፕ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆንኩት፣ ለስኮላርሺፕ ፕሮግራሙ በወጣው ማስታወቂያ ውስጥ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማሟላቴ ነበር። መምህራኖቼ ችግሬን ያውቁ ስለነበር፣ ማስታወቂያውን ጠቁመውኝ ነበር የተመዘገብኩት። ስኮላርሺፑ በመስፈርትነት ካካተታቸው ጉዳዮች መካከል ዋናው አካዳሚክ ውጤት እንደመሆኑ፣ እኔ ደግሞ ቀደም ብዬ እንደጠቆምኩት፣ በመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተና ያስመዘገብኩት ውጤት እና 7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች ከክፍል አንደኛ አወጣ ስለነበር፣ የአካዳሚክ መስፈርቱን በሚገባ ማሟላት ችያለሁ። ከአካዳሚክ መስፈርት በተጨማሪ፣ ሌሎች መስፈርቶች፣ በተለይም በችግር ውስጥ ሆኜ ትምህርቴን እከታተል የነበርኩበት ሁኔታ፣ ለፕሮግራሙ እንድታጭ ካደረጉኝ ጉዳዮች መካከል ሌላው ነበር። በወቅቱ፣ ትምህርቴን አዳማ እከታተል የነበረው አጎቴ ጋር በመጠጋት ነበር። በወቅቱ የነበርኩበት የአኗኗሪ ሁኔታ፣ ትምህርቴን ባማባቡ እንድከታተል የሚያደርገኝ አልነበረም። በከፍተኛ ችግር ውስጥ ሆኜ ነበር ትምህርቴን እከታተል የነበረው። ከአጎቴ ልጆች ጋር ነበር ትምህርቴን እከታተል የነበረው። ይህንን የኑሮዬን ሁኔታ፣ ለስኮላርሺፕ ፕሮግራሙ ተማሪዎችን ለማወዳደር የመጡ የፋዌ ባለሙያዎች፣ በአካል መኖሪያዬ ድረስ በመምጣት ማረጋገጥ ችለዋል። ስለሆነም፣ የወጡትን መስፈርቶች ማሟላቴ በመረጋገጡ፣ የስኮላርሺፑ ፕሮግራም ተጠቃሚ ሆኜ ልመረጥ ችያለሁ።

ትማር ፡- የስኮላርሽፕ ፕሮግራሙ ተጠቃሚ መሆናችሁ በወቅቱ ምን ስሜት አሳድሮባችሁ ነበር?

ቤዛዊት ፍቃዱ ፡- በወቅቱ፣ የስኮላርሺፑ ፕሮግራሙ ውስጥ መታቀፌን ስሰማ ከፍተኛ ደስታ ነበር የተሰማኝ። በተለይም፣ ከብዙ ተማሪዎች መካከል መመረጥ መቻሌ በራሱ፣ እጅግ አስደሳች ጉዳይ ነበር። የወደፊት የህይወት አቅጣጫዬንም ሆነ የአይታ አድማሴን እንደገና እንድከልስ አድርጎኛል። አቅጣጫዬን ዳግም

አንዳስተካክል አድል ሰጥቶኛል። በህይወት ውስጥ፣ አንዳንዴ ማርሽ ቀያሪ፣ አቅጣጫ ለዋጭ ክስተቶች እንደመኖራቸው፣ ስኮላርሺፕ ፕሮግራሙ ከእኔ ህይወት አንፃር ከዚያ የሚመደብ ክስተት ነበር ብል ማጋነኔ አይሆንም። ስኮላርሺፑ፣ በራሱ ይዟቸው የመጣቸው እድሎች፣ በትምህርት አቀባበሌም ሆነ በአኗኗሬ ላይ ካመጣቸው ለውጦች በተጨማሪ፣ እርስበእርስ መደጋገፍንና መግባባትን የመሳሰሉ ለማህበራዊ መስተጋብሮች ቁልፍ በሆኑ የህይወት ተሞክሮዎች ላይ እጅግ አስፈላጊ ቁምነገሮችን አስተምሮኛል፤አስጨብጦኛል። ባለኝ አቅምም፣ ለሌሎች መትረፍ እንዳለብኝ አስገንዝቦኛል።

አብዱለዚዝ ሳዶ ፡- እንደዚህ ዓይነት እድሎች ማንንም ያስደስታሉ። በትምህርት ዓለም ድጋፍ ማግኘት በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ለትምህርት ውጤታማነት የራሱ ድርሻ/አስተዋፅኦ አለው። እገዛው በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ዘጠነኛ ክፍል እያለሁ ውጤቴ ካሉት ልጆች ከፍተኛ በመሆኑ፣ በፋዌ-ኢትዮጵያ በኩል በተመቻቸ እድል ኡጋንዳ ለጉብኝት ሄጃለሁ። ከእኔ በተጨማሪ፣ ቤተሰቤ በፋዌ ስኮላርሺፕ ባገኘሁት እድል በጣም ደስተኛ ነበሩ።

ትማር ፡- በስኮላርሽፕ ፕሮግራሙ መታቀፋችሁ በትምህርት አቀባበላችሁም ሆነ በሌሎች ሁኔታዎች አንፃር ያስገኘላችሁን ጥቅም ብትዘረዝሩልን?

ቤዛዊት ፍቃዱ ፡- የፋዌ-ኢትዮጵያ፣ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሺፕ ፕሮግራም የሰጠኝን ጠቀሜታ በተመለከተ በሶስት አብይት ጉዳዮች አንፃር መዘርዘር እችላለሁ።

1ኛ/ የትምህርት ጠቀሜታውን በተመለከተ፡- ስኮላርሺፕ ፕሮግራሙ፣ የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ ካላቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአንዱ (ባሸዋም ሁለተኛና መሰናዶ ትምህርቤት) እንድማር እድል ሰጥቶኛል። የተሻለ ትምህርት ቤት እንድማር እድል ከማግኘቴ በተጨማሪ፣ በስኮላርሺፑ አማካይነት የተለያዩ አጋዥ መጻህፍት፣ ከተለያዩ የትምህርት ግብዓቶች ጋር ይሟሉልኝ ነበር። ይህም፣ ክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ ቀልብን ከሚስቡ አሉታዊ ጣልቃ-ገብ ሃሳቦች ነፃ በመሆን መላ ትኩረቴ ትምህርቴ ላይ ብቻ እንዲሆን ረድቶኛል። ለትምህርት ውጤቴ ማማር ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል።

2ኛ/ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ፡- የስኮላርሺፕ ፕሮግራሙ ተጠቃሚ ከሆንኩ በኋላ፣ ምንም የገንዘብ ችግር አልነበረብኝም። በመሆኑም፣ የትምህርት ቤት ክፍያ ይሸፈንልኝ ነበር። ለአንድ ተማሪ ለትምህርቱ የሚያስፈልጉት ሁሉም ነገሮች ሙሉበሙሉ ተሟልተውልኛል። ከዚህ በተጨማሪ፣ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ተሟልተውልኝም፣ በየወሩ 600 ብር ይሰጠኝ ነበር። ይህ ክስተት ደግሞ፣ በራሱ የፈጠረብኝ ደስታ ወደር አልነበረውም። ፍፁም ደስተኛ ሆኜ ነበር ትምህርቴን የተከታተልኩት።

3ኛ/ ማህበራዊ ጥቅሙ፡- በስኮላርሺፑ አማካይነት ይሰጡ በነበሩ የተለያዩ ስልጠናዎች የተነሳ፣ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የነበረኝ አመለካከት በከፍተኛ ደረጃ ሊሻሻል ችሏል። በዚህ ረገድ፣ በትምህርት ቤቴም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ፣ "LEADERSHIP እና LIFE SKILL" በመሳሰሉ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ የተሰጡኝ የተለያዩ ስልጠናዎች፣ አመለካከቴ ላይ ለመጣው ለውጥ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል።

እነዚህን መሰል ስልጠናዎች፣ በፋዌ-ኢትዮጵያ ማስተርካርድ ፋውንዴሽን ስኮላርሺፕ ፕሮግራም ተሳታፊ ከሆኑ ከሌሎች ትምህርት ቤት ተጠቃሚ ተማሪዎች ጋር የመገናኘት እድልን ይሰጡ ስለነበር፣ ለእርስበእርስ ትውውቅ ከመርዳታቸውም በላይ፣ ጓደኛ እንዳፈራም ሆነ ኔትወርክ እንድዘረጋ ረድተውኛል። ራሴን በሚገባ እንድገልፅ አግዘውኛል። ራስን ችሎ መኖርን አስተምረውኛል። በነፃነት ማሰብን አዳብሮልኛል። ፕሮግራሙ፣ ከ2ኛ ደረጃ ትምህርቴ ባሻገር፣ በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ ወቅት በማህበራዊ ነክ ጉዳዮች ላይ ለነበረኝ አዎንታዊ ተሳትፎ ትልቅ ድርሻ ነበረው። በመሆኑም፣ ከስኮላርሺፑ መርህ አንዱ የሆነውንና "የተደረገልህን መልካም ነገር፣ አንተም ለሌሎች ከማድረግ አትቆጠብ (PRINCIPLE OF GIVING BACK)" የሚለውን መሰረት በማድረግ፣ በአቅሜ መርሁን ልተገብር ሞክሬአለሁ።

አብዱለዚዝ ሳዶ፡- በስኮላርሺፑ ፕሮግራሙ ያገኘሁትን ጥቅም በተመለከተ፣ በርካታ ማሳያዎችን መጥቀስ እችላለሁ። ከጽህፈት መሣሪያዎች ጀምሮ፣ ለአንድ ተማሪ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ የትምህርት ቁሶች፣ ለትምህርት አጋዥ የሆኑ መጻህፍት እና ሌሎች ግብዓቶች እንዲሟሉልኝ ተደርገውልኛል። እነዚህ ድጋፎች፣ ለትምህርት ውጤቴ ማማር ከፍተኛ አገዛ ነበራቸው። በተለይም፣ ለተለያዩ ትምህርቶች እንደማጣቀሻ የሚያገለግሉ መጻህፍት ለውጤቴ ማማር የነበራቸው አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ነበር። በኢኮኖሚ ረገድም በየወሩ ይሰጠኝ የነበረው የገንዘብ ድጎማ፣ አስፈላጊ ነገሮችን እንዳሟላ በእጅጉ ረድቶኛል። ሥራ ፈጠራ (ENTREPRENEURSHIP) የመሳሰሉ የተሳተፍኩባቸው የተለያዩ አቅም አጎልባች ስልጠናዎች፣ የእንግሊዝኛ ማሻሻያንና ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን የተመለከቱ ቱቶሪያሎች፣ ከትምህርት ውጤቴ ባሻገር አስከዛሬ ድረስ በማከናውናቸው የተለያዩ ተግባራት በጣም እየጠቀሙኝ ነው።

ትማር ፡- በትምህርት ቤት ቆይታችሁ ካስተዋላችሁት በመነሳት፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ሴት ተማሪዎችን በተመለከተ እነዚህ ተጠናክረው ቢቀጥሉ፣ እነዚህ ደግሞ ቢስተካከሉ የምትሏቸውን ብትዘረዝሩልን?

ቤዛዊት ፍቃዱ ፡- ከትምህርት ጋር በተያያዘ፣ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ላይ እንደማስተውለው፣ በአንዳንድ መምህራንም ሆነ በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ዘንድ ሴቶችንና ወንዶችን በተመለከተ ያለው አመለካከት/አይታ ሊስተካከል የሚገባው ይመስለኛል። እንደሚታወቀው፣ ከወንዶች ይልቅ፣ ሴቶችን ትምህርት ቤት ድረስ ተከትለዋቸው የሚመጡ ጉዳዮች አሉ። ማህበረሰቡ፣ ወላጆች እና የተለያዩ አምነቶች ሳይቀሩ፣ ለሴቶች የሚሰጧቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ። ስለሆነም፣ ትምህርት ቤት አካባቢ በሴቶች የትምህርት ቤት ሁለንተናዊ ተሳትፎ ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ ጉዳዮችን በመለየት፣ እያንዳንዱ በየትምህርት ቤቱ የሚገኝ ማህበረሰብ በተለየ ትኩረት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። ለዚህም ተገቢውን ትኩረትና ጊዜ መመደብ ይገባል። ሴት ተማሪዎችን፣ በየትምህርት ቤቱ ውስጥ ካሉ ከሌሎች ሴት ተማሪዎችም ሆነ መምህራን ጋር ማገናኘት፣ በዚህ ረገድ ጠቀሜታ አለው። እርስበእርስ መተጋገዝን ያዳብራል። ያለፍራቻ አንዳንድ ከሴቶች ጋር የተያያዙ ችግሮችን (ለምሳሌ፣ ከወር አበባ ጋር የተያያዙ፣ ከሴቶች ንፅህና መጠበቂያ/MODESS አጠቃቀም፣ ወዘተ.) በተመለከተ በነፃነት መወያየትን

ይፈጥራል፤ አመቺ ሁኔታዎች እዲፈጠሩም እገዛ ያደርጋል። እነዚሁ ሁሉ ሁኔታዎች፣ ለመማር ማስተማሩ ስኬት የሚኖራቸው ድርሻ፣ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ፣ ሴቶች ከትምህርታቸው በተደጋጋሚ ሲቀሩ የቀሩባቸውን ምክንያቶች ለማወቅ፣ በተለየ ትኩረት እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልጋል። እንደጓደኛ፣ እንደቤተሰብ ሆኖ ውይይት ማድረግ ጠቀሜታው እጅግ ከፍተኛ ነው። በዚህ ረገድ፣ ሴቶችን በተመለከተ የሚያጋጥሟቸውን የተለያዩ እንቅፋቶች፣ በትምህርት አቀባበላቸው ላይም የሚስተዋሉባቸውን ችግሮች አየለየ ከመፍትሄ ጋር ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር የሚያቀርብ እና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ የሚሠራ አካል እንዲቋቋም ማድረግ፣ በእጅጉ ጠቃሚ ነው። በተለይም፣ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚደርሱ ዖታዊና መሰል ጥቃቶች ተድበስብሰው እንዳይቀሩ፣ ጥቃት አድራሾች የሠሩት ጥፋት ትክክል እንደሆኑ አድርገው እንዳይቆጥሩ እና መሰል ክስተቶች እንዳይደጋገሙ፣ የዚህ አካል መኖር በእጅጉ ጠቃሚ ነው። ስለሆነም፣ እንዲህ ዓይነቱ አካል የሚያደርገው ዘርፈብዙ ጥረት፣ ለችግሮች የመፍትሄ አካል ከመሆን ባሻገር፣ ለመማር ማስተማሩ ከሚኖረው አዎንታዊ አስተዋፅዖ በተጨማሪ፣ መብትን ከማስከበር ጋር የሚያያዝ ነውና፣ ትምህርት ቤቶች ለዚህ ጉዳይ ካለፈው በተለየ መልኩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል።

አብዱለዚዝ ሳዲ፡- ሴት ተማሪዎች፣ በተለየ መልኩ መደገፍ እንዳለባቸው በፅኑ አምናለሁ። እነዚህ ተማሪዎች፣ በዛ ያሉ ተጨማሪ ሃላፊነቶች እንዳሉባቸው መርሳት የለብንም፤ በተጫባጭ የምናየው ሃቅ ነው። በማንኛውም መንገድ፣ ይህን ታሳቢ ያደረገ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል። በተለይም፣ ሴት እህቶቻችን በብዙ ጫና ውስጥ ሆነው ወደትምህርት ቤት እንደሚመጡና ትምህርታቸውንም እንደሚከታተሉ ተረድተን፣ ሁላችንም ይህን ጫናቸውን በተለየ ሁኔታ ተረድተን ለትምህርታቸው አስፈላጊ የሚባሉ ድጋፎችን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅብናል። እነዚህ ድጋፎች፣ በተለያዩ ተፅእኖዎች ውስጥ ያሉትን የህብረተሰባችንን ግማሽ አካል መደገፍ ስለሆነ፣ ሃገራዊ ፋይዳው እጅግ ከፍተኛ ነውና በትኩረት መንቀሳቀሱ ተገቢነቱ አያጠያይቅም። ከዚሁ አንፃር ቢስተካከል፣ ቢሻሻል ብዬ የምጠቁመው፣ በወንዶች በኩል የሚስተዋለው ትንኮሳ እየቀነሰ ቢሆንም፣ አሁንም ትኩረትን ይሻል። በማህበረሰብ ደረጃ ለሴቶች ያለው ግንዛቤ መሻሻል የሚታይበት ቢሆንም፣ አሁንም ትኩረት ሊነፈገው የማይገባው የማህበረሰባችን ዐብይ ጉዳይ መሆኑን በአፅንኦት አሳስባለሁ። "ሴት ልጅ ተምራ የት ልትደርስ ነው?" የሚለው አባባል፣ አሁንም በሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ላይ የራሱ ተፅእኖ እንዳለው በቅጡ ሊጤን ይገባል፤ ሙሉ በሙሉ ከህብረተሰቡ ውስጥ ይህ አሉታዊ አመለካከት እስኪወገድ ድረስ፣ የተለያዩ የግንዛቤ ማስፊያ መንገዶችን ሁላችንም በትኩረት ማከናወን ይጠበቅብናል።

ትማር፡- በአርአያነት የምታዩዋት ሴት ማነች? (በአካባቢችሁም ሆነ በሃገር አቀፍ ደረጃ)

ቤዛዊት ፍቃዱ፡- ለእኔ አርአያ የማደርጋትና በአእምሮዬ ውስጥ የሳልኳት ሴት፣ በገሃዱ ዓለም ከማያቸው ሴቶች ይልቅ፣ ከልጅነቱ ጀምሮ ሁሉም ሰው መሆን የሚፈልገውን እንደሚመኝ ሁሉ፣ ሁሌም አርአያ የማደርጋት ያቺን በልጅነቴ አእምሮዬ ውስጥ ቀርጬ ያስቀመጥኳትን ሴት ነው። ቤዛዬ፣ አርአያዬ የማደርጋት ይችን ሴት ነው። ደስ የማይል ነገር ያጋጥመኛል። ተስፋ መቁረጥ ሊኖር የሚችልበት አጋጣሚም ሊከሰትብኝ ይችላል። በጣም አስደሳች ጊዜም ሊኖረኝ ይችላል። በእነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች ውስጥ አእምሮዬ ውስጥ ያለችውን ማንነቴን ነው የማስታውሰው። "እከሌ ነች አርአያዬ" ከምል ይልቅ፣ አርአያዬ የማደርጋት ይህቺን ሴት ነው።

አብዱለዚዝ ሳዲ፡- እንደሃገር በአርአያነት የማያቸው ሴት፣ የክብር ዶ/ር አበበች ጎበና ናቸው። የአሳቸው አርአያነት ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ ለሁሉም የሰው ልጅ ነው ማለት እችላለሁ። ወላጅ አልባ የሆኑና ደጋፊ የሌላቸውን ብዙ ህፃናትን አስተምረው ለወግ ማእረግ ማብቃታቸው በእጅጉ ያስደንቀኛል። ከፈጣሪ በታች ባደረጉት በዚሁ የተቀደሰ ተግባራቸው፣ ምጊዜም አርአያዬ አድርጌ አስታውሳቸዋለሁ። ከምንም ተነስተው፣ ብዙ ውጣውረዶችን በማለፍ ለዚህ ሰውን መርዳት ለሚለው በጎ ተግባራቸው መብቃታቸው፣ ራሱ አርአያዬ አድርጌ እንድናገርላቸው ካደረጉኝ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። ማንኛችንም ከወሰንን፣ በማንኛውም የህይወት ጎዳና ውስጥ በአሸናፊነት መዝለቅ እንደምንችል ያስተማሩኝ ናቸው፣ የክብር ዶክተር አበበች ጎበና።

ትማር፡- ስለወደፊት ዓላማችሁ ብትነግሩን?

ቤዛዊት ፍቃዱ ፡- ዓለምአቀፍ የፊልም ዳይሬክተር መሆን እመኛለሁ። ባህላችንን በፊልም ቀርጬ በዓለምአቀፍ ደረጃ ማሳየት እፈልጋለሁ። በተለይም፣ በርካታ የእኛ የሆኑ ሃገራዊ መገለጫዎቻችን ያሉ ቢሆንም፣ ዓለም እያወቀን ያለው አሉታዊ በሆኑ አንዳንድ ጉዳዮቻችን ብቻ ነው። ይህን በፊልም ጥበብ መለወጥ ምኞቴ ነው። በእኛም ውስጥ ያለውን ብዙ ጥሩ ያልሆነውን አስተሳሰብ ለመቀየር፣ በዚሁ የፊልም ጥበብ እውቀቴ ለመቀየር ያለኝ ፍላጎት ከፍተኛ ነው። እንዲያውም በዋናነት መጀመር የምፈልገው፣ በሃገር ውስጥ ያለውን ይህን አሉታዊ ስሜት በመቀየር ነው። ዓለምአቀፉን፣ በቀጣይነት የምሰማራበት ይሆናል።

አብዱለዚዝ ሳዲ፡- ለወደፊቱ በዋና ዓላማነት የምይዘው፣ በትምህርቴ ዓለም መቀጠል ነው። በቀጣይ ዓመት፣ አሁን በማታው የትምህርት ፕሮግራም እየተከታተልኩ ያለሁትን ትምህርት እጨርሳለሁ። ቢያንስ አሰከማስተርስ እቀጥላለሁ። ሌላው ዓላማዬና ፍላጎቴ፣ በተሰማራሁበት የንግዱ ዓለም በስፋት መሰማራት ነው። ለዚህ ፍላጎቴ እውን መሆን፣ አቅሜን በተለያየ መልኩ ማሳደግ እንዳለብኝ እገነዘባለሁ። ለአቅሜ ማደግ ደግሞ፣ የተለየ ትኩረት አሰጣለሁ። ይህም ሁኔታ፣ በቢዝነሱ ዓለም የሚኖረኝን ስኬት ይበልጥ ያሳካልኛል፤ በውስጤ ያለውን ሰውን የመርዳት ፍላጎቴን በበለጠ ጥንካሬ እንዳስቀጥል ያግዘኛል የሚል እምነት አለኝ። በመሆኑም፣ ሰውን መርዳት የምችልበት ተቋም የማቋቋም ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ። በተለይም፣ በአናቴ ከደረሰው ህመም በሚገባ እንዳስተዋልኩት፣ የአእምሮ ችግር ያለባቸው ሰዎች የተለየ ክብካቤና ትኩረት የሚሹ ናቸውና፣ እነሱን የመርዳት ዓላማ ያነገበ ተቋም ለማቋቋም ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ። በፈጣሪ እርዳታ፣ ይህንና ሌሎች ሰዎችን መርዳት የምችልባቸውን ተቋማት እንደአቅሜ እውን እንደማደርግ ተስፋ አለኝ።

ከዚህም ከዚያም ፪

•ከአርቲስት ትእግስት በቀለ አንደበት

ሮዝ፡- ይሄን ቃለምልልስ ከመጀመራችን በፊት በነበረን ቆይታ እንዳስተዋልኩት አንቺ ልጅሽን በአማርኛ ነው የምታወሪው። ባለቤትሽ ደግሞ በጣሊያንኛና በእንግሊዝኛ። ልጃችሁ ቃላትን እየተላመደ ባለበት በዚህ ወቅት ይህ የቋንቋ መደበላቅ ችግር አይፈጥርበትም?

ቲጂ፡- ይህጉዳይ፣እንዳንተሁሉእኛንም አሳስቦን ዶክተሮችን አነጋግረን ነበር። ህፃናት፣ ልጆች አፍ ከመፍታታቸው በፊት ባለው ጊዜ ከአስራ አምስት በላይ ቋንቋዎችን የመቀበል ችሎታ አላቸው። ለመናገር ይዘገዩ ይሆናል። አፍ ሲፈቱ ግን ሁሉንም አውቀዋቸው ይገኛሉ። በዚህ የተነሳ፣ ልጄ ከእኔ ጋር በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ በአማርኛ ነው የማናግረው። አማርኛ እንዲለምድ ነው የምንፈልገው። ባለቤቴ ብዙ ጊዜ በጣሊያንኛ ነው የሚያወራው።እኔና ባለቤቴ ደግሞ በእንግልዝኛ እናወራለን። ስለዚህ ልጃችን ሶስቱንም ቋንቋዎች ይዞ የሚያድግ ይመስለኛል።

ምንጭ፡- ሮዝ መጽሄት፣ሐምሌ 1999 ዓ.ም.

•የታላቁ አርቲስት የጥላሁን ገሠሠ ትዝታ

በትዳር በኩል የሚገጥመኝ ሰዎች በጥሩ ሁኔታ የሚቀበሉኝና የሚከብሩኝ ናቸው። በህጋዊ ጋብቻ ያገባኋቸውና በሚስትነት የማውቃቸው፡-

1.ወ/ሮ አሥራት ዓለሙ
2.ወ/ሮ ሂሩት መስፍን
3.ወ/ሮ ፌሪያል አህመድ
4.ወ/ሮ ማርታ ሲማቶስ
5.ወ/ሮ ሮማን በዙ ናቸው።

ስለአስራቴ ምን ብዬ ማውራት እንዳለብኝ አላውቅም። የመጀመሪያ ትዳሬና እናቴ ናት። ፈጣሪ ሐጢያት አለብህ ቢለኝ እንኳን የመጀመሪያው እርሷን የበደልኩት በደል ነው። ከአሥራቴ አምስት የልጅ ፍሬን አይቻለሁ።ምንያህል ጥላሁን፣ እኔውንኝ ጥላሁን፣ ንፁህብር ጥላሁን፣ የዓለም ዘውድ ጥላሁን እና ሄላገነት ጥላሁን ይባላሉ። ከአስራቴ በኋላ ሂሩትን አግብቼ በ2ዓመት የትዳር ቆይታችን ናታን እና ናሆሚ የሚባሉ ልጆችን አፍርተናል። ሂሩት መሳፍንትና መኳንንት ከሚባሉ ቤተሰቦች የተወለደች ልጅ ነች። በእርግጥ ነው በቤተሰቦቿ ሳይሆን ሙያዬ ነገሥታትንም ይማርካል።ሂሩቴ ሴትነቷና ክብሯ፣ ለእኔ የነበራትም ፍቅር ከፍተኛ ነበር። ከሷ ጋር እንደተለያየን ወ/ሮ ቀለሟ ማሞን አግብቼ (ህጋዊ ጋብቻ አይደለም) ቃልኪዳን ጥላሁን የተባለች ሴት ልጅ ወልጃለሁ። ከዚያ በመቀጠል ከፌሪያል አህመድ ጋር ተጋብተን በአካል እና ዳንኤል ጥላሁን የተባሉ ሁለት ልጆች ወልደናል። በማስከተል፣ ከማርታ ሲማቶስ ደግሞ ናሆሚ እና ፑፒ የተባሉ ልጆች ተወልደዋል ። በመጨረሻም፣ ከማከብራትና ከማፈቅራት ከወ/ሮ ሮማን በዙ ሔለን እና ዮናታንን ወልጃለሁ። የሚገርመው በአጋጣሚ ከሂሩት እና ከማርታ ናሆሚ የሚል ተመሳሳይ መጠሪያ ያላቸው ልጆች አሉኝ። ግን ባለማወቅ የተፈጠረ አጋጣሚ ነው። እንግዲህ በአጠቃላይ 14 ልጆች አሉኝ ማለት ነው።

ምንጭ፡- ሎሚ መጽሄት ሰኔ 14-ሰኔ 20/2006 ዓ.ም.

•የትጉህ ሰው መገለጫ ተግባራት

- ስለ ኑሮ ያለው ሀሳብ ቁርጥ ያለ ሆኖ፣ ዓላማ ላይ የተመረኮዘና ዓለማውን እያሻሻለ የሚሄድ፣
- ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚያቅድና የሚያስብ፣
- ሥራን በቅደም ተከተል አስገብቶ ሊያከናውን የሚችል ወይም እንዲከናወን የሚያደርግ፣
- የሰው ዓላማ ለመፈፀም ሰዓትና ቀጠሮ እጅግ የሚያከብ ፣ ቃሉን የማይለውጥ፣ የማይዘላብድ፣ ከሃሳቡ ጋር የተነፃፀረ እውነትን የሚያዘወትር፣
- አካላዊ ንፅህናውን የሚጠብቅ፣
- መከፋቱን ወይም መደሰቱን በጓደኞቹ ወይም በቅርፍሮቹ ፊት ላይ የማይገልፅ ረጋ ያለ የተቃና አንደበት ያለው፣
- ግላዊ ተግባሮችን ከቅርፍሮቹ ጋር የማይካፈል፣
- የአለቃውን ጠባይ ፈፅሞ የሚያውቅ፣
- ወሬና ቀልድ በሥራ ጊዜ የማይቀላቅል፣
- ስለሌላው ሰው እጅግ የሚያስብ፣
- በዘይና በእቅድ ሊሠራ በመዘጋጀት ከእሱ በእውቀት ወይም በሥራ የሚበልጡትን እየጠየቀ ሥራን የሚያሻሽል፣ ቀልጣፋ ሠራተኛ ትጉህ ሊባል ይችላል።

ምንጭ፡- መነን መጽሄት 13ኛ ዓመት ቁጥር አንድ ጥቅምት 1961 ዓ.ም.





የአምስተኛው ዙር የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የስኮላርሺፕ ፕሮግራም የ5ኛው ዙር ተማሪዎች በከፊል
Mastercard Foundation Fifth Coheret Gradutes



የፋዌ - ኢትዮጵያ አህጉራዊ ጽ/ቤት ምክትል ዳይሬክተር፣ በማስተርካርድ ስኮላርሺፕ ፕሮግራም አተገባበር ወቅት በሜንቶርነት አስተዋፅኦ ላደረጉ መምህራን ሽልማት ሲያበረክቱ
Awarding teacher mentors by Teresa Omondi, FAWE-RS Deputy Executive Director



የአምስተኛው ዙር የማስተርካርድ ፋውንዴሽን የስኮላርሺፕ ፕሮግራም የምረቃ ሥነስርዓት ተሳታፊ እንግዶች በከፊል
Partial view of gusts at The Fifth Cohort Graduation Ceremony


TOP TEN HOTEL
E-Ethiopia Chapter General Assembly
March 19,
Top Ten Ho
Addis Ababa

Message from the Director General of FAWE-Ethiopia



W/ro Roman Degefa

The attention given to women's education is related to the understanding of the key role and superior position of women in order to facilitate the success of a country's comprehensive changes in the economic and social sectors. Currently, understanding the decisive role of women in any development and other national affairs, many countries, especially all the developing nations, are giving special emphasis for girls' education in a diversified way from the preceding times.

FAWE-Ethiopia, as an indigenous civil society organization, understanding the significant role and importance of women's universal participation in our country's progress towards making a success story in fighting poverty and backwardness once and for all, it is carrying out various lofty activities by designing multi-faceted programs that enable women to promote their participation in education and improve their skills in various fields,. FAWE-Ethiopia, since its establishment, is fully implementing the comprehensive programs, which enable female students to increase their efforts in making very valuable progress in their studies through withstanding the negative pressures and stereotypes they encountered in their daily lives. Being actively involved in this process, many women successfully completed their high school education, and joined different higher education institutions.

These same students were also able to graduate from various higher education institutions and become good citizens who can serve their country in various fields. The success of these young people indicates that female students of our country have a robust determination and viable ability to reach the level they aspire if the conditions are favorable for them. FAWE-Ethiopia, on behalf of its family members, FAWE-Ethiopia staffs and its partners, I would like to take this opportunity to extend my appreciation for these successful women and as well as male students who have been supported by various scholarship programs and have been able to play their part in the success of FAWE-Ethiopia's goals and visions.

FAWE-Ethiopia, with its female students focused various activities; the vigorous partnership it has been able to create with various local and foreign partners and stakeholders has played a crucial role in achieving tangible results. For this, the activities performed during this fiscal year and the actually attained rewarding activities are living witnesses. On this occasion, these partners and stakeholders, understanding the purpose and the vision of FAWE-Ethiopia, and recognizing that it will carry out effective tasks in the future, once again on behalf of FAWE-Ethiopia, I would like to express my sincere thanks to these partners who have been on our side with their peculiar and notable supports. I would like to express my belief that this support will strongly continue to enable us make further achievable steps and register vivid results.

"Educating women is educating society!"

FAWE-Ethiopia's Accomplishments in the year 2022

FAWE-Ethiopia is one of the FAWE 34 National Chapters established in 1994 just after 2 years of the founding of Forum for African Women Educationalists Regional Secretariat (FAWE-RS). It was registered and licensed as NGO by the Ministry of

Justice in 2003, and reregistered as Ethiopian Residents Charity Organization in 2010 by the Ethiopian Charities & Civil Society Organizations Agency. Furthermore, it was again registered as Civil Society Organization (CSO) by the Authority for Civil Society Organizations in 2018.

In order to achieve its overall objectives, FAWE-Ethiopia, in collaboration with the relevant Governmental and Non-Governmental Organizations, different stakeholders, and FAWE-RS is currently running four active projects in various regions of the country. FAWE-Ethiopia has been implementing several significant activities and registered vital and salient results through these four projects in the year 2022. The four projects are the Mastercard Foundation Scholarship Program, Break Free project, MakeWay project, and CSSP2 (Civil Society Support Program2). These all projects have been actively executed in Bahirdar and Debrebrihan cities of Amhara National Regional State; in Aleltu Woreda and Adama and Sheno cities of Oromia National Regional State; in Hawassa city of Sidama National Regional State; and in Addis Ababa city Administration. Relying on these four projects, FAWE-Ethiopia has planned and implemented several program activities in the year 2022. Key achievements of these four projects in this fiscal year are reflected in detail next.

Mastercard Foundation (MCF) Scholarship Program

In order to help economically disadvantaged but brilliant scholars who can become leaders of their country, FAWE-Ethiopia, in partnership with Mastercard Foundation, has developed and implemented the Mastercard Foundation Scholarship Program since 2014. This scholarship Program has been carried out in the cities of Bahirdar, Hawassa, Adama and Addis Ababa of Amhara, Sidama, Oromia National Regional States and Addis Ababa City Administration respectively. Because of this scholarship program, FAWE-Ethiopia Chapter has been undertaking various activities in 2022. The main achievements of this project are depicted by the following activities:

•FAWE-Ethiopia conducted The Gender Responsive Pedagogy (GRP) Training of Trainers (ToT) for teachers from eight target schools at Jerusalem Children and Community Development Organization JeCCDO training center at Bishoftu town from May 19-21, 2022. The training substantially equipped teachers with knowledge, skills and attitudes for gender responsive pedagogy, enabled them to develop and use gender responsive methodology that can ensure equal participation of boys and girls in the teaching and learning process and to assist school management to mainstream gender issues. The trainees were drawn from 8 partner schools in Adama, Hawassa, Addis Ababa and Bahir Dar. 19 (10 females) teachers and school directors/ vice directors took the training. Furthermore, those teachers who got the Training of Trainers (ToT) cascaded the GRP training for other teachers in return at their respective schools. The cascading training was successfully offered for 289 (85 females) teachers at Goro school (Adama); Tabor school (Hawassa); Millennium school (Addis-Ababa); and Tana-Haik school & Bahir Dar academy school (Bahir Dar).



Gender Responsive Pedagogy (GRP) Training

•FAWE-Ethiopia also organized the TUSEME (Let Us Speak Out!) Training of Trainers (ToT) at Goro School (Adama) from 5 to 7 May 2022. The training provided teachers with the necessary knowledge and skills that helped them facilitate the introduction and running of TUSEME in their respective schools, with the purpose of empowering girls as well as boys for their social and academic development. The trainees were drawn from 8 partner schools in Adama, Hawassa, Addis Ababa and Bahirdar. 18 (10 females) teachers and school heads have received the ToT.

